በጋምቤላ ክልል የጋምቤላ ከተማ እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመጓግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተተኳሪነት

በ

ፀሐይ ወርቁ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሑፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል

በአማርኛ ማስተማር ስነዘዴ የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሣይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

ነሐሴ 2011ዓ.ም

ጅማ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እቅድ አዘገጃጀት እና ትግበራ ፍተሻ፤በጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተማ እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመጓግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተተኳሪነት

በ

ፀሐይ ወርቄ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ፅሁፍ አማርኛት ምህርት ክፍል በአማርኛ ማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ጌታቸው አንተነህ (ዶ/ር)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የደህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ –ጽሑፍ–አማርኛ ትምህርት ክፍል

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

ጅማ

## ማረጋገጫ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እቅድ አዘገጃጀት እና ትግበራ ፍተሻ፤ በጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተማ እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተተኳሪነት ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ፣ የደህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ –ጽሑፍ– አማርኛ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይ ህጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ ወጥ የራሴ ስራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸውን ልዩ ልዩ ድርሳናትም በትክክል በዋቢ የተገለጹ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ ስም ፀሐይ ወርቄ

ፊርማ ..............

ቀን ...................

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ -የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ሚያገባኬቅጽ

አማካሪ .............................. ፊርማ .............. ቀን

........................

የውስጥ ፈታኝ ......................... ፊርማ .......... ቀን

......................

የውጭፈታን .......................... ፊርማ ............

ቀን..................

ማውጫ

አርዕስት.................................................................................................ገጽ

ምስጋና ............................................................................................. I

አበርክቶ............................................................................................ II

አጠቃሎ................................................................................................................................... III

ምእራፍ አንድ መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ .......................................................................1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት
..............................................................................4

1.3. የጥናቱ ዓላማ
...........................................................................................7

1.4. የጥናቱ
ጠቀሜታ.............................................................................................8

1.5. የጥናቱ ወሰን
.............................................................................................8

1.6 የቁልፍ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም
ብያኔ.............................................9

ምዕራፍ ሁለት. የድርሳናት ክለሳ

2.1 ፅንሰ ሀሳባዊ /ቃለ ነቢባዊ መሠረቶች
........................................................10

2.1.1 የእቅድ ምንነት
...............................................................................10

2.1.2 የትምህርት እቅድ ምንነት
.............................................................................10

2.1.3 የትምህርት እቅድ አስፈላጊነት
.............................................................
.11

2.1.4 የትምህርት ዕቅድ ሞዴሎች (Models of lesson plan)
..............................12

2.1.5 የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት
............................................................16

2.1.5.1 ዕቅዱን ማዘጋጀት
.............................................................
.....................17

2.1.5.2 ዕቅዱን መተግበር
.............................................................
...................18

2.1.5.3 ዕቅዱን ማጣማም
.............................................................
...................19

2.1.6 የቋንቋ ትምህርት እቅድ ዓይነቶች
.............................................................
...20

2.1.6.1. ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ
.............................................................
.......20

2.1.6.2. ሣምንታዊ የትምህርት ዕቅድ
.............................................................
.....21

2.1.6.3. ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ..............................................................22

2.1.7 በእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር ወቅት የባለ ድርሻዎች ተገባር...........................23

2.1.7.1 የርዕሰ መምህሩ ሚና....................................................................23

2.1.7.2 የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ሚና........................................................23

2.1.7.3 የመምህሩ ሚና........................................................................24

2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ.................................................................25

2.2..1 የብሉምስ ታክሰኖሚ የመማር ስፍረቶች

(Bloom'staxonomyoflearningDomains)..................................................26

2.2.1.1 አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain).........................................28

2.2.1.2 ክህሎታዊ ምድብ (Psychomoter domain)......................................28

2.2.1.3 ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)..........................................30

2.2.2 የትምህርት እቅድ እርከኖችች (Lesson Plan Phases)………….31

2.3. የተዛመጅ ፅሁፍ ቅኝት..........................................................33

ምዕራፍ ሶስት የአጠኚን ዘዴ

3.1. የጥናቱ ዘዴ...........................................................................36

3.2.የጥናቱ ተሳታፊዎች እና ናሙና አመራረጥ............................................36

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘደዎች...................................................36

3.3.1. የሰነ ደፍተሻ…………………………………………………………………………37

3.3.2. ምልከታ.........................................................................................37

3.3.3. ቃለ መጠይቅ....................................................................................38

3.4 የጥናቱ ሂደት........................................................................................38

3.5.የመረጃ መተንተኛ ዘዴ.............................................................................39

ምዕራፍ አራት፡ - የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

4.1 የተጠኝዎች ዳራ...................................................................... 40

4.2 በልዩ ወረዳው በሚኙ አምስት የመማግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተገሚኟዎች አሰባሰብዚደት.......................................................................................41

4.2.1 አጠቃላይ የእቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ዳሰሳ...................................42

4.2..2 በየትምህርት ቤቶቹ የሚገበሩት እለታዊ እቅዶች ፍተሻ.........................42

4.3 ከሰነ ፍተሻ የተገኙ ውጤቶች ትንተና..................................................66

4.3.1. የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት

ከአዕምሮአዊ ምድብ

አንጻር......................................................67

4.3.2 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከይበልጥ

ክሂሎታዊ ምድብ

አንጻር.............................................................68

4.3.3 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከስሜታዊ ምድብ አንጻር ........49

4.4.4 ከክፍል ምልከታ የተገኘ ሚጃ ትንተና.............................................50

4.4.4. በቃለ መጠይቅ የተገኙ ሚጃዎች ገለጻና ማብራሪያ................................54

4.4.4.1.መምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙ ሚጃዎች ገለጻና ማብራሪያ...............56

.4.4.2.ከምክትል ርዕሳነ መምህራን እና ከክፍለ ትምህርቱ ተጠሪዎች

በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ገለጻና
ማብራሪያ.....................................89

4.6. የውጤት ትርጎማ ማብራሪያ (Discussion)
......................................69

4.4.1 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት

ከአዕምሮአዊ ምድብ ክፍሎች
አንፃ.........................................................69.

4.4.2 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት

ከክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች
አንጻር.......................................................71

4.4.3 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት

ከስሜታዊ ምድብ ክፍሎች
አንጻር.......................................................74

ምዕራፍ አምስት፡ - ማጠቃለያና
አስተያየት....................................................93

5.1
ማጠቃለያ.........................................................
......................93

5.2.
አስተያየት.......................................................
.......................94

ዋቢ
መፃህፍት.........................................................
............................96

አባሪዎች ....................................................................

# ምስጋና

በቅድሚያ ሁሉን ቻይ ለሆነው ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ጊዜያቸውን ሰውተው ሳይሰለቹ ርዕሱን ከማፅደቅ ጀምሮ አጠቃላይ ስራውን ደጋግመው በማየት ቀናውን መንገድ ለመሩኝ፣ የተለያዩ ማጣቀሻዎችን በማስጠት ትብብራቸውን ለቸሩኝ ውድ አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ፣ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ በመቀጠልም የተጠቃለለውን ስራ በማንበብ ገንቢ የሆነ ሙያዊ አስተያየታቸውን የሰጡኝን አቶ በቃሉ ፈረደን በጣም አመሰግናለሁ የቤተሰቡን ሃላፊነት በመሸከም ልጆቻችንን በማከባከብ ከጎኔ ሆኖ ላበረታታኝ ውድ ባለቤቴ ጥጋቡ ተክሌ፣ በዚህ ትምህርት ምክንያት ለናንተ የሚገባችሁ ጊዜ ለተሻማሁባችሁ ውድ ልጆቼ በአማኑ ጥጋቡ እና ዮናታን ጥጋቡ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ ይህን ጥናት ስሰራ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ መረጃ በሰበሰብኩበት ወቅት ጊዜያቸውን ሰውተው በቅንነት መረጃ ላቀበሉኝ የኤሊያ፣ መቅደ፣ ባዝየል፣ አከዶ፣ ኢታንግ እና ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም ይህን ስራ ስሰራ ሀሳብ አስተያየታቸውን ለለገሱኝ እና በፀሎት ላሰቡኝ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳቸው እላለሁ፡፡

# ምእራፍ አንድ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰዉ ልጅ ስራዉን ዉጤታማ ለማድረግ በዕቅድ መመራት አለበት።ምክንያቱም ዕቅድ ሥራችንን እንዴት እንደምንሰራ፣ በምን እንደምንሰራ የትና መቼ፣ ከማን ጋር እንደምንሰራ የመሳሰሉትን አበይት ጉዳዮች አቅጣጫ የምናስይዝበት ዓይነተኛ መንገድ ከመሆኑም በላይ የቅድመ ሥራ ትልም በስርዓቱ በማስቀመጥ እና ያንን ዕቅድ በአግባቡ በመተግበር የሚያግዘን ሁነኛ መንገድ ነዉ። ይህንን አስመልክቶ ጀንሰን /Jensen (2001) ሲገልጹ፤ የትምህርት እቅድ ለመምህራን የትምህርቱን አላማ እንዲመርጡ፣ የተለያዩ ተግባራትን እና ከአላማ ጋር የተያያዙት ክንውኖችን በቅደም ተከተል እንዲያደራጁ፣የሚያስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎችን፣ እያንዳንዱ ተግባር የሚፈጅበትን (የሚወስድበትን) የጊዜ ርዝማኔና ተማሪዎችን እንዴት በቡድን እንደሚያደራጁ ሆን ብለው ተዘጋጅተው እንዲያስቡ ለማድረግ እድል ይሰጣቸዋል። በማለት ካብራሩ በኋል አክለውም፤መምህራን ከአንዱ ተግባር ወደ ሌላው ተግባር ለመሸጋገር፣በአሁኑ እቅድ እና በማንኛውም ባለፈው ወይም በወደ ፊት እቅዶች ያለውን ቁርኝት በመማር ማስተማር ሂደት እና በተግባራዊ ግምገማ ያለውን ተዛምዶ የሚያንፃባርቁበት ነው። ምክንያቱም መምህራኑ ይህንን ግንኙነት የሚረዱት እና አውቀው የሚተገብሩት ግንኙነቱን ለተማሪው በማሰራጨት እና ዕቅዱን በጣም ትርጉም አዘል ለማድረግ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል በማለት ያስቀምጣሉ።

ትምህርት ተፈጥሮ ያላትን እምቅ እዉቀት ለመገንዘብ ወሳኝ ነገር ቢሆንም የሰዉ ልጅ ለመማር ያለዉ አቅም ዉስን ነዉ። ስለሆነም በርካታ ጉዳዮችን አግበስብሰን አንወስድም። በመሆኑም ሁሉንም ክህሎቶች ባንዴ ለመማር በጣም አስቸጋሪ ነዉ የሚሆነው። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች በተፈጥሮ ራሰን በራስ ለማስተማር ተፈላጊዉ አቅም ወይም ችሎታ ላይኖራቸው ይችላል። ስለዚህ ትምህርትን በእቅድ ማገዝ የግድ ይላል። የትምህርት ዕቅድ ደግሞ በአግባቡ ከተከናነ በትንሹም ቢሆን ለመማር አቅም ማጎልበት እንደ ግብዓት በመሆን ያገለግላል። የትምህት እቅድን ጠቀሜታ ምሁራን በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል። ፋረል/Farrell / (2002) እንደገለፁት የትምህርት ዕቅድ ለመምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት ዉስጥ ምን ያህሉን መሸፈን እንዳለባቸዉ የሚገነዘቡበት የስነ ዘዴ ምህዳር ነዉ ይላል። ስፕራት/Spratt, et al /

(2005) በበኩላቸዉ ሲገልጹ የትምህርት ዕቅድ ማለት ሲያስተምሩ ምን ዓይነት ቁሳቁስ መጠቀም እንዳለባቸዉና በምን ዓይነት ስነ ዘዴ ማስተማር እንዳለባቸዉ መንገድ የሚያሳይ አፅንኦታዊ የትምህርት ይዘት ነዉ። የመምህሩ ዕቅድ ማቀድና በትክክል ዉሳኔ ስጭነቱ የተማሪዎችን ባህሪ መቅረጽ ላይ ከፍተኛ ሚና አለዉ። ምክንያቱም ተማሪዎችን በሥርዓት በክፍል ዉስጥ አመራር ለመስጠት ለመምህራኑ የትምህርት ዕቅድ አንዱ አመራጭ ስለሆነ ነዉ። እንደ ናኢሜ እና ሌሎች /Naimie et al./ (2012) አባባል የማስተማርና የመማር ስነ ዘዴዎች በጣም የተዛመዱ ናቸዉ። እናም ስለ ዕቅድ ሲናገሩ" በደንብ ማቀድ የሥራህ ግማሽ መንገድ ነዉ"ይላሉ።

በተለይ የትምህርት ስራ በእቅድ እየተመራ ተለክቶ እና ተመጥኖ የሚከናወን ተግባር ነዉ። አለበለዚያ ለማከናወን አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ከትምህርቱ የሚፈለገዉን ዉጤት ለማግኘት አዳጋች ይሆናል። ለዚህም ነዉ አብዛኛዎቹ ምሁራን ዕቅድ በትምህርት ዉስጥ ስላለዉ ሚና ከፍተኛነት አጥብቀዉ የሚመክሩት። ቀጥለዉ የተጠቀሱት ስለትምህር ትዕቅድ እንደሚከተለዉ ይገልጻሉ።

አሚኒኒክ እና ሌሎች/ Amininik et al./ (2000) ደግሞ አንደገለጹት የትምህርት ዕቅድ በት/ቤቶች የመምህራን መዘጋጀት በመማር ማስተማር ሂደቱ ዉስጥ ለመምህራኑ እንደ አቅጣጫ መሪነት ስለሚያግዛቸዉ የትምህርት ጥራትን ለማምጣት አንዱ መንገድ ነዉ ብለዉ ያምናሉ። እንደ ኮፖላ እና ሌሎች / Coppola et al. 2004) ገለጻ የትምህርት ዕቅድ ለትምህርት ዋናዉ መሠታዊ መዋቅርና ፍሬ ነገር ነዉ። ሁስቶን እና ቤች/ Houston and Beech (2002) እንደገለጹት ደግሞ በክፍል ዉስጥ የተለያየ ባህሪና የትምህርት አቀባበል ደረጃ ያላቸዉ ተማሪዎች ስላሉ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ለመምህራን ፈታኝ የሆኑ ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ቢሆንም ለነዚህ ፈታኝ ችግሮች የመፍትሄ ምንጩ ወሳኝ የሚሆነዉ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ነዉ።

የትምህርት ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ የትምህርት ዕቅዱ ሲዘጋጅ በየሳምንቱና በየዕለቱ ተከፋፍሎ መዘጋጀት አለበት። ዕቅዱን በተግባር የምንጠቀምበት፣ለሚሰጠዉ ሰዓት ኢኮኖሚያዊና የትምህርቱ ፕሮግራም የሚያጠናክር መሆን አለበት ይልዲሪም/ (Yildirim, 2003) ።

ማንኛዉም የትምህርት ቤቱ መምህር ያለ ዕለታዊ ዕቅድ ክፍል ውስጥ መግባት የለበትም። ምክንያቱም ግብ ያለዉ ትምህርት ለመስጠት ዕቅድ ዋነኛ መሣሪያ በመሆኑ ነዉ።

ከሀገራችን የቋንቋ መማርና ማስተማር ስነዘዴ ምሁራን አንዱ የሆኑት ማረዉ (1998፣ 168)፣ የቋንቋ መማርና ማስተማር ከዕቅድ ጋር ስላለዉ መስተጋብር እንደሚከተለዉ ያብራራሉ። የቋንቋ ትምህርት እና የመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ መስተጋብር ያላቸው እና ተደጋጋፊነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የቋንቋ ትምህርት መታቀድ ይኖርበታል ። ዕቅዱም ሰፋ ብሎ በምእራፍ አጠር ብሎ በዕለት ሊሆን ይችላል። በምዕራፋዊም ሆነ በዕለታዊ የታቀደው የቋንቋ ትምህርት ለምንድ ነው የማስተምረው? እንዴት ነው የማስተምረው? ትምህርቱ እንዴት ነው የሚገመገመው? የሚሉትን ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች መመለስ አለበት። የዕለታዊ ትምህርት ዕቅድ ዋና ጉዳይ ለምን ማስተማር እንደሚያስፈልግ፣ መቼ እና እንዴት ማስተማር እንደታሰበ፣ ምን አይነት የማስተማሪያ መሳሪያ መጠቀም እንዳስፈለገ እና እንዴትስ መገምገም እንደሚቻል በግልጽ እና በትክክል ማመልከት አለበት በማለት የቋንቋ መማርና ማስተማር ከዕቅድ ጋር ያላቸዉን ተያያዥነት ያስረዳሉ።

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን እንደሚያስረዱት የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ የማስተማር ስራችንን በአግባቡ ለመከወን የሚያስችል ሁነኛ ብልሀት እንደሆነ እና የምንፈልገዉን ዉጤት ለማስገኘት፤ የትምህርት ስራችንን ስናከናዉን የምንጓዝበትን መንገድ ለማወቅ፤ ለስራችን የሚያስፈልጉንን ግብአቶች ለመምረጥ ባጠቃላይ ለስራችን ዉጤታማነት መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን አጠንክረዉ እንደገለጹት እንረዳለን።

ይህ ጥናት በርዕሱ ዙሪያ ያሉ የተለያዩ ንድፈ ሀሳባዊ እውነታዎችን መሰረት በማድረግ በጋምቤላ ክልል በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትን ቃኝቷል። መሰረታዊ ትኩረት ያደረገዉ ግን በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ ነዉ። ምክንያቱም የእያንዳንዱ ቀን የትምህርት ሥራ ለማከናወን ወሳኝ እና ሥራዉን ለመከወን መሰረታዊ መንገድ በመሆኑ ነዉ። ጥናቱ በተጠናበት አካባቢ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር እና መማር ሂደት ወቅት ከእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር

ፍተሻ ጋር ተያይዘው ያሉትን ሁኔታዎች በመፈተሽ ከዘመናዊ የመማር ማስተማር እቅድ አፈጻጸም ጋር የተገናኙ ጥቁምታዎች ሰጥቷል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳት ዋናው ምክንያት ባስተማረችባቸው የተለያዩ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድ አዘገጃጀት የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍ ከተሰጠው የትምህርት ጊዜ ጋር አጣጥሞ ለማጠናቀቅ በሚያስችል መልኩ አለመከወኑን እና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዱ ከተሰጠው ጊዜና ሰዓት ጋር ተጣጥሞ ያለመዘጋጀት ችግር በስፋት ታስተውል ነበር።በመሆኑም ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌሎች ችግሮች ሊኖሩ ቢችሉም? የተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል በስርኣቱ ታቅዶ መማር ባለመቻላቸው ይሆን ወይ የሚል ጥያቄ አጥኚዋ ስላደረባትም ጭምር ነዉ።በተጨማሪም መምህራኑ የሚያቅዷቸዉ የትምህርት ዕቅዶች ተማሪዎቹ ለትምህርት የቀረበዉን ይዘት ከመረዳት እና ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉ ከማድረግ በተጨማሪ የተማሩትን ወደ ተግባር እንዲቀይሩ የሚያደርጉ በመሆናቸው ነው ወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥናት ለማረጋገጥ በመፈለጓ ነዉ።

ምንም እንኳን አማርኛ የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ከመሆኑም በተጨማሪ የጋምቤላ ክልላዊ መንግስት የስራ ቋንቋ ቢሆንም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስመዘግቡት ዉጤት ዝቅተኛ መሆኑ፣በቋንቋዉ ክህሎች ያላቸዉም ሁኔታ በደረጃዉ ልክ አለመሆኑ፣በብሄራዊ ደረጃ በሚዘጋጀዉ የአስረኛ ክፍል ፈተና የሚያስመዘግቡት ዉጤት በጣም አነስተኛ መሆኑ በግልጽ ይታያል። ለምሳሌ በ2009 እና በ2010 ያስመዘገቡት ዉጤት የሚከተለዉን ይመስላል።

**የኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በ2009 እና በ2010 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የኣማርኛ ቋንቋ ፈተና ዉጤት**

| ዓ.ም | የትምህርት ቤቱ ስም | የተፈታኝ ተማሪ ብዛት | | የሀገር አቀፍ ፈተና ዉጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | A | B | C | D | F |
| 2009 | ኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወንድ | 385 | - | 2 | 105 | 196 | 82 |
| | | ሴት | 171 | - | - | 32 | 86 | 53 |
| | | ድምር | 556 | | 2 | 137 | 282 | 135 |
| 2010 | ኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወንድ | 390 | - | 8 | 131 | 168 | 83 |
| | | ሴት | 164 | - | 7 | 44 | 68 | 45 |
| | | ድምር | 554 | - | 15 | 175 | 236 | 128 |

**የመኮድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በ2009 እና በ2010 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የኣማርኛ ቋንቋ ፈተና ዉጤት**

| ዓ.ም | የትምህርት ቤቱ ስም | የተፈታኝ ተማሪ ብዛት | | የሀገር አቀፍ ፈተና ዉጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | A | B | C | D | F |
| 2009 | መኮድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወንድ | 325 | - | - | 138 | 137 | 50 |
| | | ሴት | 96 | - | - | 41 | 46 | 9 |
| | | ድምር | 421 | - | - | 179 | 183 | 59 |
| 2010 | መኮድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወንድ | 249 | - | 1 | 98 | 102 | 48 |
| | | ሴት | 115 | - | - | 41 | 39 | 35 |
| | | ድምር | 364 | - | 1 | 139 | 141 | 83 |

**የአከዶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በ2009 እና በ2010 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የኣማርኛ ቋንቋ ፈተና ዉጤት**

| ዓ.ም | የትምህርት ቤቱ ስም | የተፈታኝ ተማሪ ብዛት | | የሀገር አቀፍ ፈተና ዉጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | A | B | C | D | F |
| 2009 | አከዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወንድ | 37 | - | 5 | 18 | 8 | 6 |
| | | ሴት | 18 | - | 3 | 9 | 3 | 3 |
| | | ድምር | 55 | - | 8 | 27 | 11 | 9 |
| 2010 | አከዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወንድ | 39 | 1 | 10 | 18 | 6 | 4 |
| | | ሴት | 13 | - | 3 | 5 | 2 | 3 |
| | | ድምር | 52 | 1 | 13 | 23 | 8 | 7 |

በኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከአጠቃላይ 554 የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ብሄራዊ ፈተና ተፈታኝ ተማሪዎች መካከል አንድም ተማሪ A ካለማምጠቱም ባሻገር፣ 364ቱ ''D" እና ከዚያ በታች ዉጤት አግኝተዋል፡፡ በ2009 ዓ.ም በመኮድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከአጠቃላይ 421 ተፈታኝ ተማሪዎች 242ቱ ''D" እና ከዚያ በታች ዉጤት አስመዝግበዋል፡፡ይህ ውጤት የሚያመለክተን የፌደራል መንግስቱ እና የክልሉ የስራ ቋንቋ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከውጤት አንጻር ሲመዘን ከግማሽ በላይ ውጤት አልባ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች ሊኖሩ ቢችሉም፤ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እቅዱ በአግባቡ አለመተግበሩ ሰፊውን ድርሻ ሊይዝ ይችላል የሚል ግምት በአጥኚዋ በኩል ተወስዷል፡፡

ስለዚህ በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርቱን ሳይማሩ የሚዘገይበት ጊዜ በርካታ በመሆኑ ለደረጃ የሚታቀደው የትምህርት ጊዜ በአግባቡ ሳይሸፈን ቢቀርም፤ ተማሪዎቹ በዓመቱ ወይም በመንፈቀ ትምህርቱ መጨረሻ ለፈተና የሚቀመጡ በመሆኑ የሥራዉን አፈጻጸም በተገቢው ሁኔታ ማለቅና የዕቅዱን አተገባበር አኳኋን መከናወኑን ከሙያ አንጻር መገምገም ስላስፈለገ ይህን ጥናት ማከናወን ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ የጥናቱ መከወን ምክንያት ሆኖ በመገኘቱ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ለምሳሌ እንደ (Richard & Lockhart, 1994) የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድን ሲያዘጋጁ በሚያደርጓቸው ድርጊቶች ላይ የተደረገ ጥናት ውጤት እንደሚገለጸው ብዙ መምህራን የትምህርት ዕቅድን ሲፅፉ ከመነሻው

ዕቅድ ያፈነግጣሉ ይህም በውጤታቸው ላይ ተጽእና ሊያሳድር ይችላል። በሌላም መልኩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን በተለይ ብዙ ልምድ ያላቸው መምህራን በቅድም ተከተላዊ ተግባራት መሰረት ትምህርታዊ ዕቅዳቸውን ያዘጋጃሉ፤በአግባቡም ይጠቀሙበታል በመሆኑም ውጤታማ ይሆናሉ በማለት ይገልጻሉ።

ይህ ሁኔታ  በእኛ አገር በተደረጉ ጥናቶችም ለምሳሌ በማስተርስ ደረጃ የተጠኑት ዮሴፍ (1989) ፤ነብዩ (2008) መስታወት (2010) የተገኘው ውጤት ተቀራራቢነት ይታይበታል። የጥናቶቹ ውጤት እንደሚያሳየው እቅዶች በአግባቡ ተዘጋጅተው አይተገበሩም፤ ከመጽሀፉ እና ከመርሀ ትምህርቱ ይዘቶች ጋር አይሄዱም፤ ሳይንሳዊ የእቅድ አዘገጃጀት ንድፈ ሀሳብ የተከተሉ አይደሉም የሚሉት ይገኙበቸዋል። በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ኮተቤ በሙሉቀን (1992) ጅማ የኒቨርሲቲ ኮኮቤ (2002) በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር እቅድን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች የጥናት ውጤትም እንደሚያሳየው እቅዶቹ በተገቢው ሁኔታ እንደማይዘጋጁ እና እንደማይተገበሩ ነው። የቋንቋ ትምህርትን በአግባቡ አቅዶ ተግባር ላይ ያለማዋል በተማሪዎች ውጤት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳደሩ ሁኔታዎች አንዱና ግንባር ቀደም ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው።

ስለዚህ በጋምቤላ ክልል በሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እቅድ ዝግጅት እና አተገባበር ምን እንደሚመስል ለማወቅ እና  ከእቅድ ዝግጅት እና አተገባበር ጋር የተያያዙ ችግሮች ካሉ የመፍትሄ ሀሳብ በጥናት አስደግፎ ለማቅረብ ከመነሳሳት በመነጨ ፍላጎት ይህን ጥናት ማካሄድ አስፈልጓል። በጥናቱ ይመለሳሉ ተብለዉ የሚገመቱ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸዉ።

1. በጋምቤላ ክልል፣ ጋምቤላ ከተማ፣ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፤ ዕቅዶች የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ስርኣት በሚፈቅደው መልኩ ባግባቡ ተዘጋጅተዉ ይተገበራሉ?
2. በጋምቤላ ክልል፣ ጋምቤላ ከተማ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እለታዊ ዕቅዶች በየደረጃዉ ካለው ጋር (የዓመት እና የምዕራፍ) ተጣጥመዉ ይሄዳሉ?

3. በጋምቤላ ክልል፣ጋምቤላ ከተማ፣ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዕቅዶችን ለማዘጋጀት ወይም ለመተግበር እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸዉ?

4. በጋምቤላ ክልል፣ ጋምቤላ ከተማ፣ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዕለታዊ ዕቅዱ ውስጥ የሚገለጸው የዓላማ እና የይዘት አቀራረጽ ከብሉምስ ታክሶኖሚ አንጻር የሚሄድ ነው?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በተመረጡት ስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። በንዑስነት ደግሞ ከዚህ በታች ያሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይይዛል።

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. በጋምቤላ ክልል፣ ጋምቤላ ከተማ፣ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ የመምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች ዕቅዶች፣ የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ስርኣት በሚፈቅደው መልኩ ባግባቡ ተዘጋጅተዉ መተግበራቸውን መፈተሽ፤
2. በጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተማ ጋመቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችእለታዊ ዕቅዶች በየደረጃዉ ካለው ጋር (የዓመት እና የምዕራፍ) ተጣጥመዉ መመርመር፤
3. በጋምቤላ ክልል፣ ጋምቤላ ከተማ፣ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዕለታዊ ዕቅዱ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን ለይቶ መዘርዘር እና

4. በጋምቤላ ክልል፣ ጋምቤላ ከተማ፣ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዕለታዊ ዕቅዱ ውስጥ የዓላማ እና የይዘት አቀራረጽ ከብሉምስ ታክሶኖሚ አንጻር መሆኑን መፈተሽ ናቸው።

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

የአማርኛ ቋንቋ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር የዓመቱንም ሆነ የዕለታዊ የትምህርት ወሰን በማመልከት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም። ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል።

1. የጥናቱን ውጤት ለጋምቤላ ትምህርት ቢሮ በማድረስ አጥኚዋም ሆኑ የትናቱ ተሳታፊዎች እነዲሁም ሌሎች መምህራን፤ ይህን ጥናት መነሻ በማድረግ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ጊዜ የሚታዩትን ስህተቶች በመለየት ለወደ ፊት የተሻለ ዕቅድ ለማዘጋጀት ይጠቅማል። ለትምህርቱ ተተግባሪነት ከሚኖረው ጠቀሜታ አንጻር ታይቶ የሚመለከተው አካል (ትምህርት ቢሮው ወይም የወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤት) ችግሩን ከግንዛቤ በማስገባት የስራ ላይ ስልጠና ለመስጠት መነሻ በመሆን ሊረዳ ይችላል፡
2. በጥናቱ ለታቀፉ ትምህርት ቤቶች መምህራን ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ከዚህ በፊት ከነበረው አዘገጃጀትና አተገባበር በተሻለ መልክ እንዲዘጋጁ መነሳሳትን ሊፈጥር እና በኣግባቡ እቅደው በመተግበር የተማሪዎቻቸውን ውጤት ለማሻሳል ሊረዳ ይችላል፤
3. ከዚህ ርእስ ጋር ተዛማጅነት ያለውን ጥናት ለሚያጠኑ ሌሎች አጥኚዎች እንደመነሻ በመሆን በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል ይችላል።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ አካባቢ በጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተማ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ከሚገኙ ዘጠኝ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል አምስቱ (አኮዶ፣ መኮድ፣ ባዝየል፣ ኢሊያ እና  ኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ብቻ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል። ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትን እና አተገባበርን መፈተሽ ላይ ያተኮረ ነዉ::  በመሆኑም ይህ

ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ በማተኮር ይዘት በተነሳው አላማ ወይም በመሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነዉ። ስለሆነም አጥኚዋ ከቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ስፋት አንፃር ከላይ በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ብቻ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ ተወስኖ ጥናቱ ተካሀዷል።

### 1.6 የቁልፍ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ

በዚህ ንዑስ ክፍል በጥናቱ ውስጥ ተደጋግመው በስራ ላይ የዋሉት ቁልፍ ቃላትና ሐረጋት በጥናቱ ውስጥ ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንጻር ትርጉማቸው እንደሚከተለው ነው።

- አዕምሮአዊ ምድብ (Cogntive domain) ፣በዚህ ጥናት ውስጥ አዕምሮአዊ ምድብ የሚባለው የእውቀት፣ የማስታወስ እና የማሰብ ችሎታን በማዳበር ላይ የሚያተኩር ነው።

- ስሜታዊ ምድብ (Affective domain) ፣በዚህ ጥናት ውስጥ ስሜታዊ ምድብ የሚባለው ነገሮችን በስሜታዊነት የምናይበት ሁኔታ ሲሆን ስሜትን፣ ዝንባሌን፣ ፍላጎትን… ያጠቃልላል።

- ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain) ፣በዚህ ጥናት ውስጥ ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ የሚባለው የተማሪዎችን ክሂሎች ማዳበር ላይ የሚያተኩር ነው።

- ዕለታዊ የትምህርት እቅድ (daily lesson plan) ፣ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ማለት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ወይም በአንድ ቀን ውስጥ ምን መማር እንዳለባቸው የሚያሳይ የአጭር ጊዜ ዕቅድ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት. የድርሳናት ክለሳ

## 2.1 ፅንሰ ሀሳባዊ /ቃለ ነቢባዊ መሠረቶች

### 2.1.1 የእቅድ ምንነት

አንድን ጉዳይ ለመጀመር እና ለመከወን ሲታሰብ ስለጉዳዩ በጥልቀት ማሰላሰል እና ትንታኔ መስጠት፤ ስራውን በአግባቡ ለመከወን ይረዳ ዘንድ በተገቢው ሁኔታ ማቀድ፤ ስራውን መሞከር በትእግስት ደግሞ ደጋግሞ ማድረግ፤ የሚከወነውን ነገር እያሸሻሉ ድርጊትን ማስቀጠል ለስኬት ሊያደርስ የሚችል አካሄድ እንደሆነ የሙያው ባለቤቶች መምህራንም ሆኑ የስራ አመራር ባለሙያዎች የሚስማሙበት እውነታ ነው። አንድ ስራ ከውጥኑ ተነስቶ እስከ መጨረሻው ግብ ለመድረስ  እቅድ ወሳኙን ሚና ይጫወታል። ይህን አስመልክቶ ግዋንግ ቾል ቻንግ/ Gwang chol chang (2006) ሲገልጹ፤ እቅድ ማለት አንድን ሥራ ለማከናወን ምን እንደምንሰራ፣ ለምን  እንደምንሰራ እና እንዴት እንደምንሰራ ዉሳኔ የምንሰጥበት ሲሆን በብዙሃን የስምምነት ዉጤት መሰረት የሚገነባ የሥራ ሂደት ሆኖ ሌሎች ባለ ድርሻ አካላትም ለአፈጻጸሙ የጋራ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት የሥራ ክንዉን ንድፍ ነዉ ይላሉ። እቅድ እንደ የሥራ መሰሪያነቱ ፖሊሲንና የወጪ  አዉታሮችን ብቻ የሚይዝ ሳይሆን የዓላማ ቅደም ተከተልን፣ ቁለፍ ተግባራትን፣ ለአፈጻጸም ህጋዊ ቅንጅትን፣ ክትትልንና ግምገማንም ያካትታል።

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምረዳው፣ እቅድ የምንሰራው ስራ ምን እንደሀነ፣ ከየት ተነስቶ የት እነደሚደርስ ወይም ምን ውጤት ልናስገኝበት እንደምንችል፣ ስራውን እንዴት እንደምንሰራው የምናውቅበት የስራችን ማዋቀሪያ መሰረታዊ ንድፍ እንደሆነ ነው።

### 2.1.2 የትምህርት እቅድ ምንነት

የትምህርት ዕቅድ የትምህርቱን አላማ አመራረጥ፣ የተለያዩ ተግባራት ከአላማ ጋር ተያያዥነታቸውን፣ የተግባራቱን ቅደም ተከተል፣ የሚያስፈልገውን መርጃ መሰሪያ፣ እያንዳንዱ ተግባር የሚፈጅበትን ጊዜ እና ተማሪዎችን እንዴት በቡድን እንደሚያደራጅ እና እንዴት እንደሚገመግም መረጃ የሚሰጥ ቅጽ ነው።በማለት (Jenson, 2001) ገልጸዋል።

የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ተማሪዎችን ለማስተማር የታቀደውን ትምህርት ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል በሳይንሳዊ ዘዴ የተዘጋጀ የስራ ማገዣ መሳሪያ ነው Elizzabeth (1982፡12)። ስለ ትምህርት ዕቅድ ጠቀሜታ ሲያስረዱ ‹‹አጠቃላይ የትምህርት አካሄድ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ዕቅድ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ይኖረዋል።›› ከዚህ

በተጓዳኝ (Dorothy 1985፡48) ስለዚህ ዕቅድ ሲናገሩ <<የትምህርት ዕቅድ ስኬታማ ለሆነ የትምህርት ሂደት እንደመሳሪያ ወይም መርጃ የሚያገለግል ነው። ይህ ደግሞ ለጥሩ የማስተማር ሂደት አስፈላጊና እንደ መርህም ይጠቅማል>> ይላሉ። ይህ ማለት የመማር ማስተማርን ሂደት ያለ ዕቅድ ስኬታማ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ያስገነዝበናል።

በመሆኑም የትምህርትን ሂደት ግብ ለማድረስ ዕቅድ ወሳኝና ዋነኛ የመምህሩ ተግባር መሆኑን ማወቅና መተግበር ተገቢ ነው። የትምህርት ዕቅድ ከጀማሪ መምህራን ጀምሮ እስከ ልምድ ያላቸው መምህራን ድረስ ሁሉም ይገለገሉበታል። እንደዚሁም የትምህርት ዕቅድ ከታችኛው የትምህርት እርከን አንስቶ እስከ ከፍተኛ የትምህርት እርከን ድረስ የሚሰራበት ወሳኝ መሣሪያ መሆኑም መዘንጋት የለበትም (Fink, DL 2005)። የትምህርት ዕቅድን ሲገልፁ የትምህርት ዕቅድ የተቀናጀ ተለጣጣቂነት ያለው የትምህርት ዕቅድ ለታቀደው ግብ /አላማ/ በአግባቡ ለማከናወን ያስችላል ይላሉ።

### 2.1.3 የትምህርት እቅድ አስፈላጊነት

የትምህርት ዕቅድ የዉጤታማ መምህር የልብ ትርታ ነዉ። የትምህርት ዕቅድ ለሁለተኛ ቋንቋ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር፣ ቋንቋን ለማስተማር የመምህሩና የተማሪዉ ዕዉቀት ለማቆራኘት፣ ስርዓተ ትምህርቱንና የማስተማር አዉዱን ለማገናኘት መልካም አጋጣሚ ይፈጥርልናል። የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ብዙ ጥቅሞች አሉት። Spratt, et al (2005) በዝርዝር ሲገልጹ፤

- መምህራን ስለሚያስተምሩት የትምህርት ዓላማ፣ ይህ ዓላማ ግቡን እንዲመታ የሚያስችሉ ድርጊቶችን፣ የእነዚህን ዓላማዎች ተከታታይነት፣ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ፣እያንዳንዱ ድርጊት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ እና ተማሪዎችን በቡድን እንዴት እንደሚመድቧቸዉ አስበዉ እንዲመርጡ አጋጣሚዉን ይፈጥርላቸዋል።
- መምህራን አንድን የዓላማ ድርጊት ከሚቀጥለዉ የዓላማ ድርጊት ለማቆራኘት፣ አሁን ያለዉ የትምህርት ዕቅድ ካለፈዉ ዕቅድ ወይም ለወደፊት ከሚታቀደዉ ዕቅድ የሚኖራቸዉ ግንኙነት እና በመማር ማስተማር እንቅስቃሴና በግምገማዉ ሂደት ላይ ያላቸዉን ተጣጥሞሽ እንዲያዩበት ይረዳቸዋል። ምክንያቱም መምህሩ እነዚህን ነገሮች ግምት ዉስጥ ስለሚያስገባ የትምህርት ዕቅዱ ለእነዚህ ድርጊቶች ትርጉም ያለዉ ይሆናል፡፤

- የትምህርት ዕቅዱ ሂደት ለመምህራኑ ከሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት ጋር ያላቸዉን የእዉቀት ተመጣጣኝነት ራሳቸዉን ለመገምገም አጋጣሚዉን ይፈጥርላቸዋል። ለምሳሌ መምህሩ ዉስብስብ የሆነና ህጉን እርግጠኛ ሆኖ የማያዉቀዉ የቋንቋ ስዋስዉ ቢገጥመዉ በትምህርት ዕቅዱ ሂደት ላይ ግንዛቤ ለማግኘት አስፈላጊዉን ቅደም ተከተል መዉሰድ አለበት።
- የትምህርት ዕቅድ ለመምህራን በራስ የመተማመን ባህልን ያዳብራል፡ ፡መምህሩ መቼ፣ እንዴትና ምን ለመስራት እንደፈለገ ግልጽ ይሆንለታል።
- መምህሩ ከመጽሐፉ ጋር በተያያዘ የክፍለ ጊዜዉን ሰዓት አያባክንም እናም ለቀጣዩ ምን እንደሚሰራ የማሰብ ዕድሉን ይፈጥርለታል።
- አንድ መምህር የሌላዉን መምህር ክፍለ ጊዜ ሳይሻማ የራሱን ክፍለ ጊዜ በትክክል እንዲጠቀም ይረደዋል፡
- የትምህርት ዕቅዶች በትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምራን ፋይል ተደርገዉ ከተቀመጡ፤ የሳምንቱን የመማር ማስተማር ሂደት ለመገምገም ለሚመጡት የትምህርት ቤቱ ሱፐርቫይዘርና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች በመረጃነት ያገለግላሉ።

በመጨረሻም የትምህርት ዕቅድ ለመምህሩ ሞያዊ ብቃት በመረጃነት የገለግላል። መምህራን አንዳንድ ጊዜ የትምህርት ዕቅዶቻቸዉን ከሌላ የትምህርት ቁሳቁስ ጋር በማዋሃድ የሰነዶች ማህደር (portfolio) በማዘጋጀት የዓመቱ አቋማቸዉን ይገመግሙበታል። በተጨማሪም መምህራን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሥራ ፍለጋ በሚሄዱበት ወይም በሚወዳደሩበት ጊዜ ከነበሩበት ተቋም ያካበቱትን ልምድ መስፈርቱን ለማለፍ እንደግብአት ይጠቅማቸዋል (Wei, Meile.2006) ።

ከላይ በተለያዩ ምሁራን እንደተገለጸው፤ የትምህርት ዕቅድ ለዉጤታማ መምህራን ለስራቸው ስኬታማነት አይነተኛው እና ቁልፍ ጉዳይ ነዉ። በተጨማሪም በስርአቱ የተዘጋጀ እና የተተገበረ የትምህርት ዕቅድ ለሁለተኛ ቋንቋን የመረዳት ችሎታ ለማዳበር፣ ቋንቋን ለማስተማር የመምህሩና የተማሪዉን የስራ ውጤት በዕዉቀት ለማቆራኘት፣ ስርዓተ ትምህርቱንና የማስተማር አዉዱን ለማገናኘት መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ዋና ተግባር ነው። በተጨማሪም የትምህርት ስራውን ለሚያከናውኑት መምህራን እና የትምህርት ባለሙያዎች በጠቅላላ ስራውን በአግባቡ ለማከናወን

እና ለመምራት የሚያስችላቸው ሁነኛ መፍትሄ ነው። በሌላ መልኩም በአግባቡ የተዘጋጀ እና የተተገበረ የትምህርት ዕቅድ መምህራን የስራቸውን ክንውን እና አፈጻጸም ሁኔታ ለመገምገም እና ስራቸውን በወጉ ለማስቀጠል የሚረዳቸው መንገድ ነው።

### 2.1.4 የትምህርት ዕቅድ ሞዴሎች (Models of lesson plan)

ትምህርታዊ እቅድ ብዙ አይነት አቀራረቦች አሉት። በብዛት የተለመደው የሞዴል አይነት (Tyler's 1949) rational- linear framework ነው። ይህ ሞዴል ተከታታይነታቸውን የጠበቁ አራት ደረጃዎች አሉት።

1. ዝርዝር አላማዎች ማካተት ( specific objectives )
2. ለማስተማሪያ የሚሆኑ ተግባራትን መምረጥ (select learning activities )
3. የማስተማሪያ ተግባራትን በቅደም ተከተል ማደራጀት (Organize learning activities) እና
4. የግምገማ ስልቶችን መወሰን (specifiy methods of evaluation) ናቸው።

እንደ ቦርኮ እና ኔልስ (Borko and Niles, 1987) አገላለፅ መምህራን የተሰጡት ደረጃ ተከታታይነቱን እና ቀጥተኛ ሂደቱን ብዙ ጊዜ እንደማይጠቀሙ ማረጋገጫ ባይኖርም አሁንም የTyler ሞዴል በብዛት እያገለገለ ነው ። ለምሳሌ Taylor (1970) መምህራን የትምህርት ዕቅዳቸውን ሲያዘጋጁ በተግባር የሚያደርጓቸው ነገሮችን ሲያጠና በብዛት ትኩረት የሚሰጡት በተማሪዎቻቸው ፍላጎት ላይ ነው የሚል ውጤት አግኝቷል። በጣም አስፈላጊውን ነገር የጥናቱ ውጤት የመምህራን ትምህርት ፕሮግራም ትምህርታዊ ዕቅድን ለማዘጋጀት በደንብ እንደማይዘጋጅበት ያመለክታል። በዚህ ውጤት ላይ ተመስርቶ (Yinger, 1980) እቅድ በደረጃ የሚካሄድበትን አዲስ አማራጭ ሞዴል አዘጋጀ።

- የመጀመሪያ ደረጃ የሚይዘው የችግሮች ሀሳብ ( Problem conception ) ነዉ። ይህ ማለት ዕቅድ የሚጀምረው ተያያዥነት ካላቸው የመምህሩ ግብ፣ እውቀት እና ልምድ የምርምር ውህዶች (cycle) ውስጥ ነው።

- የሁለተኛው ደረጃ የተፈጠረውን ችግር እና የተገኘውን መፍትሔ ( problem formulated and asolution achieved) የሚያሳይ ነው።
- የሦስተኛ ደረጃ የዕቅዱን አተገባበር ከግምገማ ጋር የሚያያይዝ ( Implementing the plan along with its evaluation ) ነው። yinger ይህንን ሂደት የሚያየዉ እንደ የዕለት ተዕለት ትግበራ ነው። ይህም የእያንዳንዱን ዕቅድ ክስተት የሚወስኑት ባለፉትና ወደ ፊት በሚመጡት ክስተቶች ላይ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመተግበር ላይ ያሉ የእለታዊ ማስተማር እቅዶች ሊያጠቃልሏቸው ወይም ሊይዟቸው የሚገቡ የእለታዊ እቅድ አተገባበር ዝርዝር ጉዳዮች የሚከተለውን ይመስላሉ።

1. መግቢያ (Introduction)፤ቀደም ሲል የተማሩትን በማስታወስ የእለቱን ትምህርት ዋና ይዘት በማስተዋወቅ ለእለቱ ትምህርት እንዲዘጋጁ የሚያደርጉ ነጥቦችን መጥቀስ
2. ማነቃቂያ (Warmup)፤ የእለቱን ተምህርት በቀና እና በተሳካ መልኩ ለማከናወን ይረዳ ዘንድ ትምህርቱን በምን መልኩ ቢማሩ እንደሚመቻቸው የተዋዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይዘቶችን ጠቅለል አድርጎ በማቅረብ /በመግለጽ/ ለእለቱ ትምህርት አዘጋጅተው ንቁ የሚያደረጉ ነጥቦችን ማስቀመጥ
3. አቅራቦት (Presentation)፤ ይዘቶችን ማስቀመጥ፣ ተማሪዎች ከይዘቶች ጋር በተያያዘ መልኩ የሚከውኗቸውን ተግባራት፣ የክፍሉን አደረጃጀት፣ የመምህሩን የክፍል አመራር ሁኔታ በዝርዝር መግለጽ፤ ተማሪዎች በቁጥጥር እና በነጻነት ሊያከናውኗቸው የሚችለትን ተግባራት በግልጽ ማስቀመጥ፤
4. ምጋቤ ምላሽ (Feedback)፤ በእያንዳንዱ ተናጥላዊ ተግባር መምህሩም ሆነ ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው የእለቱን ትምህርት ለማገዝ መስጠት የሚችሉትን ምጋቤ ምላሽ መጠቆም
5. ማጠቃለያ (Concluding Remarks)፤ በእለቱ ትምህርት ውስጥ የትምርቱን አላማ ለማሳካት ይጠቅማሉ የሚባሉትን የይዘት እና የእለቱ ትምህርት ክንውን ፍሬ ጉዳዮችን መርጦ ማጠቃለል። የእለቱን ትምህርት ክንውን ሊያግዙ የሚችሉ እና ከዋና ዋና ይዘቶች

ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥያቄዎች መጠየቂያ መንገድ መጠቆም። የእለቱን ትምህርት ክንውን የሚያግዙ ተጨማሪ አጋዥ የትምህርት መሳሪያዎችን መጠቆም።

እንደ (Richard & Lockhart, 1994) የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድን ሲያዘጋጁ በሚያደርጓቸው ድርጊቶች ላይ የተደረገ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው ብዙ መምህራን የትምህርት ዕቅድን ሲፅፉ ከመነሻው ዕቅድ ያፈነግጣሉ። ከዚህ ባሻገር የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን በተለይ ብዙ ልምድ ያላቸው መምህራን በቅድም ተከተላዊ ተግባራት መሰረት ትምህርታዊ ዕቅዳቸውን ያዘጋጃሉ። በአግባቡም የታለመለትን ግብ ለማስገኘት ይጠቀሙበታል።

ቀደም ሲል የነበረውም ሆነ አሁን እየተተገበሩ ያሉ የትምህርት እቅድ ሞዴሎች ማስመዝገብ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ ሊያስገኙ የሚችሉ አላማዎች፣ እነዚያን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ተግባራትን፤ እነዚህን ተግባራት በወጉ ማደረሻ አቀራረቦችን፣ ተደጋጋሚ ልምምዶችን፣ አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ግምገማዎች ከምጋቤ ምላሻቸው ጋር እና ማጠቃለያዎችን ሊይዙ እንደሚገባቸው እንገነዘባለን። እነዚህን በትክክል መቀረጽ እና መተግበር ካልቻሉ የቋንቋ ትምህርት አላማ ከታለመለት ግብ ለመድረስ ይቸገራል። ማለትም ተማሪዎችን በአግባቡ አስተምሮ የታለመለትን ግብ (በቋንቋው ብቁ ተጠቃሚ ማድድግ እና በፈተና ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ) የሚችሉ ተማሪዎችን መፍጠር አይቻልም።

### 2.1.5 የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት

የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ለጥሩ የማስተማር ሂደት ድጋፍ መሆን የሚችሉ የትምህርት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መሪ ሀሳቦችን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ይህ በተለይ የዕለት የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ውስጥ በዋናነት የሚነሳ ጉዳይ ነው። አንድ የቋንቋ መምህር የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ከማዘጋጀቱ በፊት ስለተማሪው፣ ስለመማሪያ ክፍሉ፣ ስለመማሪያ መጽሐፍ ይዘትና አጠቃላይ በዕቅዱ ላይ መስፈር ስለሚገባቸው ዝርዝር ጉዳዮች ጠለቅ ያለ ዕውቀት ቢኖረው የተሻለ ነው። ምክንያቱም መምህሩ አስፈላጊ የሆኑትን አብይ ነጥቦች በጥልቀት ከተረዳ በመምህሩ ለሚዘጋጀው የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ እገዛ ሊያደርግለት ይችላል።

በተጨማሪም ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ለምን እና ምን እንዲሁም በምን ዘዴ እንደሚያስተምር አስቀድሞ እንዲያስብ ሊያደርጉት ይችላሉ። የዕቅድን አዘገጃጀት በተመለከተ (Elizzabeth 1982፡18) የሚከተሉትን መርህ ሐሳቦች አስቀምጠዋል። ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት ሊካተት የሚገባው ቀን፣ ክፍል፣ የተማሪዎች እድሜ፣ የተማሪው ብዛት፣ ክፍለ ጊዜ፣ ጠቅላላ አላማና ይህንን ርእስ ለምን እንደሚያስተምር፣ የሚያስተምረው የትምህርቱ ይዘት ምን እንደሆነ፣ የታቀደው የትምህርት አወቃቀር እና የጊዜ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል፣ ውስን ወይም የመማር ማስተማር ዓላማ ከሚያስተምረው ትምህርት ተማሪው ምን እንደሚማር ማወቅ ተገቢ ነው ይላሉ። እንደምሁሩ አገላለጽ የቋንቋ መምህራን የትምህርት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ከላይ የተጠቀሱትን መሪ ሀሳቦች በትምህርት ዕቅዳቸው ውስጥ ማካተት እንደሚገባቸው ፍንጭ ይሰጣሉ። በተጨማሪም የትምህርት ዕቅድን በምናዘጋጅበት ጊዜ ከዚህ በታች የቀረቡትን ሀሳቦች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል።

### 2.1.5.1 ዕቅዱን ማዳበር

**ሀ**. አንድ ውጤታማ የትምህርት እቅድ የሚጀምረው አስፈላጊ እና ግልፅ የሆነ አላማን በመፃፍ ነው።

አላማ ማለት የአንድን ትምህርት ውጤት ገላጭ ነው፡ ፡አላማዎች የሚገልፁበት ተማሪዎችን እንዲደርሱልን የምንፈልገው መድረሻ እንጂ ጉዞውን አይደለም። በዕለታዊ የትምህርት እቅድ ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ ግልፅ እና በደንብ የተፃፉ አላማዎች ናቸው። እነኚህ አላማዎች ተማሪዎች ሊማሩ የሚገባቸውን በግልፅ ለመዘርዘር፣ አስፈላጊ ተግባራቶችን ለማገዝ እና አጠቃላይ የትምህርቱ ትኩረትና አቅጣጫን ለማሳየት ያገለግላሉ።

በተጨማሪም መምህራን ተማሪዎቻቸው በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተማሩትን ለመገምገም መንገድ ይሰጣቸዋል። በግልፅ የተፃፉ አላማዎች ተማሪዎች በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ወይም ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅ እንዲያውቁ ያገለግላቸዋል። Shrum and Glisan, 1994 ከተማሪዎች ባህሪይ ለመለየት የሚከተሉትን የተግባር ግሶች መጠቀም ይመከራል። እነዚህም ከBloom taxonomy of thinking process ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ተግባራዊ ግሶችን ሊያጠቃልል ይችላል።

ተግባራዊ ግሶች ለምሳሌ መለየት፣ ማቅረብ፣ መግለፅ፣ ማብራራት፣ ማሳየት፣ መዘርዘር፣ ማነፃፀር እና ማከራከር ለመምህሩ የትምህርቱን እቅድ በእነዚህ ዙሪያ ለመንደፍ ግልፅ እና ቀላል ነው። እነኚህን ተግባራዊ ግሶች መጠቀም እንዲሁም ለተማሪው በእያንዳንዱ ትምህርት ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅ በቀላሉ ለመረዳት ይረዳቸዋል።

**ለ** .የትምህርቱ ተግባራት

የትምህርቱ ዓላማ ከተፃፈ በኋላ፣ መምህራን እነኚህን አላማዎች በተሳካ ሁኔታ በውጤታማ መልኩ መሳካታቸውን ለማረጋገጥ ተግባራትን እና ሂደቶችን መወሰን አለባቸው። በዚህ ደረጃ ማቀድ ማለት በተግባራቶቹ አስፈላጊነት እና መዋቅሮች የምናስብበት መንገድ ነው። ይህ ደረጃ የትምህርት እቅድን የምናስይዝበት ነው።

### 2.1.5.2 **ዕቅዱን መተግበር**

ትምህርታዊ ዕቅድን መተግበር በጣም አስፈላጊ እና ከባድ የዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዑደት ክፍል ነው። በዚህ ክፍል የትምህርት ዕቅዱ በራሱ በክፍሉ ነባራዊ እውነታ ምክንያት ወደ ዳራቸው ሊያፈገፍግ ይችላል።

ብዙ ልምድ ያላቸው መምህራን እንደሚያውቁት ባልታቀዱ ድርጊቶች ምክንያት አቅጣጫቸው በቀላሉ ሊቀየር ይችላል። ቢሆንም መምህራን የመጀመሪያ ዕቅድ በአዕምሮ ብቃትን በመመርመር መሆን ማስታወስ ይኖርባቸዋል። ይህ ግን ለጀማሪ መምህራን ከባድ ነው። ምክንያቱም ነገሮች በመጥፎ አቅጣጫ መሄዳቸውን ለማወቅ አስፈላጊ ልምድ ላይኖራቸው ስለሚችል ነው። በዚህ አይነት ሁኔታ ምትክ የሚሆን ጉድለትን የመሙያ ዕቅድ አዘገጃጀት በቂ እውቀት ላይኖራቸው ይችላል።

መምህራን እቅዳቸውን በሚተገብሩበት ወቅት ሁለት ጠቃሚ ጉዳዮችን ለመቆጣጠር መሞከር አለባቸው። እነሱም፡- የአቀራረብ አይነቶች እና የአቀራረብ ፍጥነት ናቸው። በትምህርት አሰጣጥ ውስጥ ያሉ የአቀራረብ አይነቶች እና የተግባራት ምርጫ ክፍሉን ተወዳጅ እና ህይወት ያለው ሊያደርጉት ይችላሉ። አቀራረብን ለመቀያየር መምህራን የተግባራትን አካሄድ ከፈጣን እንቅስቃሴ ወደ ዝግ ያለ እንቅስቃሴ በየ ጊዜው መቀያየር አለባቸው። መምህራኖቹ በተጨማሪም የግል

ስራ፣ የቡድን ስራ፣ የጥንድ ስራ ወይም የሙሉ ክፍል ተሳትፎን በመስጠት የክፍሉን አደረጃጀት መቀየር ይችላሉ።

የአቀራረብ ፍጥነት አካሄድ ከፍጥነት ጋር የተያያዘ ነው ፤ ልክ እንደ ትምህርት ጊዜ መምህራን የፍጥነት ስሜት እንዲያዳብሩ ካስፈለገ (Brown, 1994) የሚከተሉትን መመሪያዎች እንድንጠቀም ይመክራል።

ሀ. ተግባራት በጣም ረጃጅም በጣም አጭርም መሆን የለባቸውም።

ለ. ተግባራትን ለመስጠት የተለያዩ ስልቶች በአንድ ላይ ተያይዘው መሄድ አለባቸው።

ሐ. በእያንዳንዱ ተግባር መሀል ግልፅ ሽግግር መኖር አለበት።

መምህራን ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለተማሪው ጥቅም መስራታቸውን ካስታወሱ ለተለያዩ ተግባራት ትምህርታዊ እቅድ ላይ ብቻ ስላሉ እነሱን ብቻ መከተል ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል።

### 2.1.5.3 ዕቅዱን መገምገም

የዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ የመጨረሻው ክፍል የሚከሰተው ትምህርቱ ካለቀ በኋላ እና መምህሩ የትምህርቱን ውጤታማነት እና ውድቀት መገምገም ሲገባው ነው። በተጨማሪም ብራውን (Brown, 1994) እንደሚያስታውሰን የእቅድ ግምገማ በትምህርቱ ሂደት ውስጥም ሊካሄድ ይችላል። ትምህርቱን ካስተማርን በኃላ፣ ጥሩ ይሁን አይሁን እና ለምን ብሎ መጠየቅ እና ማሰብም ተገቢ ነው። ይሁን እና ስኬትም ሆነ ውደቀትም" ሁለቱም አንፃራዊ ቃላት ሲሆኑ ትርጓሜ ያቸውም በእያንዳንዱ መምህር እና ተማሪ እይታ ልዩነት ሊኖረው ይችላል። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ባሉ የመገምገሚያ ክፍሎች በስተቀር መምህሩ የተማሪውን ውጤታማነት በተለይ በቋንቋ ትምህርት ለማወቅ ይቸገራል። እቅዱን ወይም ያስተማረውን ውጤት ካልገመገመ ለሚቀጥለው ትምህርት ምን አይነት ማስተካከያ ማድረግ እንዳለበት መፈተሽ አይችልም።

ከዚህ የምንረዳው የቋንቋ ትምህርት ወይም ሌላ ማንኛውንም ትምህርት ዉጤታማ መሆኑን እና አለመሆኑን ለመረዳት የትምህርት እቅዳችንን አፈፃጸም በማስተመማር ሂደትም ሆነ ካስተማርን

በኋል ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መተግበሩን እና የታለመለትን ውጤት ማስገኘቱን መገምገም ይጠበቅብናል።

የማስተማር እቅድን በተገቢው መንገድ ማዘጋጀት እና መተግበር ከፍተኛው የመምህር ደረጃ የሚያሟላቸው መስፈርቶች ከሚባሉት ጉዳዮች አንዱና ዋንኛው ነው። እነዚህ እንደ ኢሮፓዊያን አቆጣጥር ከ2017 እስከ 2022 እንዲተገበሩ የተያዙት፤ ውጤታማ መልካም የሆነ የትምህረት ከባቢን ለመፍጠር የሚያስችለው እና ከፍተኛው የመምህር ደረጃ የሚያሟላቸው መስፈርቶች ተብለው የተቀመጡት የሚከተሉት ናቸው።

- ተማሪዎቹን የሚፈትን የሚያነቃቃ እና ፍላጉት የሚያጭር ግምት ማሳደር

  Set high expectations which inspire, motivate and challenge pupils

- በተማሪዎቹ የተሸለ እድገት እና ውጤት ማምጣት

  Promote good progress and outcomes by pupils

- የጥሩ የሙያ እና የስነማስተማር የስርዓተ ትምህርት እውቀትን ማሳየት/መግለጽ

Demonstrate good subject and curriculum knowledge

- በስርዓቱ የተዘጋጀ ትምህርትን ማቀድ እና በአግባቡ ማስተማር

  Plan and teach well structured lessons

- ማስተማርን ለተማሪዎቹ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት እና ፍላጎታቸውን ለማጠናከር በሚስችል መልኩ መላበስ

Adapt teaching to respond to the strengths and needs of all pupils

- ትክክለኛ እና ውጤታማ ፈተና/ምዘና መዘጋጀት

Make accurate and productive use of assessment

- ባህሪን፣ ውጤታማ እና ሰላማዊ የትምህርት አከባቢ ለመፍጠር /በአግባቡ መምራት/ መቆጣጠር

**Six models of lesson observation: an international perspective. May 2018**

እነዚህ ከፍተኛው የመምህር ደረጃ የሚያሟላቸው መስፈርቶች ተብለው የተቀመጡት ጉዳዮች በጠቅላላ የመማር ማስተማር እቅድን በተገቢው መንገድ ማዘጋጀት እና መተግበርን መሰረት

ያደረጉ እውነታዎች ናቸው። ስለዚህ ማንኛውም መምህር በተለያየ ደረጃ የሚገኙ እቅዶችን በተገቢው መንገድ ማቀድ እና መተግበር የጥሩ መምህርነት ሃላፊነት እና የዘወትር ተግባር ነው።

### 2.1.6 የቋንቋ ትምህርት እቅድ ዓይነቶች

የትምህርት ዕቅድ ዓመታዊ፣ ሣምንዊና ዕለታዊ ዕቅድ በመባል ይከፈላሉ (Farrell, 2002; Bailey, 1986:15-40) ።

#### 2.1.6.1. ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ

ዓመታዊ ዕቅድ የአንድ ኮርስ ስርዓተ ትምህርት አጠቃላይ ሀሳብን እና የምናስተምረዉ ትምህርትና ለትምህርቱ የሚፈጀዉ ሰዓትን ያሳያል። ዕቅዱ ለሚቀጥለዉ ዓመት የትምህርት ዝግጅት በዓመቱ መጨረሻ ለት/ቤቱ ርዕሳነ መምህራን የሚገባ ሲሆን ሣምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ በምናዘጋጅበት ጊዜ እንደ መመሪያ ያገለግላል። ዓመታዊ የትምህርት ዕቅዱን የሚያዘጋጅ መምህር በዝርዝር የሚያስተምረዉ ለክፍሉ ደረጃ ከተዘጋጀዉ ስርዓተ ትምህርት ጋር መጣጣሙን መገንዘብ አለበት።

#### 2.1.6.2. ሣምንታዊ የትምህርት ዕቅድ

ሣምንታዊ ዕቅድ ከዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ የሚወሰድ ሲሆን የምናስተምረዉን ትምህርት ከመጀመራችን በፊት ለአንድ ሣምንት የትምህርት ጊዜ የሚዘጋጅ ዕቅድ ነዉ። ዕቅዱ ከመምህሩ የማስተማር ጊዜ ጋር ኢኮኖሚያዊ፣ የትምህርቱን ፕሮግራም የሚያጠናክር፣ ተግባራዊና ሥራ ላይ የሚዉል መሆን አለበት። ይህ የሰምንታዊ የትምህርት ዕቅድ መግለጫ ቅፅ በብዙ ትምህርት ቤቶች ይዘጋጃል። ይህም የዕቅድ ዓይነት የየዕለቱ ትምህርት የተወሰነ አላማ መሰረት በማድረግ በሳምንት ውስጥ በሚኖሩት ክፍለ ጊዜያት ምንና እንዴት ለማከናወን እንታቀደ የሚገልፅበት ነው (Purgason, K. B. 1991)።

#### 2.1.6.3. ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ

ዕለታዊ ዕቅድ ከሣምነታዊ ዕቅድ የሚወሰድ ሲሆን መምህሩ በዕለቱ የትምህርት ክፍለ ጊዜዉ ምን እንደሚያስተምር ተዘጋጅቶ ክፍል ዉስጥ ለማስተማር የሚጠቀምበት ዕቅድ ነዉ። ዕቅዱ የስርዓተ ትምህርቱ ዓላማ ጽንሰ ሀሳብን፣ የሰዓት ክፍልፋይን፣ ሂደትንና አስፈላጊዉን የትምህርት

ቁሳቁስን፣ ከትምህርቱ ጋር የተያያዙ ሙከራዎችን፣ ጥያቄዎችንና ዉይይቶችን እንዲሁም የክፍልና የቤት ሥራዎችን መያዝ አለበት።

ከዚህ በተጨማሪም በቋንቋ ዕቅድ ውስጥ ዋናና ወይም መካተት የሚገባቸው የዕቅድ ከፍሎች የትምህርት ማቅረቢያ ዜዴዎች፣ የመምህሩና የተማረው ተግባር፣ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችና ምዘና ናቸው። ይኸውም መምህሩ በየ እለቱ ምን ማስተማር እንደ ሚገባው ዘርዝር ባለ መልኩ የሚያዘጋጀው ሲሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለተማሪ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ዕውቀት በመረጣቸው የማስተማሪያ መሣሪያ በመታገዝ በዝርዝር የሚፈለገውን እንዲገልፅ ያዘጋጁታል (Yi, Ming 2012) ።

## ዕለታዊ ዕቅድ ሲዘጋጅ መታሰብ ያለባቸዉ ነጥቦች

እንደ Richards, J. C. (1998) ገለጻ ዕለታዊ የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ዉስጥ መግባት አለባቸዉ።

1. እያንዳንዱ ተማሪ የተለያየ የትምህርት አቀባበል ፍላጎት፣ ችሎታና ባህሪ ያለዉ መሆኑን በመገንዘብ ሁሉንም ያማከለ ዕቅድ መሆን አለበት።
2. በዕለታዊ ዕቅዱ ዉስጥ የምንዘረዝራቸዉ የትምህርት ቁሳቁሶች ምክንያታዊና የምንጠቀምባቸዉ መሆን አለባቸዉ እንጂ ለስሙ ብቻ የምንዘረዝራቸዉ መሆን የለባቸዉም።
3. ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማበረታታት እንጂ ከአቅማቸዉ በላይ የሆኑ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ አለማስገደድ።
4. ከተማሪዉ መጽሐፍ በቀጥታ ተገልብጠዉ የሚጻፉ የመልመጃ ጥያቄዎችን አለመስጠት።
5. ተማሪዎች የሚሠሯቸዉ መልመጃዎችንና የቤት ሥራዎችን ለሠራዉ ተማሪ ዋጋ ያለዉ ነጥብ መስጠት። ምክንያቱም ሌሎች ተማሪዎችንም ለመስራት ስለሚያበረታታ።
6. የትምህርቱ ዋናዉ ርዕስ ምንድነዉ? የሚሰጡት መልመጃዎችን የጋራ ስሜት ካላቸዉ የመማር ማስተማሩን ስለሚያቀለዉ ተማሪዎች መምህሩን በጥሞና እንዲከታተሉ ያደርጋል።
7. የተማሪዎችን ስሜት እንዴት ወደ ትምህርቱ ማምጣት እችላለሁ? ትምህርቱ ሲጀመር ትምህርት የሚሰበስብ ዘዴ በመጠቀም የዕለቱን ትምህርት መጀመር። የተማሪዎቹ ሀሳብ

ወደ ትምህርቱ እንዲያደርጉ በማድረግ ስዕሎችን፣ ፎቶዎችን አልያም ሀሳባቸዉን ወደ ዕለቱ ትምህርት እንዲሰበስቡ ማድረግ።

8. የዕለቱ ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ምንድን ናቸዉ? መታስብ ያለበት ዋናዉ ነገር ምን ዓይነት መልመጃዎችን፣ ስዋሰዎችን፣ ቃላትን ወዘተ... ማስተማር አለብኝ የሚለዉ ይሆናል። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ቀድመዉ ከታሰቡ በክፍል ዉስጥ በምናስተምርበት ጊዜ የመደናገር ስሜት ስለማይኖር ለተማሪዎቹ ግልጽ የሆነ ትምህርት ለማስተላለፍ ያስችላል።
9. በምን ዓይነት ቅደም ተከተል ማስተማር አለብኝ? አንድ ጥቅል የሆነ የማስተማር ህግ አንድ መምህር ካለፈዉ ክፍለ ጊዜ ትምህርት ክለሳ መጀመር አለበት። ከዚያም የዕለቱ ትምህርት መግቢያ፣ ዝርዝር ገለፃ፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ መልመጃዎችን ማሰራትና ስለሰሯቸዉ መልመጃዎች ግብረ መልስ መስጠት ናቸዉ።
10. ምን ዓይነት ችግር አለብኝ? ዕቅዱ ሲታቀድ ችግሮች እንዴት መወገድ "እንዳለባቸዉ መታሰብ አለበት። ችግሮቹ ምናልባት ከመልመጃዎች ፣ከሰዓት አጠቃቀም፣ ከክፍለ ጊዜ፣ ከተማሪዎች አንጻር አልያም ከመምህሩ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህን ግምት ዉስጥ ያስገባ ዕቅድ ሲታቀድ ከነመፍትሄዉ ስለሚታቀድ ችግሩን ቀላል ያደርገዋል።

### 2.1.7 በእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር ወቅት የባለ ድርሻዎች ተገባር

የትምህርት እቅድ ሲዘጋጅም ሆነ ሲተገበር ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አሉ። ከነዚህም ውስጥ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ዋና ዋናዎች መምህሩ፣ የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ እና የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወይም ምክትል ርእሰ መምህር ናቸው።

#### 2.1.7.1 የርዕሰ መምህሩ ሚና

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከፍተኛ ድርሻ ያለዉ በመሆኑ አጠቃላይ የትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ሂደት ዉጤታማ ይሆን ዘንድ የትምህርት ዕቅዱን ተግባራዊነት የመከታተልና የማስፈጸም፣ ለትምህርት መሻሻል የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች (department heads) እና ለመምህራኑ የሞያ እገዛና ምክሮችን በመለገስ የትምህርቱ ሥራ በታለመለት ጊዜና ዕቅድ እንዲተገበር የመቆጣጠርና የመገምገም ሥራ ያከናዉናል። ስለሆነም

ርዕሰ መምህሩ በተጓደሉና ዉሳኔ በሚያስፈልጋቸዉ የእቅድ ጉዳዮች ላይ ከትምህርት ክፍሉ ተጠሪዎች ጋር በመሆን ዉሳኔ በመስጠት ዕቅዱን እንዲተገበር ተጠሪዎችን መገምገምና መከታተል አለበት (Spooner, F. 2007) ።

### 2.1.7.2 የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ሚና

የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች (department heads) የመምህራኑ የየዕለቱ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ በመሆናቸዉ ጥራት ያለዉን የመማር ማስተማር ሂደትን ለማስቀጠል ሙሉ አቅማቸዉን በመጠቀም ክፍል ዉስጥ ምልከታን ጨምሮ ለመምህራኑ በየዕለቱ የዉሎዉne ግብረ መልስ እየሰጡ መሄድ ይጠበቅባቸዋል። ተጠሪዎቹ በአሰራር የሥራ ልምዳቸዉ እና ክህሎታቸዉ ከመምህራኑ በመጠኑም ቢሆን የተሻሉ ናቸዉ ተብሎ ስለሚታሰብ በየዕለቱ የዕቅዱ ዓላማና ይዘት እየገመገሙ መምህራኑን የመደገፍ ግዴታ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ዕለታዊዉ የትምህርት ዕቅዱ እንዲተገበር የትምህርት ክፍሉ ተጠሪዎች የሚከተሉትን የሥራ ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል (Purgason, K. B. 1991) ፣

1. በመማር ማስተማር ሂደቱ ያካበቱትን ልምድ በተግባር ማሳየት አለባቸዉ።
2. በክፍል ዉስጥ እያስተማሩ ማሳየትን ጨምሮ ለመምህራኑ ሞዴል ሆነዉ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፤
3. ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር በመሆን መምህራኑ እዉቀታቸዉን ለማዳበር የእርስ በርስ የልምድ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ ማስተባበር።
4. ምክንያታዊ የሆኑ ግብረ መልሶችን በመስጠት ከትምህርት ክፍሉ መምህራን ጋር ያለፈዉን ጉድለት የማረምና ስለቀጣዮቹ ቀናት የትምህርት ዕቅድ ለዉጤታማነታቸዉ እንዴት መፈጸምና ማስፈጸም እንዳለባቸዉ መወያየት የመሳሰሉት ናቸዉ።

### 2.1.7.3 የመምህሩ ሚና

በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን ሚና በጊዜውና በወቅቱ ለተማሪዎቻቸው የሚጠበቅባቸውን ዕውቀት ማሳወቅ ነው። መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት እያንዳንዱ ተግባር በተማሪዎቻቸው ላይ ተፅእኖ አለው። መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡት ትምህርት

እንዴት በቅደም ተከተል በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳቸው ላይ ማስፈር እንዳለባቸው (Fink,Dl. 2005) ሲያስረዱ መምህራን በየዕለቱ በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡትን ትምህርት በተመለከተ ዕቅዳቸው ላይ ሲነድፉ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎችን ቢከተሉ ይመረጣል። በመጀመሪያ የዕለቱን ትምህርት ለተማሪዎቻቸው ማስተዋወቅና ተማሪዎቹ የትምህርቱ ፍላጎት እንዲያድርባቸው እና በንቃት እንዲከታተሉ ማነቃቂያ ማድረግ፣ ስለአቀረቡት ርዕስ ራሳቸው አስቀድመው ማብራሪያ ከመስጠታቸው በፊት ተማሪዎቹ ስለርዕሱ ቀደም ያለ ዕውቀት እንዳላቸው እድል በመስጠት መጠየቅ ፣በመጨረሻም በሚያቀርቡት የዕለት ትምህርት ውስጥ ሙያ ነክ ቃላት ወይም ከባድ ቃላት ናቸው ብለው የሚያምኑበትን ማስተማር ናቸው። የቃላት ፍቺው ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት አንዳንድ የመደናገርና የመረዳትን ችግር በተማሪዎቹ ላይ እንዳይከሰት ለማድረግ ይረዳሉ።

የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥም ሆነ በቤታቸው ተማሪዎቻቸው እንዲሠሩ የሚፈልጉትን ማናቸውንም ተግባር ራሳቸው በደንብ የሚያወቁት መሆን አለበት። Harmer (1991፡221)"መምህራን ተማሪዎቻችው እንዲፈፀሙላቸው የሚፈልጉትን ማንኛውም ክሂል አስቀድመው እራሳቸው ቢቻል በተግባር አሊያም በቲዎሪ ደረጃ ሊያውቁት ይገባል። መምህራን በዕቅዳቸው ላይ ከተማሪዎቻቸው ብቃት አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ ተግባር ለማዘጋጀት እንዲረዳቸው የተማሪዎቻችውን ችሎታ አስቀድመው የሚያውቁ ቢሆን ይመረጣል በማለት Dorothy (1985.51) የሚከተለውን ሀሳብ ይሰነዝራሉ። "በይበልጥ መምህራን ስለተማሪዎቻቸው አስቀድመው ካወቁ በጥሩ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል። የቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን እያዝናኑ የማስተማር ስልት የማስተማሩን ሂደት የሚያጎለብት መሆን አለበት።"ይላሉ።

Hargreaves (1972፡135-136) ሲያስረዱ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያሳዩት የአመራር ብቃት በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን እድገት ከማፈጠን አኳያ ትልቅና ወሳኝ ሚና አላቸው። ዲሞክራት መምህራን ተማሪዎቻቸው በነፃነት ሐሳባቸውን እንዲገልፁ ያበረታታሉ። በተጨማሪም አንድን ተማሪ ከሌላው ባለማበላለጥ ያከብራሉ። ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን የውስጥ ስሜት

እንዲናገር እድል ይሰጣሉ። ይህም በራሳቸው ላቅ ያለ አመለካከት እና በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያዳብሩ ያደርጓቸዋል።

ከዚህ እንደምንገነዘበው በትምህርት እቅድ ዝግጅት ወቅት የቋንቋ ትምህርቱን ኣላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛውን ድረሻ የሚወጣው መምህሩ ነው። ስለዚህ መምህሩ እቅዱን በሚያዘጋጅበት ወቅት ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ሊተገብረው እና ታላሚውን ኣላማ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ሊጠነቀቅ እና ብርቱ ጥረት ሊያደርግ ይገባዋል።

## 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ

### 2.2.1 የብሉምስ ታክሶኖሚ የመማር ስፍረቶች (Bloom's taxonomy of learning Domains)

ብሉምስ ታክሶኖሚ ማለት ምን ማለት ነው? (What is Bloom's taxonomy?) ብሉምስ ታክሶኖሚ ብዙ በደረጃቸው የተሰደሩ (የተደረደሩ) አስተሳሰቦች በስድስት የአእምዊ ደረጃዎች በውስብስብነታቸው የተደራጁ ደረጃዎች የተከፋፈለ ሞዴል ነው። ለዓመታት ደረጃዎቹ እንደመሰላል ለማሳየት ''climb to a higher level of thought'' ተሞክሮ ብዙ መምህራን ተማሪዎቻቸው ወደ ከፍተኛው የዕውቀት ደረጃ እንዲለወጡ ሲመራቸው የነበረ ነው። ሶስቱ ራከስር ያሉት ደረጃዎች እውቀት፣ ትርጉም እና ወደ ተግበር መለወጥ ናቸው። ሶስቱ ከፍተኛ ደረጃዎች ትንተና፣ ግንባታና ግምገማ ናቸው።

የትምህርት አላማ ከሚፈለገው ግብ አንጻር በአይነት በአይነቱ መመደብ እጅግ ጠቃሚ የሆነና የትምህርት አላማዎችን ለመምረጥ የሚያገለግል ዘዴ ነው። የትምህርት አላማ አይነትና ክፍል እንደ እጽዋትና እንሰሳት የዘር አከፋፈል ሁሉ አላማዎችን ማስገኘት ከምንፈልገው ውጤት አንጻር በምድብ በምድባቸው ለመደልደል ይረዳናል። የትምህርት አላማ ምድብ በአጠቃላይና በዝርዝር

ሊገለጡና ከትምህርት በኋላ ሊደረስባቸው የታለሙ የቋንቋ ትምህርት ግቦችን/ ውጤቶችን/ በመልክ በመልካቸው ያስቀምጥልናል።

የትምህርት አላማዎች በሶስት ዋና ዋና ምድብ ይከፈላሉ።እነሱም፡-

1.አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

2. ክሂሎታዊ ምድብ (Psychomoter domain) እና

3.ስሜታዊ ምድብ (Affective domain) ናቸው።

#### 2.2.1.1 አዕምሮኣዊ ምድብ (Cognitive domain)

ይህ የሚያተኩረው በእውቀት እና የአዕምሮ ክሂሎች እድገት ላይ ነው። (Bloom, 1956) እንደገለጸው ይህ ምድብ የሚያካትተው ማስታወስ (recall) ወይም ዝርዝር እውነታዎችን (recognition) ማወቅ፣ስርዓታዊ ሂደት እና ለአዕምሮኣዊ ችሎታ እና ክሂሎች እድገት የሚያገለግል ሀሳብን ነው። ይህ ስድስት ዋና ዋና ምድቦች ሲኖሩት እነዚህም ከቀላል ባህሪያት ወደ ውስብስብ ባህሪያት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

እነዚህም ምድቦች የሚታወቁት እንደ ክብደታቸው ደረጃ ነው። ይህ ማለት የመጀመሪያዎቹን በደንብ ከተካንን ከተረዳን በኋላ ነው ወደ ሚቀጥለው የምንሸጋገረው። እነሱም ዕውቀት (knowledge)፣ ፍችን መረዳት (compresnsion)፣መከወን /ወደ ተግባር መለወጥ/ (Application)፣ ትንተና (Analysis) ፣ማጠቃለል /ግንባታ/ (Synthesis) እና ግምገማ (Evaluating) ናቸው። የአዕምሮአዊ ምድብ መግለጫ (Bloom, 1956)

**1.እውቀት (Knowledge)** እውቀት ቀደም ብለው የተማሩትን ማስታወስን ይይዛል። ይህም አንዳንድ ነገር ከዝርዝር እውነታ ተነስቶ አጠቃላይ ቃለነቢባዊ እሳቤዎችን ለማስታወስና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ስራ ላይ መዋልን ያጠቃልላል። እውቀት ከአዕምሮአዊ ክፍል ውስጥ ዝቅተኛውን ምድብ ያመለክታል።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍ ቃላት የሚከተሉትን ይይዛሉ**

ያስተካክላሉ፣ይተነብያሉ፣ይገልፃሉ፣ይለያሉ፣ያውቃሉ፣ያመለክታሉ፣ይዘረዝራሉ፣ያዛምዳሉ፣ይጠራሉ፣ያስታውሳሉ፣አስመስለው ይሰራሉ፣ይመርጣሉ፣ማለት(እንዲህይላሉ)፣…

**2.ትርጉም /ፍች/ን መረዳት (Comprehension) ፡-**በጥሬው ሲተረጎም አንድን ነገር ተረድቶ የመያዝና ለዚያ አስፈላጊውን የመግለጫ ትርጓሜ መስጠት መቻልን ያመለክታል። ይህም የሚያጠቃልለው ቀጥታ ትርጓሜን ማለትም ከአንድ ቅርጽ ወደ ሌላ፣ቃላትን ወደ ቁጥር የማመሳሰልን ትርጓሜን ማለትም ማስረዳትንና ማጠቃለልን ከትርጉሙ በመነሳት ለወደፊት ምን እንደሚደረግ መተንበይን ይይዛል። ትርጉም ከእውቀት ላቅ ያለ ቢሆንም አሁንም በዝቅተኛ የአዕምሮአዊ ምደባ ደረጃ ላይ ይገኛል።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍቃላት**

ይለውጣሉ፣ ይተረጉማሉ፣ ይለያሉ፣ ዋጋ ይገምታሉ፣ ያስረዳሉ፣ ያጠቃልላሉ፣ ምሳሌ ይሰጣሉ፣ ይተነብያሉ፣ እንደገና ይጽፋሉ፣ ያሳጥራሉ፣ ትርጉሙን ያብራራሉ፣ …

4. **መከወን /ወደ ተግባር መለወጥ (Application)፡-**ወደ ተግባር መለወጥ ማለት ቀደም ሲል ያወቁትን ወይም በክፍል ውስጥ የተማሩትን ወደ አዲስና ተጨባጭ ሁኔታዎች መለወጥ ነው። ይህም የሚያጠቃልለው ህጎችን፣ዘዴዎችን፣ጽንሰ ሐሳቦችን፣ መመሪያዎችን እና ፍልስፍናዎችን ወደ ተጨባጭና ተግባራዊ ሁኔታዎች ማሸጋገር መቻልን ያጠቃልላል። ይህ የአዕምሮታዊ ምደባ ከላይ ከተጠቀሱት ከእነ ትርጉም ላቅ ያለ ደረጃ ላይ የሚገኝ ምደባ ነው።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍቃላት**

ይለውጣሉ፣ ይሰራሉ፣ ሰርተው ያሳያሉ፣ ይፈለስፋሉ፣ ያስተካክላሉ፣ ያንቀሳቅሳሉ፣ ይተነብያሉ፣ ያዘጋጃሉ፣ ያገናዝባሉ፣ ይጠቁማሉ፣ ይተገብራሉ፣ ያዛምዳሉ፣…

**4.ትንተና (Analysis) ፡-** ትንተና አንድን ነገር ወደ መሰረታዊ ክፍሎች የመበተን ችሎታን ያመለክታል። ይህ የሚጠቁመው በትንተናው ወቅት የአንድን ግዙፍ አካል መሰረታዊ ክፍሎችን በማወቅ የድርጅታዊ መዋቅሩን ግልጽ በሆነ መንገድ ለመረዳት እንዲቻል ነው። ትንተና ክፍሎችን መለየትን፣ የክፍሎችን ዝምድና ማወቅንና በድርጅታዊ ህጎች ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉትን ቁምነገሮች ማስተዋልን ይይዛል። ትንተና በአዕምሮታዊ ምደባ ውስጥ እስከ አሁን ከተገለጡት የበለጠ ደረጃ አለው። ይህም የሆነበት ምክንያት አንድን ነገር ለመተንተን ስለነገሩ ይዘትና መዋቅር ደህና አድርጎ መረዳትን ስለሚይዝ ነው።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍቃላት**

በክፍል በክፍሉ ያስቀምጣሉ፣ ይተነትናሉ፣ ይከፋፍላሉ፣ ይገልጣሉ፣ ይመርጣሉ፣ ያዛምዳሉ፣ ይጠቁማሉ፣ ስዕላዊ መግለጫ ያሳያሉ፣…

**5.ግንባታ (Synthesis):-**ግንባታ ማለት ልዩ ልዩ ክፍሎችን በአንድ ላይ በመሰብሰብ አንድ

አዲስ ነገር መፍጠር ነው። ግንባታ ንግግር ማዘጋጀትን፣ ጥናት ማካሄድንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። ይህ ምደባ በአዕምሮታዊ የምደባ ክፍል ውስጥ ከፍተኛው ሲሆን የመፍጠር ችሎታን ሊያስጨብጡ የሚችሉ አላማዎችን የሚያጠቃልል ነው።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍ ቃላት**

ያጣምራሉ፣ ይቀላቅላሉ፣ ይደምራሉ፣ ይፈጥራሉ፣ ይክባሉ ይደርሳሉ፣ ዲዛይን ያወጣሉ፣ ያሻሽላሉ፣ ይገነባሉ፣ እንደገና ያዘጋጃሉ፣ ያዛምዳሉ፣ ያስተውላሉ፣ ያጠቃልላሉ፣…

**6.ግምገማ (Evaluation)፡-** የአንድን ነገር ዋጋ የመመጠንና የመገምገም ችሎታን ይይዛል። ለምሳሌ የአረፍተ ነገርን፣ የግጥምን፣ የአንድ ጥናታዊ ጽሁፍን፣ የቅርጽንና የመሳሰሉትን ደረጃ መገምገምን ያጠቃልላል። ይህም ግምገማ በአንድ በተወሰነ የመገምገሚያ ነጥብ ላይ መመስረት አለበት። የመገምገሚያው ነጥቦች በሚገመገመው ጉዳይ ላይ የተመሰረቱ ወይንም የሚገመገመው ጉዳይ በሌላ በኩል ከሆኑ ነጥቦች የሚወዳደር መሆን አለበት። ግምገማ በአዕምሮኣዊ ምደባ ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ የያዘና በውስጡም ሌሎችን ምደባዎች በሙሉ የሚያጠቃልል ነው። በተጨማሪም ግምገማው ግልጽ በሆነ የመገምገሚያ ነጥቦች ላይ የተመሰረተ የህሊና ፍርድ የያዘ መሆኑ መረሳት የለበትም። ከቋንቋ ትምህርት አንጻር ይህ ምድብ የስነልሳንን እና የስነ ጽሁፍ እውቀተን ለማስተማር እና እነዚህን እውቀቶች ለማስጨበጥ በይበልጥ የሚረዳ ስፍረት ነው።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍቃላት በአብዛኛው የሚከተሉትን ያቅፋሉ፤**

ይገመግማሉ፣ ማስረጃ ያቀርባሉ፣ ሂስ ይሰጣሉ፣ ይደግፋሉ፣ ያጠቃልላሉ፣ ምክንያት ይሰጣሉ፣ መከላከያ ያቀርባሉ፣…

ከላይ ከተጠቀሱት የአዕምሮታዊ ምድብ ክፍሎች ትንተና የምንረዳው መምህራን የቋንቋ ትምህርት እቅድ አላማ በሚያቅዱበት ጊዜ የተማሪዎቻቸውን እውቀት ለማወቅ ማለትም የተማሩት ነገር ምን ያህል ካላቸው እውቀት አንፃር መግለፅ እንደሚችሉ ለመረዳት፣ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ይዘት የመተርጎም ብቃታቸውን ማወቅን፣ የተማሩትን ትምህርት እንዴት ወደ

ተግባር እንደሚለወጡ ለማወቅ፣ የቀረበላቸውን ይዘት እንዴት ወደ ተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች መተንተን እንደሚችሉና በተቃራኒውም የተዘረዘሩትን ንዑሳን ክፍሎች በአንድ ላይ ማዋቀር ወይም መገንባት መቻላቸውን ለማወቅና ተማሪዎቹ ካላቸው የተለያየ እውቀት አንፃር መገምገም መቻላቸውን ለማቀድ ያግዛቸዋል፡፡

### 2.2.1.2 ክህሎታዊ ምድብ (Psychomoter domain)

ይህ የክሂሎታዊ ምድብ የሚያተኩረው የተማሪዎችን ክሂሎች ማዳበር ላይ ነው (Harrow.A.J. 1972) ፡፡በይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ደረጃዎች ስር የሚመደቡት የመጀመሪያው ቅፅበታዊ እንቅስቃሴ (Reflex) ሲሆን ብዙ ጊዜ በዚህ ዝቅተኛ ደረጃ (low level) የትምህርት አላማዎች አይገለፁም፡፡ ሁለተኛው መሰረታዊ እንቅስቃሴ (fundamental movements) የሚባለው ሲሆን ይህ ብዙ ጊዜ የሚተገበረው በታዳጊ ልጆች (young children) ነው፡፡ መዳህ (crawl)፣ መሮጥ፣ መዝለል፣ መድረስ፣ አቅጣጫ መቀየር የሚባሉትን ነገሮች በውስጡ ይይዛል፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታ (perceptual abilities) መያዝ፣ መፃፍ፣ ሚዛን መጠበቅ ፣መለየት፣ መቆጣጠር የሚሉትን ሀሳቦች በውስጡ ያካትታል፡፡

አራተኛው አካላዊ ችሎታ (Physical abilities) ደግሞ ማቆም መጀመር፣ በፍጥነት መሄድ፣ መቀየር፣ መዋሀድ የሚሉትን በውስጡ ሲይዝ አምስተኛው ክህሎታዊ እንቅስቃሴ (Skill movement) ሲሆን መጫወት፣ ምት፣ መዋኘት፣ መጥለቅ፣ መጠቀም በውስጡ ይይዛል፡፡ ስድስተኛ የማይዋዥቅ ግንኙነት (nondiscursive communication) መግለፅ፣ መፍጠር፣ መቅረፅ፣ አንድን ድርጊት መረዳት ያመለክታል፡፡ ይህም ከቀላል ወደ ውስብስብ የቀረበ ነው፡፡

ይህን ሀሳብ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ይመለከታል፡፡ እነሱም አንደኛ ማዳመጥ ድምጸችን ለመለየት፣ መልዕክትን ለመረዳት፣ መረጃን ለመቀበል፣ ተናጋሪዎች ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ለማገዝ፣ መልዕክትን ለመገምገም፣ ራስን ለማዝናናትና ንግግርን ለማድነቅ እነዚህን ሀሳቦች አላማ በማድረግ የሚተገበር የክሂል አይነት ነው በማለት (በድሉ 1996፣46) ገልጿል፡፡

ሁለተኛ ንግግር በተናጋሪውና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት ነው። ማቀበያ (productive skill) ክሂል የሆነው የንግግር ክሂል ይዳብር ዘንድ መቀበያ (receptive skill) የሆነው የማዳመጥ ክሂል መዳበር አለበት። የሁለቱ ክሂሎች መዳበር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። በአብዛኛው የቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ተግባራት በተለይ አንድ የቋንቋ ክሂል ላይ ማተኮር አስፈላጊ ይሆናል። በተለይ በንግግር በተናጋሪውና በአድማጭ መካከል የሚሄድ የሁለትዮሽ ቃላዊ ተግባቦት መሆኑን ልብ ማለት ያሻል በማለት (በድሉ1996፤57) ገልጿል።

ሶስተኛ ማንበብ ማለት አንድ የቀረበን ፅሁፍ ወይም ነገር ትክክለኛ ድምጾቱን ጠብቆ ማንበብ መቻልን ያመለክታል። ተማሪዎች ያነበቡትን ጽሁፍ አስመልክቶ ማብራሪያ እንዲሰጡ ቢጠየቁ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍ ይላል። ያነበቡትን ቅንጫቢ ፍሬ ሀሳብ ይህ ነው ብለው ለማጠቃለል ያበቋቸው መረጃዎች ምን እንደሆኑ ምክንያቶቻቸውን እንዲዘረዝሩ ቢደረግ የዘነጓቸውን ጠቃሚ ዝርዝር መረጃዎች ያስታውሳሉ። ዝርዝር ጉዳዮችን ማስታወስ ደግሞ ማን፣ መቼ፣ እንዴት፣ የትን፣ለምን ከዋናው ሀሳብ/ ጭብጥ ጋር እንደሚገናኝ ለማወቅ ይረዳል በማለት (በድሉ1996፤39-40) ገልጿል።

አራተኛው ፅህፈት ሲሆን ጥሩ የመፃፍ ችሎታ ተማሪዎች ጥሩ የማሰብ ብልሀት (thinking strategies) እንዲያዳብሩ ያደርጋል። መላ መምታትን፣ መጠየቅን፣ ግምት መስጠትን፣ መላ ምት ማረጋገጥን እና የተደረሰበትን ውጤት መገምገምን እንዲማሩ ያደርጋል (Block and Mangieri, 1995; Applebee, Langer and Mullis, 1988)፡ አዘወትሮ የሚጽፍ ተማሪ የሚጽፈውን ይዘት እየከለሰ ይመረምራል። ያደራጃል። ከቃላት ጋር ስለሚጫወት የተለያዩ ፍቺዎቻቸውን ያውቃሉ፤ የአገላለፅ ስልቱን ያዳብራሉ፤ የራሱን ሀሳብ ማደራጀት ይማራል። ከዚህ በተጨማሪ ጽሁፋቸው በሌላው መነበቡ ስለራሳቸው ያላቸውን ግምት ከፍ ያደርጋል፤ ለሌላው አስፈላጊ እንደሆኑ አድርገው ይገምታሉ በማለት (በድሉ1996፤52) ገልጿል።

ከላይ ከተገለፁትን የክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎችን ወደ ቋንቋ ትምህርት አምጥተን ስንረዳው መምህራን የቋንቋት ምህርት እቅድ አላማ በሚያቅዱበት ጊዜ የተማሪዎቹን የቋንቋ ክሂል ለማለማመድና ለማዳበር የተሰጠውን ይዘት መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ክሂል የሚሰጠውን

ትኩረት ማለትም ከማንበብ፣ ከፅህፈት፣ ከማዳመጥና ከንግግር ክሂል አንፃር እንዴት ማዳበር እንዳለባቸው ለማቀድ የሚያግዝ መሆኑን ነው፡፤

### 2.2.1.3 ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)

ስሜታዊ ምድብ እንደ karthwal, Bloom, Masia,(1973) አገላለፅ የሚያጠቃልለው ነገሮችን በስሜታዊነት (enthusiasms) የምናይበት ሁኔታ ነው። ለምሳሌ፣ ስሜትን፣ እሴትን (values) ፣ አድናቆትን፣ ፍላጎትን፣ ምስጋናን፣ መልመድን፣ ተነሳሽነትን እና ዝንባሌን ያጠቃልላል። የስሜታዊ ምድብ አምስቱ ዋና ዋና ክፍሎች ከቀላል ባህሪያት ወደ ውስብስብ ባህሪያት ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

**1.መቀበል(receiving)፡-**መቀበል የሚያመለክተው የአንዱን ተማሪ አንድን ክስተት ወይም ማነቃቂያ ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ወይም ፈቃደኛ መሆን ነው። እንደ የክፍል ትምህርት፣ መጽሀፍ ማንበብ፣ ሙዚቃ መስማትንና የመሳሰሉትን ወደ ትምህርቱ መስክ ስንመለስ መቀበል ማለት ማግኘትን፣ መያዝንና ማቆየትን ሲጠቁም ለዚህ የተማሪውን ሃሳብ መሰብሰብን ነው። የአንድ ነገር የመኖር ግንዛቤ ሲያውቅና ለዚያ ነገር የራሱን ፍላጎት ሲያሳይ ነገሩን ለመቀበል ዝግጁ ሆኗል ማለት ነው። መቀበል በስሜታዊ ምደባ ክፍል ውስጥ ዝቅተኛውን ደረጃ ያመለክታል።

#### ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍ ቃላት

ይጠይቃሉ፣ ይመርጣሉ፣ ይገልፃሉ፤ ይከታተላሉ፣ ይይዛሉ፣ ይጠቁማሉ፣ ይሰይማሉ፣ ይጠራሉ፣ ያመለክታሉ፣…

**2.መመለስ (responding) ፡-** መመለስ የሚያመለክተው ተማሪው በክፍል ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ነው። ይህም የሚያመለክተው ተማሪው የአንድን ክስተት ወይም ማነቃቂያ መቀበሉን ብቻ ሳይሆን ስለክስተቱ የራሱ የሆነ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን ነው። ተማሪው ለአንድ ነገር መልስ ለመስጠት ዝግጁ ሲሆን / የቤት ስራ መስራት፣/ በፈቃደኛነት ለመመለስ ቢፈልግ (ከታዘዘው በላይ ሲሰራ፣/ በነገሩ መሰረት ደስተኛ ሲሆን/ ለደስታ መስራት/ በስሜታዊ ምደባ ውስጥ ከፍ ወዳለ ደረጃ መሸጋገሩን ያመለክታል።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍ ቃላት (key words)**

ምላሽ ይሰጣሉ፣ ድጋፍ ይሰጣሉ (assists)፣ ይመልሳሉ፣ ያግዛሉ፣ያረጋግጣሉ፣ ይወያያሉ፣ ሰላምታ ይሰጣሉ፣ ይረዳሉ፣ ያከናውናሉ፣ ያመለክታሉ፣ ይመርጣሉ፣ ይናገራሉ፣ ይፅፋሉ፣… **3.ዋጋ መስጠት( Valuing)፡-**አንድ ተማሪ ለሚማረው ትምህርት ስለጠቃሚነቱ፣ ስለእውቀት ሰጭነቱ የራሱ የሆነ ዋጋ ሲሰጠው የበለጠ የመማርና የማወቅ ፍላጎቱ መቀስቀስ ማለት ነው። የዋጋ መስጠቱ ሁኔታ በደረጃ ይለያል። በቀላል (ማለትም በጋራ መስራት ና በጋራ የስራ ችሎታ ማሻሻልን) ወደ ከባድ (ማለትም በጋራ ለመስራት ኃላፊነት መቀበልንና) የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍ ቃላት (keywords)**

ያጠናቅቃሉ፣ ያስረዳሉ፣ ይለያሉ፣ ይገልጣሉ፣ ይከተላሉ፣ ይፈጥራሉ፣ ይጀምራሉ፣ ይጋብዛሉ፣ ይቀላቅላሉ፣ ነጥቡን ያስረዳሉ፣ ሃሳብ ያቀርባሉ፣ ያነባሉ፣ ያመለክታሉ፣ ይመርጣሉ፣ ያካፍላሉ፣ ያጠናሉ፣ ይሰራሉ፣….

**4.ድርጅት (organization) ፡-** ድርጅት የሚያጠቃልለው የተለያዩ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች በማዛመድና በውስጣቸው ሊገኝ የሚችለውን ቅራኔ በመፍታት አንድ ጽኑ የሆነ ዋጋ መስጠትን ወይም ማበጀትን ነው።

ይህም እንደ ማወዳደርን፣ ማዛመድንና መገንባትን ያሉት ዋጋ በመስጠት ላይ ማተኮር ነው። የዚህም ውጤት ለጽንሰ ሀሳብ ዋጋ መስጠትን የእያንዳንዱን ግለሰብ ኃላፊነት ማወቅን ወይም የአንድን ስርዐት ማደራጀትን የሙያ ትምህርት በማዋቀር ለአንድ አገር የኢኮኖሚ እድገት ማምጣትንና የህዝብን ፍላጎት ማሟላትን ያመለክታል።

በዚህ ምደባ አማካኝነት የአንድን ሰው ሕይወት፣ የኑሮ ፍልስፍና መያዝ እስከ መቻል ድረስ ይደርሳል።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍቃላት (key words)**

በሀሳቡ ይፀናሉ፣ ያደራጃሉ፣ ያጣምራሉ፣ ያወዳድራሉ፣ ይፈፅማሉ፣ ያግዛሉ፣ ያስረዳሉ፣ ያጠቃልላሉ፣ ይለያሉ፣ ያዋህዳሉ፣ ይቀይራሉ፣ ያስተካክላሉ፣ ያዛሉ፣ ያዘጋጃሉ፣ ያዛምዳሉ፣ ይገነባሉ፣ይለውጣሉ፣…

**5.ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (characterization by value complex)፡-** ተማሪው

እዚህ ደረጃ በሚደርስበት ጊዜ ኑሮውን ለመምራት የሚያስችለው ልምድ ያገኛል። ስለሆነም የተማሪው ጠባይ ግልጽ፣ የማይለዋወጥና ሊተነበይ የሚችል ይሆናል። በዚህ የስሜታዊ ምደባ ሰፋ ያለ ስራ የሚከናወንበት ቢሆንም ዋናው ትኩረት የሚደረገው የግለሰቡን ግላዊ ልምድ እማዳበሩ ላይ ይሆናል።

በዚህ መሰረት የሚጻፉት አላማዎች የግለሰቡን ጠቅላላ ጠባይ ማስተካከያ ላይ ማተኮር እንደ ሚገባ ቢጠቁም ምግላዊ፣ ማኅበራዊና እድገቱ ሁሉ አብሮ መዳበር እንዳለበት መዘንጋት የለበትም።

**ይህንን ለማመልከት የሚያገለግሉት ቁልፍ ቃላት (key words)**

ይፈፅማሉ፣ ይለያሉ፣ ይገልጣሉ፣ ያግባባሉ፣ ያዳምጣሉ፣ ያሻሽላሉ፣ ይሰራሉ፣ ይለማመዳሉ፣ ሃሳብ ያቀርባሉ፣ ይመጥናሉ፣ ይጠይቃሉ፣ እንደገና ያጠናሉ፣ ይከልሳሉ፣ ያገለግላሉ፣ ይፈታሉ፣ ይጠቁማሉ፣ ያስረዳሉ፣…

በአጠቃላይ ከላይ ከተዘረዘሩት የስሜታዊ ምድብ ክፍሎች የምንረዳው መምህራን የቋንቋት ምህርት እቅድ አላማ በሚያቅድበት ጊዜ የተማሪዎቻቸውን ስሜት፣ ዝንባሌ፣ ፍላጎት፣ … ለመለየት በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማቸው ላይ የሚያሰፍሯቸውን ሀሳቦች ተማሪው የሚማረውን ትምህርት ምን ያህል መቀበል እንደሚፈልግ፣ በሚማረው ትምህርት ላይ ተነሳሽነቱን በማሳየት መልስ መመለሱንና የሚሰጠውን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ መስራትን፣ የሚማረውን ትምህርት ጠቃሚነቱን በመረዳትና ለትምህርቱ ዋጋ በመስጠት በግልም ሆነ በቡድን ለመወያየት መዘጋጀትንና ሀላፊነት መቀበልን፣ የተለያዩ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች በማዛመድና በውስጣቸው ሊገኙ የሚችሉ ችግሮችን በመፍታት ዋጋ መስጠትንና የተማሪውን ግላዊ ልምድ ማዳበር ላይ ቢያተኩሩና ቢያቅዱ ተገቢነት እንዳለው ነው። በአጠቃላይ ይህ ጥናትም የBloom's taxonomy ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ የተሰራ ነው።

## 2.2.2 የትምህርት እቅድ እርከኖች (Lesson Plan Phases)

የትምህርት እቅደ ሲዘጋጅ አላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ተግባራትን፤ እነዚህን ተግባራት በወጉ ማደረሻ አቀራረቦችን፣ ተደጋጋሚ ልምምዶችን፣ አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ግምገማዎች ከምጋቤ ምላሻቸው ጋር እና ማጠቃለያዎችን ሊይዙ እነደሚገባ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ። ከነዚህ በተለየ ዘርዘር አድርጎ የእለታዊ ትምህርት እቅድን ከኒግሀም (2009) የትምህርት እቅድ እርከኖችች (Lesson Plan Phases) በስምንት እርከኖች/ ደረጃዎች/ በመመደብ እንደሚከተለው ያቀርባል።

**እርከን አንድ፤ መግቢያ (Introduction)** ፤ በዚህ ክፍል የእለቱን ትምህርት ርእስ፣ ዋናውን የትመህርቱን ሀሳብ የእለቱን ትምህርት ጠቀሜታ፣ የትኩረት አቅጣጫውን በማስተዋወቅ ተማሪዎችን ወደ እለቱ ትምህርት ተስበው እንዲገቡ ማድረጊያ ደረጃ ነው።

**እርከን ሁለት፤መደላድል/ መሰረት (Foundation)**

የቀደመውን የትምህርት ይዘት በማስታወስ፣ የእለቱን ይዘት ቁልፍ ሀሳቦች በማንሳት፣ የእለቱን ትምህርት ዓላማ ትኩረት በመስጠት ዋና ዋና ነጥቦችን ግልጽ በማድረግ፣ የቀደምት እዉቀታቸዉን ከአሁኑ ጋር ለማገናኘት የሚረዳ መደላድል /መሠረት የሚፈጠርበት ክፍል ነው።

**እርከን ሶስት፤ አዕምሮን ማነቃቃት (Brain Activation)**

ስላለፈው ትምህርታቸው እና ሰለእለቱ ትምህርታቸው የሚያውሱ ጉዳዮችን በጥያቄዎችና በውይይት መልክ በማንሳት ልዩ ልዩ ሀሳቦችን በማፍለቅ የተማሪዎች አእምሮ ለእለቱ ትምህርት በንቃት እንዲዘጋጅ የሚደረግበት ክፍል ነው።

**እርከን አራት፤ የአዲስ እውቀት / የእለታዊ መረጃ አካላት (Body of New Information)**

የእለቱን ይዘት በገለጻ፣ በንባብ፣ ማስታወሻ በመስጠት፣ በቡድን እና በጥንድ ወይም በተናጥል በማወያየት የእለቱን አዲስ የትምህርት ይዘት ወይም መረጃ የሚሰጥበት (የሚቀርብበት) ክፍል ነው።

**እርከን አምስት፤ ግልጽ ማድረግ (Clarification)**

የተለያዩ ጥያቄዎችን፣ ውይይቶች እና ገለታዎችን በማቅረብ በእለቱ የቀረበላቸውን የትምህርት ይዘት በማብራራት ተጨባጭ እና ግልጽ በማድረግ የትምህርት ይዘቱን ከዓላማ ጋር አቀናጅቶ የሚቀርብበት ክፍል ነው።

**እርከን ስድስት፤ ማለማመድ እና መከለስ (Practice and Review)**

ተማሪዎች በእለቱ የተማሩትን (የቀረበላቸውን) የትምህርት ይዘት በልዩ ልዩ መልክ መልመጃዎችን በመስጠት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ደግመው እንዲሉት ወይም እንዲሰሩት በማድረግ ስለእለቱ የትምህርት ይዘት ልምምድ እና ክለሳ የሚያደርጉበት ክፍል ነው።

**እርከን ሰባት የተናጥል (ግላዊ ልምምድ) (Independent Practice)**

የእለቱን የትምህርት ይዘት ከአላማው አንጻር ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱት እና በደንብ እንዲረዱት ግላዊ የሆኑ ስራዎችን፣ ሙከራዎችን፣ የተናጥል መለመጃዎችን፣ ሙከራዎችን የሚሰጥበት ክፍል ነው።

**እርከን ስምንት፤ መደምደመያ (Closure)**

የእለቱን ትምህርት ይዘት አንኳር አንኳር ሀሳቦችን በማንሳት አጠቃሎ ወደ መደምደሚያ ወይም መዝጊያ የሚመጣበት ክፍል ነው። ስለእለቱ ትምህርት ይዘት ማጠቃለያ በመስጠት ከሌሎች ተቀረራቢ ሰፊ የትምህርት ይዘቶች ጋር የሚሰናሰሉበት መንገድ የሚጠቆምበት ክፍል ነው።

ጥሩ የሚባል እና በብቸኝነት የሚመረጥ የትምህርት እቅድ የለም። የትምህርት እቅድ በአብዛኛው እና በመሰረታዊነት እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ከሞላ ጎደል በማካተት መቅረብ እንዳለበት እነ ከኒግሀም/ Cunnigham/ (2009) ፣ ኬንዝ ብያሬ (2010)/ Kenneth Beare/ (2018) በተሸሻለ መልኩ በመዘርዘር ይገልጹታል። አንድ መምህር የቱንም ያህል ልምድ እና እውቀት ቢኖረውም ለሚያስተምረው ጉዳይ በስርኣቱ የተደራጀ እቅድ ሊኖረው ይገባል። ይህ ካልሆነ የትምህርቱን ይዘት የቱንም ያህል የሚያውቀው ቢሆንም በስርአት እና በረድፍ ደርጅቶ ለማስተማር ይቸገራል።

## 2.3. የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

የዚህ ጥናት ትኩረቱ በጋምቤላ ክልል በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2011ዓ.ም የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት እቅድ መዳስስ ሆኖ በተለይም የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ከብሉም ታከሶኖሚ አንጻር የአላማ አነዳደፍን ከይዘቱ ጋር ያለዉን ተዛምዶ በትኩረት መተንተን ይሆናል። ልዩነታቸው የሰፋ ቢሆንም በተወሰነ መልኩ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ቀርቧል።

የመጀመሪያዉ በጁሌ አን ቫን ሲክል/ Julie Ann Van Sickle/ (2011) "የትምህርት ዕቅድ ተጽእኖ በመምህራን የማስተማር ዉጤታማነትና የመረዳት ችሎታ '' በሚል ርዕስ በ Humboldt State University ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበዉ ጥናታዊ ፅሁፍ ነዉ። ጥናቱ ትኩረት ያደረገዉ የትምህርት ዕቅድ ተጽእኖ (አዉንታዊ አልያም አሉታዊ) በመምህራን የመረዳት ችሎታና የማስተማር ዉጤታማነትን መፈተሽ ሲሆን የት እና በምን ዓይነት መንገድ መምህራን በትምህርት ዕቅድ ላይ አሉታዊም ይሁን አወንታዊ ተጽእኖዉ በመማር ማስተማር ላይ ተዛምዶ እንዳለዉ ልምዳቸዉንም ለማየት ጭምር የተዘጋጀ ጥናታዊ ጽሁፍ ነዉ። ለጥናቱ የተጠቀመበት የአጠናን ዘዴም ቅይጥ የምርምር ዘዴ ሲሆን ጥናቱ ዕለታዊ የትምህርት እቅድን ትኩረት አድርጎ የአላማና የይዘት ተዛምዶን ባይመለከትም ጥቅል የትምህርት እቅድን መመልከቱ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለዉ።

ሁለተኛ ዉበቮልካን ሲሰክ እና በህዳየት ቶክ /Volkan Cicek እና በ Hidayet Tok/ (2009) በዩኤስ አሜሪካ እና በቱርክ አገሮች "የአስራ ሁለተኛ ክፍል እና የመዋእለ ሕፃናት ትምህርት ለማጎልበት የትምህርት ዕቅድ ያለዉ ተገቢነት '' በሚል ርዕስ ሁለቱን የክፍል ደረጃዎች ያነፃፀረ ሲሆን ጥናታዊ ፅሁፉ ዓመታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ያላቸዉን ፋይዳ ለማነፃፀር የቀረበ ነዉ። የእነዚህ ሁለቱ አጥኝዎች ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያጠነጥ ነዉ ዓመታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን አተገባበር በአንድ ላይ አጣምሮ የተመለከተ ቢሆንም የዕለታዊ የትምህርት ዕቅድን ትኩረት አድርጎ አላማዉ ከይዘት ጋር ያለዉን ተጣጥሞሽ ያለመፈተሹ ከዚህ ጥናት ጋር ቢለይም ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን መጠቀሙ ግን ያመሳስለዋል።

በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በሀገር ውስጥም በርካታ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ በዚህ ጥናት አቅራቢ ከተዳሰሱት የመጀመሪያው ዮሴፍ (1989) "የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መረሃ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች አነዳደፍና ይዘቶች አደረጃጃት ብቃት ትንተና" በሚል ርዕስ በኣዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ እንዲሆን ያካሄዱት ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መረሃ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች አነዳደፍና ይዘቶች አደረጃጃት ብቃትን መገምገም ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው ገላጭ የምርምር አይነት፣ እንዲሁም ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ምንጩ የፅሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና ሰነድ ፍተሻ፤ የመረጃ መተንተኛ ዘዴው አይነታዊ ሲሆን የናሙና አመራረጥ ዘዴው አመቺ ንሞና ዘዴ ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መረሃ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች የአላማ አነዳደፍ መርሆዎችን ተከትለው አለመነደፋቸውን፣ ዝርዝር አላማዎቹ ግልፅነት የሚጎላቸው ከመሆኑም ባሻገር አደረጃጀታቸው የተዛባ መሆኑ፣ የዝርዝር አላማዎችና ይዘቱን ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የሌላቸው መሆኑን ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ባጠናው የክፍል ደረጃ፣ በምርምር አይነቱ፣ በመረጃ መሰብሰቢያነት በተጠቀመበት ዘዴ ይመሳሰላል፡፡ በሌላ በኩል ጥናቱ የተካሄደበት አመተ ምህረት፣ ቦታው፣ ሁኔታው እና የሚጠናው መጽሀፍ፤ የመርሀ ትምህርቶችን ዝርዝር አላማዎች አነዳዳፍንና የይዘቶች አደረጃጀትን መፈተሹ፣ የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ከዚህኛው ጥናት ልዩ ያደርገዋል፡፡

በሁለተኛው ደረጃ የተዳሰሰው ደግሞ የሙሉ ቀን (1991) "በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የአራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ1991ዓ.ም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሳምንታዊ/ ዕለታዊ የትምህርት ቅጽ ብቃት ፍተሻ" በሚል ርዕስ ለዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ ለክፍል ደረጃዎቹ በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሳምንታዊ/ ዕለታዊ የትምህርት ቅጽ ብቃት መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተው ገላጭ የምርምር ዘዴን ሲሆን ሰነድ ፍተሻንና የፅሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመ ሲሆን የናሙና አመራረጥ ዘዴው ነሲብ ንሞና ዘዴ ነው፡፡

የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው የአላማዎች ግልጽ አለመሆን፣ የይዘት እና የግምገማ ታሳቢ አለማድረግ፣ አንዳንድ ቦታዎች ላይ መርጃ መሳሪያዎችን አለመጠቀም ነው፡፡ ይህ ጥናት

የዕለታዊ/ ሳምንታዊ የትምህርት እቅድ አሰራር ላይ መካሄዱ፣ የተከተለው የጥናት ዘዴ ገላጭ ስልት መሆኑ እና የመረጃ ምንጭ የሰነድ ምርመራን በዋናነት ማድረጉ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። በሌላ በኩል ጥናቱ የተካሄደበት አመተ ምህረት፣ በርዕሱ፣ በቦታው፣ በመረጃ መሰብሰቢያነት የፅሁፍ መጠይቅ መጠቀሙ፣ የእቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ ማተኮሩ ከዚህኛው ጥናት ልዩ ያደርገዋል።

በሶስተኛ ደረጃ የታየው ጥናት ደግሞ በነብዩ ሐረገወይን (2008) በጢሮ አፈታ ወረዳ እና በኦሞናዳ ወረዳ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ''የአማርኛ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበዉ ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረቱ ደግሞ የዕለታዊ ትምህርት እቅድ አላማ ከይዘት ጋር ያለዉን ተዛምዶ ያተኮረ እንጂ ከብሉም ታክሶኖሚ አንጻር የእቅዱ ዓላማ ከይዘቱ ጋር ያለዉን ተጣጥሞሽ የፈተሸ ያለ መሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል። ከብሉም ታክሶኖሚ አንጻር ባይመለከትም የእለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ከይዘቱ ጋር ያለዉን ተዛምዶ መፈተሹ እና ለዚሁም ገላጭ የምርምር ዘዴን መጠቀሙ ተመሳሳይነት አለዉ።

በአራተኛ ደረጃ የተዳሰሰው በመስታወት ከልክሌ (2009) "የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ ትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከብሉም የትምህርት አላማ አመዳደብ አንፃር'' በሚል ርዕስ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቀረበዉ ጥናታዊ ጽሁፍ ነዉ። ይህ ጥናት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከብሉም ታክሶኖሚ አላማ ጋር ያለዉን ተዛምዶ የዳሰሰ እንጂ ከብሉም ታክሶኖሚ አንጻር የቋንቋ ትምህርት እቅድ ዓላማ ከይዘቱ ጋር ያለዉን ተዛምዶ ያልፈተሸ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አለዉ። አጥኝዋ ለጥናቱ የተጠቀመችበት የአጠናን ዘዴ ገላጭ የምርምር ዘዴ በመሆኑ በአጠናን ዘዴ ሁለቱም ተመሳሳይነት አላቸዉ።

በቅረብ ጊዜ በነብዩ (2008) እና በመስታወት (2009) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በጅማ ዩኒቨርሲቲ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ከቦታ አንጻር ሁለቱም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ የተከነወኑ ሰሆኑ፤ ይህ ጥናት የከናወነው የስራ ቋንቋው አማርኛ በሆነው

በጋምቤላ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ የሚከናወን በመሆኑ እና  የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫም በእቅዱ አዘገጃጀት እና አተገባበር ላይ መሆኑ ይህንን ጥናት ይለየዋል።

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል ጥናት ነዉ። ይህን ጥናት ለማካኄድ ተስማሚ ይሆናል ተብሎ የተመረጠዉ የምርምር አይነት ገላጭ የምርምር ዘዴ ነው። ምክንያቱም ጥናቱ መሰረት የሚያደርገው አጠናን ገላጭ የምርምር ስልትን  በመሆኑ ነው። ይህ የጥናት አይነት የተመረጠበት ምክንያት በጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተማ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ በሚገኙ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ያሉባቸው ችግር ምን እንደሚመስል በተለያዩ መረጃ መሰበሰቢያ መንገዶች ሰብስቦ አዘገጃጀቱንና አተገባበሩን በገለጻ መልክ ለማሳየት እና የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም የሚያስችል በመሆኑ ነው። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ እንደ አስፈላጊነታቸዉ በዓይነት በዓይነታቸዉ በማደራጀት ከመስኩ ቃለነ ቢባዊ ገለጻዎች ጋር በማሰናሰል ተገቢዉን ገለጻና ትንታኔ በበቂ ሁኔታ ተሰጥቷል። በመሆኑም አጥኚዋ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን እንደ የፈርጃቸዉ ለጥናቱ እንዲዉሉ በማድረግ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የተገኙትን መረጃዎች በማደራጀት፣ ገለጻ እና ተገቢ ትንታኔ በማስቀመጥ አስፈላጊውን ማብራሪያ በመስጠት ተጠቅማበታለች።

## 3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች እና ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ የሚካተቱ ተሳታፊዎች በጋምቤላ ክልል በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። አካባቢው ለጥናት የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ መደበኛ ስራዋን በምታከናውንበት ወቅት ችግሩን በስፋት ያስተዋለችበት በመሆኑ እና ለጥናቱ የሚያስፈልጉ

መረጃዎችን በበቂ ሁኔታ በቅርበት ለማግኘት ያስችላል ተብሎ በመታሰቡ ነው፡፡ የክፍል ደረጃው የተመረጠውም ለጥናቱ በቂ እና ትክክለኛ መረጃ ለመሰብሰብ የተሻለ እንደሆነ በመታመኑ ነው፡፡ ስለዚህ የጥናቱ ንሞና ተደራሽነትን እና የመረጃ ግኝትን ታሳቢ ያደረገ ታላሚ ንሞና ዘዴ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ካለው የጊዜ እና የገንዘብ እጥረት አንጻር፤ በክልሉ ርእሰ ከተማ ጋምቤላ የሚገኘውን አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በልዩ ወረዳዉ ውስጥ ካሉት ዘጠኝ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አምስቱን ብቻ በመውሰድ አመቺ ንሞና ዘዴን (convinent sampling method) በመጠቀም በጥናቱ ዉስጥ በተጠኝነት ተካተዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ንሞና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ለጥናቱ አላማ እና አሰራር ካላቸዉ አመቺነት አንጻር ነው፡፡ እነማንን ብመርጥ የምፈልገውን መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን አላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን የሚመርጥበት ዘዴ ነው በማለት ያለው እንዳወቅ (2009፣136) ገልጿል፡፡ መምህራንን በተመለከተም ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቁጥር አነስተኛ አስራሁለት ስለሆኑ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ (comprehensive sampling method) ሁሉም ተመርጠው የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ምክንያቱም ከወሳኝ ንሞና (non-probability sampling) ውስጥ ጠቅላይ ንሞና ዘዴ ተመራማሪው ያገኛቸውን ሁሉንም የጥናቱን አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ አድርጎ ሲወስድ ጠቅላይ ንሞና ይባላል በማለት ያለው እንዳወቀ ( 2009፣ 132 ) ገልጿል፡፡

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በጥናታዊ ፅሁፍ አዘገጃጀት ወቅት በርካታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቢኖሩም ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መረጃ መሰብሰቢያነት አጥኚዋ የተጠቀመችባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሰነድ ፍተሻ፣ ምልከታ፣ እና ቃለ መጠይቅ ናቸዉ፡፡ እያንዳንዳቸዉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በሚከተለዉ መንገድ ተግባር ላይ ዉለዋል፡፡

#### 3.3.1. የሰነድ ፍተሻ

በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከየካቲት እስከ ሚያዝያ ወር ያዘጋጇቸውን  የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ዕቅዶች (እለታዊ እና አመታዊ )ከሁሉም

መምህራን ከእያንዳንዳቸዉ አስር አስር ዕቅዶችን በመመርመር ስለዕለታዊ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር እና ከአመታዊው ጋር ተጣጥሞ ስለመሄዱ መረጃ ተሰብስቧል፤ እንዲሁም የተሰበሰበውን መረጃ በአግባቡ በማደራጀት ከእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር ንድፈ ሀሳብ ጋር በማሰናሰል ዉጤቱ ተተንትኗል፡፡

### 3.3.2. ምልከታ

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ከተሰጠው የትምህርት ዓላማ ፣ይዘት ፣የትምህርት መርጃ መሳሪያ እና የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ለማየት ይቻል ዘንድ ተገቢዉ የምልከታ መከታተያ ቅጽ፤ የእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን የሚገለጹ ሞዴሎችን የብሉምስ ታክሶኖሚን አላማ አነዳደፍ ስርአት የሚያትቱ ቃለነቢቦችን መሰረት በማድረግ፤ ተዘጋጅቶ በየትምህርት ቤቶቹ በሚያስተምሩት መምህራን ላይ በመደበኛዉ የማስተማሪያ ወቅት በእያንዳንዱ መምህር ሶስት ጊዜ ምልከታ ተደርጓል፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን የመማር ማስተማር ሂደት ከእቅዱ አንጻር ምን እንደሚመስል በማሳየት እለታዊ እቅዶቹ ከአመታዊው እና ሳምንታዊው ጋር ተጣጥሞ መሄዱን በተጨባጭ የሚያሳየን የመረጃ መሰብሰቢያ ሥልት ነው፡፡

### 3.3.3. ቃለ መጠይቅ

ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የእቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን በተመለከተ ሳይንሳዊ ሂደቱን ጠብቀው ለማዘጋጀትም ሆነ መተግበር የሚያጋጥማቸው ችግር ካለ ከእቅድ ዝግጅት አኳያ ስላላቸው ንድፈ ሀሳባዊ ግንዛቤ በፅሁፍ የተዘጋጀ (መር እና ከፊል መር) ቃለ መጠይቅ ለእያንዳንዱ መምህር ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም የእቅዱን አተገባበር እና አፈጻጸም በቅርብ ሆነው የሚከታተሉት የየትምህርት ቤቶቹ ርእሳነ መምህራን ወይም ምክትል ርእሳነ መምህራን እና የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች ስለትምህርት እቅዱ ዝግጅት ክትትል እና የአፈጻጸም ግምገማ ጉዳይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ሰፋ ያለና የተብራራ ሀሳብ ለማግኘት የሚያስችልና አጥኚው ተጠኚውን ወደ ተፈለገው አቅጣጫ በመምራት ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ስለሚቻል ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለመጠቀም ተወስኗል፡፡

## 3.4 የጥናቱ ሂደት

ትክክለኛና አስተማማኝ የሆነ ጥናትና ምርምር ለመስራት ተጠኝውን ማህበረሰብና ባህሉን ማክበር፣ የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ማሳወቅ፣ የተሳታፊዎችን ይሁንታ ማግኘት የመሳሰሉት የምርምር ስነ-ምግባሮች ሊጠበቁ እንደሚገባ Dawson (2007) ይመክራሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በቅድሚያ ከትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር፣ ከመምህራንና ተማሪዎች የምርምሩን አላማ በማስረዳት ይሁንታ መልስ ስለተገኘ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በማስከተልም የጥናቱ ተተኳሪ ክፍሎች፣ መምህራንና ተማሪዎች እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ መጀመሪያ ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ምክትል ርእሳነ መምህራን የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛ ላይ የመምህራን ቃለ-መጠይቅ ተካሂዷል፡፡ቃለ-መጠይቆች ከተጠናቀቁ በኋላ በትምህርት ቤቶቹ የክፍል ዉስጥ ምልከታ ተደርጓል፡፡ በስተመጨረሻም የተዘጋጁት እቅዶች ከስርአቱ አኳያ በጥንቃቄ ተመርምረው ከተፈተሹ እና ትንታኔ ከተሰጠባቸው በኋላ ጥናቱ ተጠናቅቋል፡፡

## 3.5.የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚችላቸውን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ፣ ለዚሁ አላማ የሚውል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተመርጧል፡፡ ቀጥሎም ለዘርፉ ባለሙያዎች በማሳየትና ከአስተያየቱ በመነሳት ማሻሻያ ተደርጎ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የትምህርት ዕቅዳቸው እንዴት እንደተዘጋጀ በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ እቅዶች ላይ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል፤ከዚህ የተገኘው መረጃም መምህራን እቅዳቸውን በተገቢው መንገድ ማዘጋጀታቸውንና መተግበራቸውን መሰረት በማድረግ ሙያዊ ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለመምህራን፣ለትምህርት ክፍል ሃላፊዎች እና ለምክትል ረእሳነ መምህራን ቃለ-መጠይቅ ቀርቧል፡፡ በቃለ መጠይቁ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው በተገኘው መረጃ መሰረት የተሰበሰው መረጃ ከእቅድ ዝግጅት እና ትግበራ አንጻር በይዘት በይዘቱ ተደራጅቶ ጥናቱን በሚያግዝ መልኩ ተተንትኗል፡፡

በጥናቱ ከአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ውስጥ በገለጻ ትንታኔ መስጠት ተግባራዊ ሁኗል፡፡ አይነታዊ ምርምር አጥኚዉ መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ለአንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለጻዊ መንገድን ተከትሎ የሚካሄድ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተመራማሪው አንድን ችግር ይወስድና ውስን የሆኑ የችግሩን ባለቤቶች በመምረጥ ያነሳውን ችግር በጥልቀት

እና በስፋት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመዳሰስ መረጃዎችን የሚሰበሰብበት እና የሚተነተንበት ነው። በማለት ያለው እንዳወቅ (2009፤19) ገልጿል። ስለሆነም ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ የእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን የሚያትቱ ቃለ ነቢቦችን መሰረት በማድረግ በገለጻ እና በትንተና መልክ የቀረበ ሲሆን ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የሚገኘው መረጃ ደግሞ እንደ ተመሳስሎሹ ተደራጅቶ በገለፃ መልክ ተተንትኗል።

በክፍል ውስጥ ምልከታ በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን የመማር ማስተማር ሂደት ከእቅዱ አንጻር ምን እንደሚመስል ለማሳየት እለታዊ እቅዶቹ ከአመታዊው እና ሳምንታዊው ጋር ተጣጥመው መሄዳቸውን ለማየት መልከታ ተደርጓል። መምህራን የአማርኛ ቋንቋን ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ከተሰጠው የትምህርት ዓላማ ይዘት፤ የትምህርት መርጃ መሳሪያ እና የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ እና የአተገባበር ብቃት ለማየት ይቻል ዘንድ፤ ተገቢዉ የምልከታ መከታተያ ቅጽ የእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን የሚገለጹ ቃለ ነቢቦችን መሰረት በማድረግ በተገቢው ሁኔታ ተዘጋጅቶ፤ በየትምህርት ቤቶቹ በሚያስተምሩት መምህራን ላይ በመደበኛዉ የማስተማሪያ ወቅት ከያንዳንዱ መምህር በምልከታ የተገኘው መረጃ በስርዓቱ ተደረጅቶ በድግግሞሹ መሰረት በመቶኛ በማስቀመጥ ተገቢ ትንተና ተሰጥቶበታ‹ል።

በእንዳንዱ መረጃመሰብሰቢያ ዘዴ (የሰነድ ፍተሻ፣ ምልከታ፣ እና ቃለ መጠይቅ) የተገኘው መረጃ ጥናቱን በሚያግዝ መልኩ በሶስትዮሽ እየተሰናሰለ ለጥናቱ ተገቢ በሆነ መንገደ ተደርጅቶ አስፈላጊው ገለጻ ተከናውኗል።

## ምዕራፍ አራት፡- የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

### 4.1 የተጠኝዎች ዳራ

በዚህ ንዑስ ክፍል በናሙናነት ተመርጠው በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ መምህራን ግላዊ መረጃ የሚቀርብበት ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ተተኳሪ ያደረጋቸው አስራ ሁለት መምህራንን ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ መረጃ ሰብሳቢዋ ባደረገችው የቅርብ ክትትል አስሩንም መምህራን ያለ አንዳች ችግር መረጃ ለመስጠት ችለዋል፡፡ በመሆኑም መረጃውን በሚገባ ያጠናቀቁ እና የመለሱ ተጠኘዎች ግላዊ መረጃ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቶች ስም | የመምህራንብዛት | | | የትምህርትደረጃ | | | | የሰለጠኑበትየትምህርትአይነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድምር | ማስተር | ዲግሪ | ዲፕሎማ | ድምር | አብይ | ንዑስ |
| 1 | ኢሊያ ሁ/ደ/ት/ቤት | - | 2 | 2 | - | 1 | 1 | 2 | አማርኛ | - |
| 2 | መኮድ ሁ/ደ/ት/ቤት | 2 | - | 2 | - | 1 | 1 | 2 | አማርኛ | - |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ኢታንግ ሁ/ደ/ት/ቤት | 1 | 1 | 2 | - | 2 | - | 2 | አማርኛ | - |
| 4 | ባዝየል ሁ/ደ/ት/ቤ/ት | 1 | 1 | 2 | - | 2 | - | 2 | ስነ ዜጋ እና እንግሊዝኛ | - አማርኛ |
| 5 | አከዶ ሁ/ደ/ት/ቤ/ት | 1 | 1 | 2 | - | 2 | - | 2 | ባዮሎጅና ስነዜጋ | - |
| 6 | ጋምቤላ ሁ/ደ/ት/ቤት | - | 2 | 2 | 2 | - | - | 2 | አማርኛ | - |

ከቃለ መጠይቁ ተሰብስበው ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የሰፈሩት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት 5(አምስት) ወንዶችና 7(ሰባት) ሴቶች በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡ መምህራኑም 1(አንድ) በአማርኛ የማስተማር ስልጠና ያገኘ ሲሆን፣ 2 (ሁለቱ) የማስትርስ ድግሪ ፣ 4 (አራቱ) የመጀመሪያ ዲግሪ እና 2(ሁለቱ) በአማርኛ ቋንቋ ዲፕሎማ አላቸዉ፡፡ 1(አንድ) መምህር በእንግሊህኛ ቋንቋ አንዱ ደግሞ በባዮሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸዉ ሲሆን ሁለቱ መምህራንም በስነ ዜጋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸዉ መሆኑን ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ በተገኘውም መረጃ መሰረት አማርኛን በንዑስ ትምህርት መስክ ያጠናቀቀ አንድ መምህር ሲሆን እንግሊዘኛን በአብይ ትምህርት መስክ ያጠና ደግሞ 1(አንድ)፣ ባዮሎጂን በአብይ ትመህርት መስክ ያጠናቀቀ 1 (አንድ) ስነ ዜጋን በአብይ የትምህርት መስክ ያጠኑ ሁለት፣ ሲሆኑ ስድስቱ ግን በአብይ ብቻ ትምህርት መስክ አማርኛን ቋንቋ ያጠኑ ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ለጥናቱ አጥጋቢ የሆነ መረጃ ሰጥተዋል፡፡ በሚያስተምረው ትምህርት በበቂ ሁኔታ ዝግጀት ያለው እና በሙያው የሰለጠነ መምህር ስርአቱን የጠበቀ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅቶ ተገቢውን ክሂሎት እና ደረጃው የሚጠይቀውን እውቀት እና ልምድ ለማካፈል አይቸገርም፡፡

## 4.2 በተጠኝ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተገኙ መረጃዎች አሰባሰብ ሂደት

በመጀመሪያ መረጃ ወደ ምትሰበስብባቸው ትምህርት ቤቶች ለመምህራኑ ስልክ በመደወል ቀጠሮ ካስያዘች በኋላ በስድስቱም የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከጥቅምት አንድ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2011ዓ.ም ያለውን የትምህርት ዕቅዳቸውን እንዲያደራጁና እንዲሰጧት ፈቃደኛነታቸውን በመጠየቅ መልካም ፈቃዳቸውን በማግኘትና በስድስቱም ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ አስራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከእያንዳንዳቸው ከጥቅምት አንድ እከስ ሚያዚያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰሩትን የዕለታዊ/ ሳምንታዊ የትምህርት እቅድ ቅፆች በድምሩ 150 እቦታው ድረስ በአካል በመሄድ መረጃው ተሰብስቧል።

በመጀመሪያ የእለታዊ የትምህርት እቅዶቹ በእቅድ አወጣጥ/ዝግጅት ወቅት መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች/ዝርዝር ጉዳዮች ከቅርጽ እና ከይዘት አኳያ ማሟላተቸውን ለማረጋገጥ በእያንዳንዳቸው ላይ የሰነድ ፍተሸው ተከናወነ።

የሰነድ ፍተሻው ስከናወን የእለታዊ ትምህርት እቅድን በያንስ መሰረታዊ የሚባሉትን የእቅድ ይዘቶች (መግቢያ (Introduction)፤ቀደም ሲል የተማሩትን በማስታወስ የእለቱን ትምህርት ዋና ይዘት በማስተዋወቅ፤ማነቃቂያ (Warmup)፤ የእለቱን ተምህርት በቀና እና በተሳካ መልኩ ለማከናወን ይረዳ ዘንድ ለእለቱ ትምህርት አዘጋጅተው ንቁ የሚያደረጉ ነጥቦችን ማስቀመጥ፤አቅራቦት (Presentation)፤ ይዘቶችን ማስቀመጥ፣ ተማሪዎች ከይዘቶች ጋር በተያያዘ መልኩ ሊያከናውኗቸው የሚችለትን ተግባራት በግልጽ ማስቀመጥ፤ ምጋቤ ምላሽ (Feedback)፤ የእለቱን ትምህርት ለማገዝ መስጠት የሚችሉትን ምጋቤ ምላሽ መጠቆም፤ማጠቃለያ(Concluding Remarks)፤) የሚሉትን ነጥቦች መሰረት አድርጎ በማየት ነው። በሌላ መልኩ ከቅርብ ግዜ ወዲህ እነ ከኒግሀም (2009) የትምህርት እቅድ እርከኖችች (Lesson Plan Phases) በማለት በስምንት እርከኖች/ ደረጃዎች/ በመመደብ እንደሚከተለው ባቀረቡት መሰረት በማስተይየት የእቅድ ዝግጅቱ ምን እንደሚመስል በማስተያየት ነው። እነዚህም፣

እርከን አንድ፤ መግቢያ (Introduction) ፤
እርከን ሁለት፤መደላድል/ መሰረት (Foundation)
እርከን ሶስት፤ አዕምሮን ማነቃቃት (Brain Activation)

እርከን አራት፤ የአዲስ እውቀት / የእለታዊ መረጃ አካላት (Body of New Information)
እርከን አምስት፤ ግልጽ ማድረግ (Clarification)
እርከን ስድስት፤ ማለማመድ እና መከለስ (Practice and Review)
እርከን ሰባት የተናጥል (ግላዊ ልምምድ) (Independent Practice)
እርከን ስምንት፤ መደምደመያ (Closure)

የትምህርት እቅድ በአብዛኛው እና በመሰረታዊነት እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ከሞላ ጎደል በማካተት መቅረብ እንዳለበት እነ ከኒግሀም/ Cunnigham/ (2009) ፣ ኬንዝ ብያሬ (2010)/ Kenneth Beare/ (2018) በተሸሻለ መልኩ በመዘርዘር ይገልጹታል። አንድ መምህር የቱንም ያህል ልምድ እና እውቀት ቢኖረውም ለሚያስተምረው ጉዳይ በስርኣቱ የተደራጀ እቅድ ሊኖረው ይገባል በማለት በአጽንኦት ያስገነዝባሉ፡

በዚህ መሰረት እለታዊ የትምህርት እቅድ ዝግጅቶች ተፈትሸው ሁሉም በሚያስብል መልኩ በቅርጽም ይሁን በይዘት መስፈርቱን በትክክል አያሟሉም። እይንዳንዳቸው ለይስሙላ ያክል የቀረቡ ውስን ነጥቦችን ብቻ የያዙ  በኣንድ ገጽ ለአንድ ሳምንት የተዘጋጁ የእለታዊ ትምህርት እቅዶች ናቸው። በዚህ ሁኔታ ደግም ቋንቋውን በአግባቡ አስተምሮ ተፈላጊውን የቋንቋ ክሂሎች ለማስጨበጥ እና በቂ ውጤት ለማስመዝገብ አስቸጋሪ ነው።

ከዚህም በመቀጠል ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በእያንዳንዱ መምህር ከተዘጋጀው የእለታዊ እቅድ ውስጥ የሰፈረውን ዓላማ በሶስቱ የ ብሎም(Bloom) ታክሶኖሚ ቃለነቢቦች መሰረት ደርጅቶ በመከፋፈል ለማሳየት ተመደበ።  ማለትም አዕምሮአዊ ምድብ የሆኑትን በአንድ ምድብ በመለየትና በማስቀመጥ የራሱ የሆነ ኮድ በመስጠት፣ ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ የሆኑትን በአንድ ምድብ በመለየትና ስሜታዊ /አመለካከታዊ/ ምድብ የሆኑትን በአንድ ምድብ በመለየትና በማስቀመጥ የራሱ የሆነ ኮድ በመስጠት ከተቀመጠ በኋላ እያንዳንዱ እለታዊ እቅድ እንደገና ተተንትኗል።

ከዛም አዕምሮአዊ ምድብ የሆነውን እንደገና በስድስት ክፍሎች በመከፋፈል ማለትም እውቀት፣ ትርጉም፣  ወደ ተግባር መለወጥ፣ ትንተና፣ ግንባታና ግምገማ የሚያመለክተውን በእያንዳንዱ ት/ቤት እና በእያንዳንዱ መምህር በመለየትና በማስቀመጥ እንዲሁም ስሜታዊ/ አመለካከታዊ ምድብ የሚገልፀውን ደግሞ በአምስት ክፍሎች በመክፈል ማለትም መቀበል፣ መመለስ፣ ዋጋ

መስጠት፣ ድርጅትና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት የሚያመለክተውን በእያንዳንዱ ት/ቤትና መምህር ተለይቶ ከተቀመጠ በኋላ በመጨረሻም ላይ ደግሞ የይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ የሆነውን ደግሞ ከቋንቋ ክፍሎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከፅህፈት ክሂሎች በመመደብ ተቀምጧል።በመጨረሻም ከእያንዳንዱ ትመህርት ቤት ከአስራ ሁለቱም መምህራን የተገኘውን መረጃ በገለፃ እና በሰንጠረዥ ተለይቶ ከተቀመጠ በኋላ የስድስቱንም ትምህርት ቤት መረጃ ከአጠቃላይ መረጃ ከሰጡት መምህራን ጋር በማቀናጀት ሶስቱንም ምድብ ለየብቻቸው በመለየት እንደገና በማቀናጀት በሰንጠረዥ መልክ ከቀረበ በኋላ አጠቃላይ የተገኘውን ውጤት በገለፃና በአሀዝ በተለያዩ ሰንጠረዦች ቀርቧል።

### 4.2.1 አጠቃላይ የተጠኚ ትምህርት ቤቶች እቅድ አዘገጃጀት ዳሰሳ

በዚህ ንኡስ ርዕስ ሰር በተጠኝ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ የሚዘጋጁ እለታዊ የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት እቅዶች አላማ አነዳደፍ፣ ከእቅድ አዘገጃጀት ቅርጽኣንጻር እና ከብሉምስ ተክሶኖሚ ዝርዝር የእቅድ አዘገጃጀት መስፈርቶች አኳያ እየታዩ እያንዳንዳቸው ተፈትሸዋል:: በየትምህርት ቤቶቹ የሚተገበሩት እለታዊ እቅዶች የአላማ አነዳደፍ ፍተሻ በሚከተለው መልኩ ተዘረዝረው ቀርበዋል።

**1. ኤሊያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ**

**መምህር አንድ ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge**)**

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ይገልፃሉ።
- ስለ ቋንቋ ምንነት ይናገራሉ።
- ስለ ቋንቋ ባህሪያት ይገልፃሉ።
- ሀሳባቸውን የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ይናገራሉ።
- የስነ-ፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይዘረዝራሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ሀረጋትን በራሳቸው አባባል ያብራራሉ።

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርቡላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።

- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁትን ሀሳቦች በማውጣት ይፅፋሉ፡፡
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁትን ሀሳቦች በማስታወሻ ይይዛሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።
- የሚነበብላቸውን ታሪክ አዳምጠው ጥያቄ ይመልሳሉ።
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩ ዐ. ነገሮችን ያያይዛሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሑፍን አጥንተው በቃል ያቀርባሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ. ነገር አስገብተው ፅፈው ያሳያሉ።
- የስንኞችንና የሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ፅፈው ያሳያሉ።
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይሰበስባሉ።
- ከማስታወሻ ላይ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።

ከታየው እቅድ ለመረዳት እንደተቻለው መረዳት (Comprehension) ትንተና (Analysis) ፣ግንባታ (Synthesis) እና ግምገማን (Evaluation) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge**)**

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካበበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ።
- ስለ ስነቃል ምንነት ናባህሪያት የተረዱትን ይናገራሉ።
- የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ።
- የስነ ፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይገልፃሉ።
- የተውኔቱን ዋና ዋና ሀሳቦች በድርጊት ቅደም ተከተል ይገልፃሉ።

- የተለያዩ ሀረጋትን ፍች ይተነትናሉ።

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁ ሐሳቦችን በማስታወሻ ይይዛሉ።
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያደርጋሉ።
- ከቀረበላቸው ምንባብበ ምክንያትና በውጤት የተገለፁት ሀሳቦችን በማውጣት ይይዛሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።
- የሚያነበብላቸውን ፅሑፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩ ዐ. ነገሮች ያያይዛሉ።
- የያዙትን ማስታወሻ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሁፍን አጥንተው በቃል ያቀርባሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ. ነገር አስገብተው ይፅፋሉ።
- የስንኞችን ናሐረጎችን ሀሳብበ ራሳቸው አገላለፅያ ብራራሉ።
- የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ይሰበስባሉ።

ከታየዉ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ መረዳት Comprehension) ፣ትንተና (Analysis) ፣ግንባታ እና ግምግማ የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

## 2. መኮድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

**መምህር አንድ ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge**)**

- ስለ ቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይናገራሉ።
- የስነ-ቃል  ምንነትና ባህሪያት ይገልፃሉ።

- የስነ-ቃል ተግባራትን ይናገራሉ።
- የነፃ እና የጥገኛ ምዕላድን ምንነት ይናገራሉ።
- የቅጥያ ምንነትና አገልግሎት ይገልፃሉ።
- የስነ-ፅሑፍን ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ይገልፃሉ።
- ስለ ዘዬ አፈጣጠር ይገልፃሉ።
- የቃላትን አገባበዊ ፍች ይገልፃሉ።
- የአንቀፅ ምንነት ይገልፃሉ።
- የነጠላ ሰረዝና የድርብ ሰረዝ ምንነትን ይገልፃሉ።
- አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን፣ የአስተዋፅኦ ምንነትንና አገልግሎትን ይገልፃሉ።
- የቃላት እማሬያዊናፍካሪያዊፍቾይገልፃሉ።
- የግጥሙን ፍሬ ሀሳብና ዐ. ነገር ክፍሎችን ይገልፃሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትንና የዘይቤ አይነቶችን ይናገራል።

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- የውይይት መመሪያ ተጠቅመው ይወያያሉ።
- የተሰጣቸውን ጥያቄዎች መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎች ይሰራሉ።

ትንተና (Analysis)

- የቃል ክፍሎች ይገልፃሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትና የዘይቤ አይነቶችን ይናገራሉ።

ከታየዉ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ መረዳት (Comprehension) ፣ ግንባታ (Synthesis) እና ግምገማ (Evaluation) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge**)**

- የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይረዳሉ።

- የማስታወሻ አነጋገር ስልትን ይናገራሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- የሐረግ ምንነትና አይነቶችን ያውቃሉ።
- የምዕላድ ምንነት ለይተው ያውቃሉ።
- የግጥምና የዝርው ፅሑፍ አነባበብ ስልትን ለይተው ያውቃሉ።
- የስነ-ፅሑፍ ምንነት ያውቃሉ።

መረዳት (Comprehension)

- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን ይገልፃሉ።

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።
- የቤተ-መፅሐፍት መመሪያን ተጠቅመው ቤተ-መፅሐፍት ይጠቀማሉ።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- ዘይቤያዊ ንግግሮችን ያውቃሉ፤ ይጠቀማሉ።
- የተሰጣቸውን የመልመጃ ጥያቄዎች ይሰራሉ።
- የክርክርን መመሪያ ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።

ትንተና (Analysis)

- ያልተፃፈውን ስነ-ፅሁፍ ስነ-ቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ።
- የቃል ክፍሎችን ለይተው ያውቃሉ።
- የስነቃል አይነቶችን ይተነትናሉ።

ከታየዉ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ግንባታ (Synthesis) እና ግምገማ (Evaluation) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**3.ኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ**

**መምህር አንድ ያዘጋችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge)

- የቋንቋ ምንነትን ይገነዘባሉ፣ የቋንቋ አገልግሎቶችን ይዘረዝራሉ።
- ከዐ. ነገር ውስጥ ምክንያትና ውጤት ይለያሉ።
- የስነ-ቃልን ምንነት ይገነዘባሉ፤ የስነ-ቃል አይነቶችን ይለያሉ።
- ነፃና ጥገኛ ምዕላድን ይለያሉ።
- የዝርውና የግጥም አነባበብ ስልትን ለይተው ያውቃሉ።
- የስነ-ፅሑፍን ምንነት ይለያሉ።
- ስለ ምዕላድ ምንነትና አይነቶችን ይለያሉ።
- የነጠብጣብና ድርብ ሰረዝን አገልግሎት ይለያሉ።
- የድርሰት አይነቶችን ይለያሉ።
- የአጭር ልቦለድን ምንነት ይገነዘባሉ።
- የሐረግ አይነቶችን ይለያሉ፣ የልቦለድ አለባውያንን ይዘረዝራሉ።
- የስነ- ፅሑፍ ምንነትና ስነ-ፅሑፍ ያልሆኑ ፅሑፎችን ይለያሉ።
- የግጥምም ምንነት ይገነዘባሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላት ይገነዘባሉ።

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- የማስታወሻ አያያዝን ይለማመዳሉ።
- የግጥም አነባበብ ስልት በመረዳት ያነባሉ።

ትንተና (Analysis)

- የቃል ክፍሎችን ይዘረዝሉ።
- የዘይቤ አይነቶችን ይዘረዝራሉ።

ከታየዉ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ መረዳት (Comprehension) ፣ ግንባታ (Synthesis) እና ግምገማ (Evaluation) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት ያዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge)

- የቋንቋ ምንነትን ይረዳሉ፡፡
- የቃላትን አገባባዊ ፍችና ቀጥተኛ ፍችን፤ የማስታወሻ አያያዝን ለይተው ይረዳሉ፡፡
- የቃላት መጥበቅና መላላት፣ የአስረጂና የውይይት ምንነትን ለይተው ይገልፃሉ፡፡
- ምክንያትና ውጤትን ለይተው ያውቃሉ፡፡
- የስነ-ቃል ምንነትን፣ ባህሪይንና ተግባር በመረጃ አስደግፈው ያብራራሉ፡፡
- የስነ-ፅሑፍ ምንነትንና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ለይተው ይገልፃሉ፡፡
- የቤተ-መፅሕፍት አጠቃቀም መመሪያንና የውይይት መመሪያን ይናገራሉ፡፡
- የአንቀፅን፣የነጠብጣብ፣የድርብ ሰረዝና የተራኪ ድርሰት ምንነትን ለይተው ያውቃሉ፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችንና የልቦለድን ቅደም ተከተላዊ ድርጊት ይናገራሉ፡፡
- የአያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት፣ የአስተዋፅኦ ምንነትና ጥቅሞችን ለይተው ያውቃሉ፡፡
- የሐረግን፣ የቃል ክፍሎችን፣ የልቦለድ ምንነትና የልቦለድ አለባውያንን ለይተው ይገልፃል፡፡
- የግጥም ሙያዊ ቃላት፣ የግጥምና የዝርው ፅሑፍ አነባበብና የዘይቤ አይነቶችን ለይተው ያውቃል፡፡
- የተውኔት አለባውያን ምንነትና አለባውያንን ለይተው ይገልፃሉ፡፡
- በስራ ደብዳቤ ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦች፤ ከቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላድን መለየትና ግጥማዊ ዘይቤን ለይተው ይናገራሉ፡፡

መረዳት (Comprehension)

- ከግሶች ሌሎች ግሶችን በመመስረትና የምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ይገልፃሉ፡፡

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- የግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን በመስራትና የዐ.ነገር ክፍሎችን ለይተው ይፅፋሉ፡፡
- የቃላት መጥበቅና ላልተው ሲነበቡ የሚኖረውን የፍች ልዩነት በመልመጃ ሰርተው ያሳያሉ፡፡

ከታየዉ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ትንተና (Analysis) ግንባታ (Synthesis) ግምገማ (Evaluation) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

## 4. ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት እቅድ ዝግጅት

## መምህር አንድ የዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge**)**

- ስለ ቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይናገራሉ።
- የዘዬ አፈጣጠርን በመለየት ይገልፃሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትን ይገልፃሉ።
- የቃል ክፍሎችን ለይተው ያውቃሉ።
- የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ።
- የግጥምና የዝርው አነባበብ ስልትን ለይተው ያውቃሉ።
- የስነ-ፅሑፍን ምንነት ያውቃሉ።
- አጠቃላይ የምዕራፉን ሀሳብ ይገልፃሉ።
- የምሳሌያዊ አነጋገሩን ሀሳብ ይገልፃሉ።
- አንቀፁን መሰረት አድርገው መልመጃዎቹን ይሰራሉ፤ ድርሰቱን ይገልፃሉ።

መረዳት (Comprehension)

- የቃላትን እማሪያዊና ፍካሬያዊ  ፍችን ይገልፃሉ።

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- የቀረቡትን መልመጃዎች ይሰራሉ።
- የቀረቡትን የግጥም አይነቶች ያነባሉ።
- አያያዥ ቃላትን በዐ. ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።
- ቃላትን በዐ.ነገር ውስጥ በሚኖራቸው ትርጉም ላይ ይወያያሉ።

- የምክንያትና የውጤት ጥምረትን አውቀው ይጠቀሙበታል።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- የተሰጣቸውን ጥያቄዎች መሰረት አድርገው የፈተናውን ጥያቄዎች ይሰራሉ።

ከታየዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ትንተና (Analysis) ፣ ግንባታ (Synthesis) እና ግምገማ (Evaluation) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት ያዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

አዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain)

እውቀት (Knowledge**)**

- የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይረዳሉ።
- የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ።
- በተማሩት መሰረት ቢጠየቁ ምላሽ ይገልፃሉ።
- የስነ-ፅሑፍ ምንነትን ያውቃሉ።
- ለስነ-ፅሑፍ መኖር ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይገልፃሉ።
- የቃላት አብይ የሆነውን እማሬያዊ ፍችን ያውቃሉ።
- የሐረግ ምንነት ያውቃሉ።
- የሐረግ አይነቶችን ያውቃሉ።
- የግጥምና የዝርው ፅሑፍ ልዩነትን ያውቃሉ።
- የቃል ክፍሎችን ለይተው ያውቃሉ።
- የቃላትን ፍካሬያዊ ፍች ያውቃሉ።
- ልቦለድ ምን እንደሆነ ያስረዳሉ ፣ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች በተማሩት መሰረት መልስ ይሰጣሉ፡

ወደ ተግባር መለወጥ (Application)

- የምክንያትና የውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ለሚጠየቁት ጥያቄ በተማሩት መሰረት ምላሽ ይሰጣሉ፣ገለፃ ያደርጋሉ፣ ያስረዳሉ።

- በተማሩት መሰረት ቢጠየቁ መልስ ይሰጣሉ፣ያስረዳሉ፣ያብራራሉ።
- የቤተ-መፅሕፍት መመሪያን ተከትለው ቤተ-መፅሕፍት ይጠቀማሉ።

ትንተና (Analysis)

- የቃል ክፍሎችን ለይተው ይዘረዝራሉ።
- የስነ-ቃል አይነቶችን ይተነትናሉ።

ከታየዉ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ መረዳት (Comprehension) ፣ግንባታ (Synthesis) እና ግምገማ (Evaluation) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በትግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

### 5. ባዝየል ሁለትኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

በተደረገዉ ሰነድ ምርመራ፣ቃለመጠይቅ እና ምልከታ በባዝየል ሁለተኛ ትምህርት ቤት እለታዊም ሆነ ዓመታዊ የትምህርት እቅድ እንደማይዘጋዘጅ ተረጋግጧል።

### 6. አከዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

ቤት በአከዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማየት እንደተቻለዉ ምንም ዓይነት የትምህርት እቅድ እንደማይዘጋጅ በተደረገዉ ሰነድ ፍተሻ፣ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ተረጋግጧል፡

### 1. ኢሊያ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

**መምህር አንድ ያዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

የማዳመጥ ክሂል

- ከሚነበብላቸው ታሪክ ተነስተው ጥያቄ ይመልሳሉ።
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁ ሀሳቦችን በማስታወሻ ይይዛሉ።

የንግግር ክሂል

- ከምንባቡ የወጡ ሐረጋትን በራሳቸው አባባል ያብራራሉ።
- የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ።
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርላቡቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሁፍን አጥንተው በቃል ያብራራሉ።
- የተውኔት አለባውያን ምንነት በሚመለከት ይወያያሉ።

- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።

የንባብ ክሂል

- ስለ ቋንቋ ምንነት የተረዱትን ከምንባቡ ይናገራሉ።
- ከምንባቡ ውስጥ ስለ ቋንቋ ባህሪያት የተረዱትን ይናገራሉ።
- የተውኔቱን ዋና ዋና ሀሳቦች በድርጊት ቅደም ተከተል ይገለፃሉ።
- ከምንባቡ ውስጥ የስነፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያትየ ሆኑ ነጥቦችን ይዘረዝራሉ።
- ከምንባቡ ውስጥ የወጡትን ስንኞችና ሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ያብራራሉ።
- ከምንባቡ ውስጥ የቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ።

የፅህፈት ክሂል

- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩት ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ።
- ከቀረበላቸው ምንባብበ ምክንያትና በውጤት የተገለፁትን ሀሳቦች በማውጣት ይፅፋሉ።
- የያዙትን ማስታወሻ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ዐ.ነገር ሰርተው ፅፈው ያሳያሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ.ነገር አስገብተው ፅፈው ያሳያሉ።

**መምህር ሁለት ያዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

የማዳመጥ ክሂል

- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁ ሀሳቦችን በማውጣት ይፅፋሉ።
- የሚነበብላቸውን ፅሁፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።

የንግግር ክሂል

- ከምንባቡ የወጡ ሐረጋትን በራሳቸው አባባል ያብራራሉ።
- የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ።

- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርቡላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሑፍን አጥንተው በቃል ያቀርባሉ።
- የተውኔት አለባውያንን ምንነት በሚመለከት ይወያያሉ።
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።

የንባብ ክሂል

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ።
- ስለ ቋንቋ ምንነትና ባህረያት ያነበቡትን ይናገራሉ።
- የስነ -ፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑትን ነጥቦች ይዘረዝራሉ።
- የቃላትን አገባበዋ ፍች ይሰጣሉ።
- የስንኞችንና ሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ያብራራሉ።
- የተውኔትን ዋና ዋና ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ያብራራሉ።

የፅህፈት ክሂል

- ከቀረበላቸው ምንባብ በምክንያትና በውጤት የተገለፁት ሀሳቦችን በማውጣት ይፅፋሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ዐ.ነገር ሰርተው ያሳያሉ።
- የያዙትን ማስታወሻ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ዐ.ነገር ሰርተው ያሳያሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ.ነገር አስገብተው ፅፈው ያሳያሉ።

2. **መኮድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ**

**መምህር አንድ ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

የንግግር ክሂል

- ስለ ቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይናገራሉ።

የፅህፈት ክሂል

- የተሰጣቸውን ጥያቄዎች መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎች ይሰራሉ።

ከታየዉ እለታዊ እቅድ ለመረዳት እንደሚቻለዉ የማዳመጥ እና የንባብ ክሂል የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

የንግግር ክሂል

የማስይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

- የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ፡

የፅህፈት ክሂል

- የተሰጣቸውን ጥያቄዎች ፅፈው ይሰራሉ።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።

ከታየዉ እለታዊ እቅድ መረዳት እንደሚቻለዉ የማዳመጥ እና የንባብ ክሂል የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

3. **ኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እቅድ ዝግጅት ፍተሻ**

**መምህር አንድ ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

የንባብ ክሂል

- የግጥምን አነባበብ ስልት በመረዳት ያነባሉ።
- የአጭርል በለድን ቅደም ተከተላዊ ሂደት ከምንባቡ ውስጥ ያነባሉ።

ከታየዉ እለታዊ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ የማዳመጥ ፣የንግግር እና የፅህፈት ክሂል የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

የንግግር ክሂል

- የቤተ-መፅሕፍትን አጠቃቀም መመሪያና የውይይት መመሪያን ይናገራሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችንናየ ልበለድ ቅደም ተከተላዊ ድርጊት ይናገራሉ።

- በስራ ደብዳቤ ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦች፣ ከቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላድን መለየትና ግጥማዊ ዘይቤን ለይተው ይናገራሉ።

የፅህፈት ክሂል

- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ዐ.ነገር ሰርተው ፅፈው ያሳያሉ።

ከታየዉ እለታቂ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ የማዳመጥ እና የንባብ ክሂልን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

## 4. ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

**መምህር አንድ ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት አቅድ**

ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

የፅህፈት ክሂል

- የተሰጣቸውን ጥያቄዎች መሰረት አድርገው የፈተናውን ጥያቄዎች ይሰራሉ።

ከታየዉ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ የማዳመጥ ፣ የንግግር እና የንባብ ክሂልን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት የዘጋጀዉ የትምህርት እቅድ**

ይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psycomoter domain)

የንግግር ክሂል

- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።

የንባብ ክሂል

- ከምንባቡ ውስጥ የቋንቋን ምንነትና አገልግሎት ይናገራሉ።

የፅህፈት ክሂል

- የተሰጣቸውን ጥያቄዎች መሰረት አድርገው የፈተናውን ጥያቄዎች ይሰራሉ።

ከታየዉ እቅድ ለማረጋገጥ እንደተቻለዉ የማዳመጥ ክሂል የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

## 5. ባዝየል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

በተደረገዉ ሰነድ ፍተሸ ፣ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ መሰረት በባዝየል ሁለትኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምንም ዓይነት የትምህርት እቅድ እንደማይታቀድ ተረጋግጧል፤በክሂሎታዊ ምድብ ስርም የታቀደ /የተሰራ/ ምንም ነገር የለም።

## 6. አከዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

በተደረገዉ ሰነድ ፍተሸ ፣ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ መሰረት በአከዶ ሁለትኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምንም ዓይነት የትምህርት እቅድ እንደማይታቀድ ተረጋግጧል፤በክሂሎታዊ ምድብ ስርም የታቀደ /የተሰራ/ ምንም ነገር የለም።

## 1. ኢሊያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእቅድ ዝግጅት ፍተሻ

**መምህር አንድ የዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

**ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)**

መቀበል (Receiving)

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ይገልፃሉ።
- ስለ ቋንቋ ምንነት ይናገራሉ።
- ስለ ቋንቋ ባህሪያት ይገልፃሉ።
- ሀሳባቸውን የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ይናገራሉ።
- የስነ-ፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይዘረዝራሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ሀረጋትን በራሳቸው አባባል ያብራራሉ።
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁትን ሀሳቦች በማውጣት ይፅፋሉ።
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁትን ሀሳቦች በማስታወሻ ይይዛሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።

- የሚነበብላቸውን ታሪክ አዳምጠው ጥያቄ ይመልሳሉ።
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩ ዐ. ነገሮችን ያያይዛሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሑፍን አጥንተው በቃል ያቀርባሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ. ነገር አስገብተው ፅፈው ያሳያሉ።
- የስንኞችንና የሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ፅፈው ያሳያሉ።
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይሰበስባሉ።
- ከማስታወሻ ላይ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።

መመለስ (Responding)

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ይገልፃሉ።
- ስለ ቋንቋ ምንነት ይናገራሉ።
- ስለ ቋንቋ ባህሪያት ይገልፃሉ።
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁትን ሀሳቦች በማውጣት ይፅፋሉ።
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁትን ሀሳቦች በማስታወሻ ይይዛሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።
- የሚነበብላቸውን ታሪክ አዳምጠው ጥያቄ ይመልሳሉ።
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩ ዐ. ነገሮችን ያያይዛሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሑፍን አጥንተው በቃል ያቀርባሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ. ነገር አስገብተው ፅፈው ያሳያሉ።
- የስንኞችንና የሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ፅፈው ያሳያሉ።
- ከማስታወሻ ላይ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።
- ሀሳባቸውን የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ይናገራሉ።
- የስነ-ፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይዘረዝራሉ።

- ከምንባቡ የወጡ ሀረጋትን በራሳቸው አባባል ያብራራሉ፡፡
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርቡላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ፡፡
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ፡፡

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ፡፡
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ፡፡
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ፡፡
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሑፍን አጥንተው በቃል ይቀርባሉ፡፡
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ፡፡

ከታየዉ እለታዊ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም፡፡

**መምህር ሁለት ያዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

**ስሜታዊ ምድብ (Affective domain**)

መቀበል (Receiving)

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካበበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ፡፡
- ስለ ስነ ቃል ምንነትና ባህሪያት የተረዱትን ይናገራሉ፡፡
- የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፡፡
- የስ ነፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይገልፃሉ፡፡
- የተውኔቱን ዋና ዋና ሀሳቦች በድርጊት ቅደም ተከተል ይገልፃሉ፡፡
- የተለያዩ ሀረጋትን ፍች ይተነትናሉ፡፡
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁ ሐሳቦችን በማስታወሻ ይይዛሉ፡፡
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያደርጋሉ፡፡

- ከቀረበላቸው ምንባብ በምክንያትና በውጤት የተገለፁ ሀሳቦችን በማውጣት ይይዛሉ።
- የያዙትን ማስታወሻ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።
- የሚያነበብላቸውን ፅሑፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩ ዐ. ነገሮች ያያይዛሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሁፍን አጥንተው በቃል በቃል ያቀርባሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ. ነገር አስገብተው ይፅፋሉ።
- የስንኞችንና ሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ያብራራሉ።
- የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ይሰበስባሉ።

መመለስ (Responding)

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካበበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ።
- ስለ ስነ ቃል ምንነትና ባህሪያት የተረዱትን ይናገራሉ።
- የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ።
- የስነ ፅሑፍ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይገልፃሉ።
- የተውኔቱን ዋና ዋና ሀሳቦች በድርጊት ቅደም ተከተል ይገልፃሉ።
- የተለያዩ ሀረጋትን ፍች ይተነትናሉ።
- ከሚያዳምጡት ፅሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለፁ ሐሳቦችን በማስታወሻ ይይዛሉ።
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያደርጋሉ።
- ከቀረበላቸው ምንባብ በምክንያትና በውጤት የተገለፁት ሀሳቦችን በማውጣት ይይዛሉ።
- የያዙትን ማስታወሻ ተሞርኩዘው ያነበቡትን አቀናብረው ይፅፋሉ።
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።
- የሚያነበብላቸውን ፅሑፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።

- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩ ዐ. ነገሮች ያያይዛሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሁፍን አጥንተው በቃል በቃል ያቀርባሉ።
- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐ. ነገር አስገብተው ይፅፋሉ።
- የስንኞችን ናሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ ያብራራሉ።

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ።
- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።
- ግጥምን ወይም ዝርው ፅሑፍን አጥንተው በቃል ይቀርባሉ።
- ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ።

ከታየዉ እለታዊ ለመረዳት እንደተቻለዉ ድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**2. መኮድ ሁለተኛ ደረጃ ትመህርት ቤት የትምህርት እቅድ ዝግጅት ፍተሻ**

**መምህር አንድ ያዘጋጀዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)

መቀበል (Receiving)

- ስለ ቋንቋ  ምንነትና አገልግሎት ይናገራሉ።
- ስለ ዘዬ አፈጣጠር ይገልፃሉ።
- የቃላትን አገባበዊ ፍች ይገልፃሉ።
- የስነ-ቃል ምንነትና ባህሪያት ይገልፃሉ።
- የስነ-ቃል ተግባራትን ይናገራሉ።
- የነፃ እና የጥገኛ ምዕላድን ምንነት ይናገራሉ።
- የቅጥያ ምንነትና አገልግሎት ይገልፃሉ።
- የስነ-ፅሑፍን ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ይገልፃሉ።
- የአንቀፅ ምንነት ይገልፃሉ።

- የነጠላ ሰረዝና የድርብ ሰረዝ ምንነትን ይገልፃሉ።
- አያያዥና መሸጋገሪ ያቃላትን፣ የአስተዋፅኦ ምንነትንና አገልግሎትን ይገልፃሉ።
- የቃላት እማሬያዊና ፍካሪያዊ ፍች ይገልፃሉ።
- የግጥሙን ፍሬ ሀሳብና ዐ. ነገር ክፍሎችን ይገልፃሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትንና የዘይቤ አይነቶችን ይናገራል።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- የቃል ክፍሎች ይገልፃሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትና የዘይቤ አይነቶችን ይናገራሉ።

መመለስ (Responding)

- ስለ ቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይናገራሉ።
- ስለ ዘዬ አፈጣጠር ይገልፃሉ።
- የቃላትን አገባበዊ ፍች ይገልፃሉ።
- የስነ-ቃል ምንነትና ባህሪያት ይገልፃሉ።
- የስነ-ቃል ተግባራትን ይናገራሉ።
- የነፃ እና የጥገኛ ምዕላድን ምንነት ይናገራሉ።
- የቅጥያ ምንነትና አገልግሎት ይገልፃሉ።
- የስነ-ፅሑፍን ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ይገልፃሉ።
- የአንቀፅ ምንነት ይገልፃሉ።
- የነጠላ ሰረዝና የድርብ ሰረዝ ምንነትን ይገልፃሉ።
- አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን፣ የአስተዋፅኦ ምንነትንና አገልግሎትን ይገልፃሉ።
- የቃላት እማሬያዊና ፍካሪያዊ ፍች ይገልፃሉ።
- የግጥሙን ፍሬ ሀሳብና የዐ. ነገር ክፍሎችን ይገልፃሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትንና የዘይቤ አይነቶችን ይናገራል።
- የውይይት መመሪያ ተጠቅመው ይወያያሉ።
- የቃል ክፍሎች ይገልፃሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትና የዘይቤ አይነቶችን ይናገራሉ።

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።
- የተሰጣቸውን ጥያቄዎች መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።

ከታየዉ እለታዊ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት የዘጋጀዉ እልታዊ የትምህርት እቅድ**

ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)

መቀበል (Receiving)

- የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረትን አውቀው ይጠቀሙበታል።
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን ይገልፃሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።
- የቤተ-መፅሕፍት መመሪያን ተጠቅመው ቤተ-መፅሕፍት ይጠቀማሉ።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- ያልተፃፈውን ስነ-ፅሁፍ ስነ-ቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ።
- የስነቃል አይነቶችን ይተነትናሉ።

መመለስ (Responding)

- የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን ይገልፃሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- ዘይቤያዊ ንግግሮችን ያውቃሉ፤ ይጠቀማሉ።

- ያልተፃፈውን ስነ-ፅሁፍ ስነ-ቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ።
- የስነቃል አይነቶችን ይተነትናሉ።

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።
- የቤተ-መፅሕፍት መመሪያን ተጠቅመው ቤተ-መፅሕፍት ይጠቀማሉ።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- ዘይቤያዊ ንግግሮችን ያውቃሉ፤ ይጠቀማሉ፡
- ያልተፃፈውን ስነ-ፅሁፍ ስነ-ቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ።

ከታየዉ እለታዊ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**3. ኢታንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት እቅድ ዝግጅት ፍተሻ መምህር አንድ የዘጋጀዉ እልታዊ የትምህርት እቅድ**

ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)

መቀበል (Receiving)

- የቋንቋ ምንነትን ይገነዘባሉ፣ የቋንቋ አገልግሎቶችን ይዘረዝራሉ።
- የስነቃል ዘርፎችን፣ ባህሪያትንና ተግባራትን ይገልፃሉ።
- የአጭር ልቦለድን ምንነት ይገነዘባሉ።
- የሐረግ አይነቶችን ይለያሉ፣ የልቦለድ አለባውያንን ይዘረዝራሉ።
- የዐ. ነገር ክፍሎች፣ የግጥም ሙያዊ ቃላት ይገነዘባሉ።
- የማስታወሻ አያያዝን ይለማመዳሉ።
- የቃል ክፍሎችን ይዘረዝራሉ።
- የዘይቤ አይነቶችን ይዘረዝራሉ።

መመለስ (Responding)

- የቋንቋ ምንነትን ይገነዘባሉ፣ የቋንቋ አገልግሎቶችን ይዘረዝራሉ።

- የስነቃል ዘርፎችን፣ ባህሪያትንና ተግባራትን ይገልፃሉ።
- የአጭር ልቦለድን ምንነት ይገነዘባሉ።
- የሐረግ አይነቶችን ይለያሉ፣ የልቦለድ አለባውያንን ይዘረዝራሉ።
- የዐ. ነገር ክፍሎች፣ የግጥም ሙያዊ ቃላት ይገነዘባሉ።
- የማስታወሻ አያያዝን ይለማመዳሉ።
- የቃል ክፍሎችን ይዘረዝራሉ።
- የዘይቤ አይነቶችን ይዘረዝራሉ።

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- የማስታወሻ አያያዝን ይለማመዳሉ።
- የግጥም አነባበብ ስልት በመረዳት ያነባሉ።

ከታየዉ እለታዊ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**መምህር ሁለት የዘጋጀዉ እልታዊ የትምህርት እቅድ**

ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)

መቀበል (Receiving)

- የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረትን አውቀው ይጠቀሙበታል።
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን ይገልፃሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።
- የቤተ-መፅሕፍት መመሪያን ተጠቅመው ቤተ-መፅሕፍት ይጠቀማሉ።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- ያልተፃፈውን ስነ-ፅሁፍ ስነ-ቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ።
- የስነቃል አይነቶችን ይተነትናሉ።

መመለስ (Responding)

- የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን ይገልፃሉ።
- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- ዘይቤያዊ ንግግሮችን ያውቃሉ፤ ይጠቀማሉ።
- ያልተፃፈውን ስነ-ፅሁፍ ስነ-ቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ።
- የስነቃል አይነቶችን ይተነትናሉ።

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- የምክንያትና ውጤት ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል።
- ከዚህ በፊት የተማሩትን መሰረት አድርገው የፈተና ጥያቄዎችን ይሰራሉ።
- የቤተ-መፅሕፍት መመሪያን ተጠቅመው ቤተ-መፅሕፍት ይጠቀማሉ።
- የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ።
- ዘይቤያዊ ንግግሮችን ያውቃሉ፤ ይጠቀማሉ፡
- ያልተፃፈውን ስነ-ፅሁፍ ስነ-ቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ።

ከታየዉ እለታዊ እቅድ ለመረዳት እንደተቻለዉ ድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም።

**4. ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት እቅድ ዝግጅት ፍተሻ**

**መምህር አንድ የዘጋጀችዉ እልታዊ የትምህርት እቅድ**

ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)

መቀበል (Receiving)

- የቃላት መጥበቅና መላላት፣ የአስረጂና የውይይት ምንነትን ለይተው ይገልፃሉ።
- የስነ-ፅሑፍ ምንነትንና ለመኖሩም ክንያት የሆኑ ነገሮችን ለይተው ይገልፃሉ።

- የቤተ-መፅሕፍት አጠቃቀም መመሪያንና የውይይት መመሪያን ይናገራሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችንና የልቦለድን ቅደም ተከተላዊ ድርጊት ይናገራሉ።
- የሐረግን፣ የቃል ክፍሎችን፣ የልቦለድ ምንነትና የልቦለድ አላባውያንን ለይተው ይገልፃል።
- የተውኔት አላባውያን ምንነትና አላባውያንን ለይተው ይገልፃሉ።
- በስራ ደብዳቤ ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦች፤ ከቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላድን መለየትና ግጥማዊ ዘይቤን ለይተው ይናገራሉ።
- ከግሶች ሌሎች ግሶችን በመመስረትና የምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ይገልፃሉ።
- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ።
- ከግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን በመስራትና የዐ.ነገር ክፍሎችን ለይተው ይፅፋሉ።
- የቃላት መጥበቅና ላልተው ሲነበቡ የሚኖረውን የፍች ልዩነት በመልመጃ ሰርተው ያሳያሉ።

መመለስ (Responding)

- የቃላት መጥበቅና መላላት፣ የአስረጂና የውይይት ምንነትን ለይተው ይገልፃሉ።
- የስነ-ፅሑፍ ምንነትንና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ለይተው ይገልፃሉ።
- የቤተ-መፅሕፍት አጠቃቀም መመሪያንና የውይይት መመሪያን ይናገራሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችንና የልቦለድን ቅደም ተከተላዊ ድርጊት ይናገራሉ።
- የሐረግን፣የቃል ክፍሎችን፣ የልቦለድ ምንነትና የልቦለድ አላባውያንን ለይተው ይገልፃል።
- የተውኔት አላባውያን ምንነትና አላባውያንን ለይተው ይገልፃሉ።
- በስራ ደብዳቤ ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦች፤ ከቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላድን መለየትና ግጥማዊ ዘይቤን ለይተው ይናገራሉ።
- ከግሶች ሌሎች ግሶችን በመመስረትና የምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ይገልፃሉ።
- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ።
- የግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን በመስራትና የዐ.ነገር ክፍሎችን ለይተው ይፅፋሉ።
- የቃላት መጥበቅና ላልተው ሲነበቡ የሚኖረውን የፍች ልዩነት በመልመጃ ሰርተው ያሳያሉ።

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- የቃላት መጥበቅና ላልተው ሲነበቡ የሚኖረውን የፍች ልዩነት በመልመጃ ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- የስነቃል ምንነት፣ ባህሪይንና ተግባርን በመረጃ አስደግፈው ያብራራሉ፡፡

ከታየዉ እለታዊ እቅድ መረዳት እንደተቻለዉ ድርጅትን (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠትን (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም፡፡

**መምህር ሁለት የዘጋጀችዉ እለታዊ የትምህርት እቅድ**

ስሜታዊ ምድብ (Affective domain)

መቀበል (Receiving)

- የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይዘረዝራሉ፡፡
- የምዕላድ ምንነትና ለመኖሩም ክንያት የሆኑ ነጥቦችን ያብራራሉ፡፡
- የአንቀፅ፣የነጠብጣብና የድርብ ሰረዝ ምንነትን ለይተው ይዘረዝራሉ፡፡
- የአያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት ምንነት፣ የአንቀፅ ምንነትና የአስተዋፅ ኦጥቅም ለይተው ይዘረዝራሉ፡፡
- የቃል ክፍሎችን ምንነት፣የሐረግን ምንነትና የልበለድ አለባውያንን ለይተው ያብራራሉ፡፡
- የግጥም ሙያዊ ቃላትንና የዘይቤ አይነቶች ምንነት ለይተው ያብራራሉ፡፡
- የተውኔት አለባውያንን ለይተው ይገልፃሉ፡፡
- የቃላት መጥበቅና መላላት ያላቸውን ልዩነትና የገላጭ ድርሰትና የውይይት ምንነትን ለይተው ይገልፃሉ፡፡
- የቃላትን አገባባዊ፣ የማወስታሻ፣ የማስታወሻ አያያዥንና የምክንያት የውጤትን ምንነት ለይተው ይዘረዝራሉ፡፡
- ከግሶች ሌሎች ግሶችን በመመስረትና የምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ይዘረዝራሉ፡፡
- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ፡፡

- የቤተ-መፅሐፍት አጠቃቀምና የውይይት መመሪያን በመለየት ወደ ተግባር ይለውጣሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርተው ያሳያሉ።
- የዐ. ነገር ክፍሎች ምንነትና ከግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርተው ያሳያሉ።

መመለስ (Responding)

- የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይዘረዝራሉ።
- የምዕላድ ምንነትና ለመኖሩ ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ያብራራሉ።
- የአንቀፅ፣ የነጠብጣብና የድርብ ሰረዝ ምንነትን ለይተው ይዘረዝራሉ።
- የአያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት ምንነት፣ የአንቀፅ ምንነትና የአስተዋፅኦ ጥቅም ለይተው ይዘረዝራሉ።
- የቃል ክፍሎችን ምንነት፣ የሐረግን ምንነትና የልቦለድ አለባውያንን ለይተው ያብራራሉ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትንና የዘይቤ አይነቶች ምንነት ለይተው ያብራራሉ።
- የተውኔት አለባውያንን ለይተው ይገልፃሉ።
- የቃላት መጥበቅና መላላት ያላቸውን ልዩነትና የገላጭ ድርሰትና የውይይት ምንነትን ለይተው ይገልፃሉ።
- የቃላትን አገባባዊ፣ የማወስታሻ፣ የማስታወሻ አያያዥንና የምክንያት የውጤትን ምንነት ለይተው ይዘረዝራሉ።
- ከግሶች ሌሎች ግሶችን በመመስረትና የምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ይዘረዝራሉ።
- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ።
- የቤተ-መፅሐፍት አጠቃቀምና የውይይት መመሪያን በመለየት ወደ ተግባር ይለውጣሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርተው ያሳያሉ።
- የዐ. ነገር ክፍሎች ምንነትና ከግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርተው ያሳያሉ።

ዋጋ መስጠት (Valuing)

- ምንባቡን መሰረት ያደረገውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው ያሳያሉ።

- የቤተ-መፅሐፍት አጠቃቀምና የውይይት መመሪያን በመለየት ወደ ተግባር ይለውጣሉ፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- የዐ. ነገር ክፍሎች ምንነትና ከግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡

ከታየዉ እለታዊ እቅድ መረዳት እንደተቻለዉ ድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠትን (Characterization by value complex) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት የታቀደ እቅድ የለም በተግበራውም ወቀት የተከናወነ ድርጊት አልታየም፡፡

## 5. ባዝየል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት እቅድ ዝግጅት ፍተሻ

በተደረገዉ የሰነድ ምርመራ፣ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ በባዝየል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምንም ዓይነት የትምህርት እቅድ እንደማይዘጋጅ ተረጋግጧል፡፡ መምህራኑም በተደረገላቸዉ ቃለ መጠይቅ አንዱ መምህር በስነ ዜጋ አንዱ ደግሞ በባዮሎጂ የትምህርት ዓይነት እንደተመረቁ ገልጸዉ ነገር ግን አማርኛ ቋንቋ ስለሚናገሩ ብቻ ተገደዉ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደሚያስተምሩ እና እለታዊም ሆነ ዓመታዊ የትምህርት እቅድ አዘጋጅተዉ እንደማያቁ ለማዘጋጀት ተነሳሽነቱም እንደሌላቸዉ ጨምርዉ አብራርተዋል፡፡

## 6. አከዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት እቅድ ዝግጅት ፍተሻ

በአከዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ምንም ዓይነት የትምህርት እቅድ እንደማይዘጋጅ በተደረገዉ የሰነድ ምርመራ፣ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ተረጋግጧል፡፡ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸዉ ሁለት መምህራንም አንዱ በእንግሊዝኛ ሌላኛዉ በስነ ዜጋ ትምህርት ክፍል እንደተመቁ ገልጸዉ ነገር ግን ወደ ትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ባለመመደቡ ባላቸዉ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ ዘጠነኛ‹ሀ›እና‹ለ› ክፍል አንድ አንድ ተካፍለዉ እንደሚሸፍኑ ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን ባላቸዉ የስራ ጫና እና በወረዳዉ እርከን፣ ደረጃ እድገት እና የትምህርት ለዉጥ ባለመሰራቱ ፣ደመወዝ በወቅቱ ባለመከፈሉ፣ወዘተ ምክንያት የትምህርት እቅድ ለማዘጋጀት ተነሳሽነቱ እንደሌላቸዉ አክለዉ ገልጸዋል፡፡

### 4.3 ከሰነ ፍተሻ የተገኙ ጥቅል ውጤቶች ትንተና በመቶኛ

ይህ ጥናት በተለያዩ አጥኚዎችና ምሁራን የተገለጸውን የብሉምስ ታክሰኖሚ ቃለ ነቢብ መሰረት በማድረግ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ ትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀትን መፈተሽ አላማው ያደረገ ሲሆን፣ በምዕራፍ አንድ 1.2 ስር ለተሰጡት መሪ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ይሆናል። ለጥያቄዎቹ መልስ ለመፈለግ ከ1/2/2011 – 30/8/2011 ዓ.ም ድረስ በጋምቤላ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ጋመቤላ ከተማ ጋምቤላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በተጠኚነት በተመረጡ የዘጠነኛ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጁ 150 (አንድ መቶ ሃምሳ) ያህል የእለታዊ እቅዶች ለትንተናው ተመረጠዋል። የተመረጡት እቅዶችም በብሉምስ ታክሰኖሚ ትወራዎች መሰረት የተጻፉትን የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት በመመርመር ከሰነድ ፍተሸው የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

#### 4.3.1. የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከአዕምሮአዊ ምድብ አንጻር

ሠንጠረዥ1. የዕለታዊ የትምህርት  እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከአዕምሮአዊ ምድብ ክፍሎች አንጻር የሚያሳይ ሠንጠረዥ፡-

| የዕለታዊ የትምህርት እቅድ የጊዜ ርዝማኔ | አጠቃላይ የዕለታዊ የትምህርት እቅድና ሙናብዛት | ከአዕምሮአዊ ምድብ መለኪያ አንጻር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እውቀት | መረዳት | ወደ ተግባር መለወጥ | ትንተና | ግንባታ | ግምገማ |
| ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ30/2011 ዓ.ም | 150 | 90 (60%) | 5 (3.33%) | 45 (30%) | 10 (6.66%) | 0 (0%) | 0 (0%) |

ከላይ በሰንጠረዥ 1 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ከስድስቱም መምህራን ከተሰበሰበው መረጃ ውስጥ የታቀዱት የዕለታዊ ትምህርት እቅድ የአዕምሮአዊ ምድብ ክፍሎችን እውቀት 90 (60%)፣ መረዳት 5 (3.33%)፣ ወደ ተግባር መለወጥ 45 (30%) እና ትንተና 10 (6.66%) በአላማ ውስጥ የታቀደ ሲሆን ግንባታና ግምገማ በአንዱም እቅድ አላማ ላይ ያለ መታቀዳቸውን ተስተውሏል።

ሰንጠረዥ 2 ስድስቱን የአዕምሮአዊ ምድብ ከከፍተኛ ደረጃ እና ከዝቅተኛ ደረጃ አንጻር የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡-

| የዕለታዊ የትምህርት እቅድ የጊዜ ርዝማኔ | የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አጠቃላይ ብዛት | የአዕምሮአዊ ምድብ ዝቅተኛ ደረጃ | የአዕምሮአዊ ምድብ ከፍተኛ ደረጃ |
|---|---|---|---|
| ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ30/2011 ዓ.ም | 150 | 138 (92%) | 12(8%) |

ከዚህ ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በናሙና ከቀረቡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ውስጥ 138 (92%) አላማዎች ዝቅተኛውን የአዕምሮአዊ ምድብን (እውቀት፣ ትርጉምና ወደ ተግባር መለወጥ) የሚያሳይ ሲሆን ከፍተኛው የአዕምሮታዊ ምድብን ትርጉም ብቻውን 12(5%) አላማዎች በውስጡ መያዙን ያሳያል። ከዚህ የምንረዳው በአእምሮአዊ ምድብ ከተቀረጹት አላማዎች ውስጥ ከከፍተኛ ደረጃ ይልቅ ዝቅተኛ ደረጃውን መያዛቸውን ከሰነድ ፍተሻ መረጃው ማረጋገጥ ተችሏል።

### 4.3.2 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ አንጻር

ሠንጠረዥ1. የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች አንጻር የሚያሳይ ሠንጠረዥ፡-

| የዕለታዊ የትምህርት እቅድ የጊዜ ርዝማኔ | አጠቃላይ የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ናሙና ብዛት | የይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ መለኪያ | | | አንጻር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | ፅህፈት |
| ከጥቅምት1 እስከ ሚያዚያ 30/2011 ዓ.ም | 150 | 20(13.33%) | 35(23.33%) | 45(30%) | 50(33.33%) |

ከዚህ ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በናሙና ከቀረቡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ ማዳመጥ 20 (13.33%)፣ መናገር 35 (23.33%)፣ ማንበብ 45 (30%)ና ፅህፈት 50 (33.33%) በሆነ መጠን መምህራን ማቀዳቸውን በሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

#### 4.3.3 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከስሜታዊ ምድብ አንጻር

ሠንጠረዥ1. የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከስሜታዊ ምድብ ክፍሎች አንጻር የሚያሳይ ሠንጠረዥ፡-

| የዕለታዊ የትምህርት አቅድ የጊዜ ርዝማኔ | አጠቃላይ የዕለታዊ እቅድ ናሙና ብዛት | ከስሜታዊ ምድብ ክፍሎች አንጻር | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መቀበል | መመለስ | ዋጋመስጠት | ድርጅት | ረቂቅየሆነዋጋመስጠት |
| ከጥቅምት1 እስከ ሚያዚያ 30/2011 ዓ.ም | 150 | 65 (43.33%) | 55 (36.66%) | 30 (20%) | 0 (0%) | 0 (0%) |

ከዚህ ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በናሙና ከቀረቡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ውስጥ መቀበል 65 (43.33%)፣ መመለስ 55 (36.66%) ና ዋጋ መስጠት 30(20%) በአላማቸው ውስጥ ያቀዱ ሲሆን ድርጅትና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት ያለማቀዳቸውን ያመለክታል።

## 4.4. ከቃለ መጠይቅ የተገኘ ተትነተን እና የዉጤት ማብራሪያ

እንደ ሪቻርድ (Richard) (1998 103) አስተያየት ትምህርታዊ እቅድ አንድ መምህር ስለ ትምህረቱ አስቀድሞ አስቦ ችግሮችን ለመፈታት፣ትምህርቱን ለማደራጀት፣መምህሩ የሚከተለዉን ካርታ (map) ለማዘጋጀትና ማስተማር ያለበትን ነገር መዝግቦ ለመያዝ እንደሚያስፈልግ እና እንደሚታቀድ ገልጸዋል።በተደረገዉ ቃለ መጠይቅ በቃለ መጠይቁ ከተካተጡት አስራ ሁለት መምህራን ስምንቱ አለታዊ የትምህርት እቅድ እንደሚያዘጋጁ ነገር ግን ሂደቱን እና ተጣጥሞሹን ያለጠቀ እንደሆነ ሲገልጹ አራቱ ምህራን ግን ጭራሹንም እንደማያቅዱ ተናግረዋል።ይህ ደግሞ የትምህርት እቅዱ በተገቢ ሁኔታ ያለመታቀዱን እና የመማር ማስተማሩን ስራ ዉጤታማ እንዳላደረገዉ ያስገነዝባል።

ሪቻርድ (Richared)(1996) እንድሚያስረዱት የትምህርት እቅድ መምህሩ ትምህርቱን በብቃትና በዉጤታማነት እንድያደራጁ በዉስጡ የትምህርት ዓላማ፣ተማሪዎች የሚተገብሯቸዉ ተግባራት፣ለእያንዳንዱ ተግባር የሚያስፈልገዉ ሰዓት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የመተግበሪያ ስልቶች፣ በእያንዳንዱ ተግባር የቡድን አደረጃጀትን፣ የምዘና ስልትን፣ ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና አማራጩጭን ፣ አካቶ መያዝ አለበት በማለት ገልጸዋል፤፤ በቃለ መጠይቁ የተካተቱት አስራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም በእለታዊ የትምህርት እቅድ ቅጽ ዉስጥ የትምህርት ቤቱ ስም፣ የመምህሩ ስም፣ የትምህርቱ ዓይነት፣ ቀን፣ ክፍለ ጊዜ፣ የትምህርቱ ምዕራፍ፣ ርዕስ፣ አላማ፣ ይዘት፣ የተማሪዉና መምህሩ ተግባር፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት፣ መርጃ መሳሪያ፣ግምገማ፣ ዋናዋናዎቹ እንደሆኑ ገልጸዋል። ይህ የሚያመለክተዉ መምህራኑ ከላይ የዘረዘሯቸዉ በእለታዊ የትምህርት እቅድ ቅጽ መካተት ያለባቸዉ ጉዳዮችን ያዉቋቸዋል እንጅ በተገቢዉ እንደማይተገብሯቸዉ ነዉ።

በአእምሮአዊ ምድብ ስር እዉቀትን /የተማሪዎችን እዉቀት / ለመለካት በሚያዘጋጁት የትምህርት እቅድ ዓላማ ዉስጥ ከግንዛቤ በማስገባት እንደሚያቅዱ፣የቃላትን ችሎታ ለመለካት በይዘቱ ላይ የቃላትና የሀረጋት ፍች ከቀረቡ ይህንን መሰረት በመድረግ እንደሚያቅዱ፣ ወደተግባር መለወጥን በተመለከተ ተማሪዉ በዕለቱ የሚማረዉን ትምህርት በተለያየ መንገድ / በቡድን በማደራጀት፣በማከራከር፣በማወያየት፣ ወደ ተግባር እንድለዉጡ በሚይዘዉ ይዘት መሰረት በማድረግ በእለታዊ የትምህርት እቅድ ዉስጥ እንደሚያቅዱ፣ ትንተናን በይዘቱ ላይ የሚዘረዘሩ ሀሳቢች ቀረበዉ ከሆነ በእለታዊ የትምህርት እቅድ ዉስጥ እንደሚያቅዱ፣ ግንባታንና ግምግማን ግን በጭራሽ እንደማያቅዱና ግምገማ በትምህርት እቅድ ዉስጥ እራሱን የቻለ ቦታ እዳለዉ ስምንቱ መምህራን ገልጸዋል።አራቱ መምህራን ግን ጭራሹንም የትምህርት እቅድ እንድማቅዱ በተደረገዉ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል።

በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከትነው ስሜታዊ ምድብ እንደ karthwal, Bloom,Masia,(1973) የሚያጠቃልላቸው ነገሮች በስሜታዊነት ( enthusiasms ) የምናይበት ሁኔታ ነው።ለምሳሌ፣ ስሜት፣ እሴቶች (values )፣ አድናቆት፣ ፍላጎትን፣ ምስጋናን፣ መልመድን፣ ተነሳሽነት እና ዝንባሌዎች ያጠቃልላል። የትምህርት እቅድ አላማ የስሜታዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት መቀበልን፣ መመለስን፣ ዋጋ መስጠትን፣ መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል።

ከስሜታዊ ምድብ ስር የሚመደበው የመጀመሪያው መቀበል ሲሆን መምህራን ለሚያስተምሩት ትምህርት ተማሪዎች ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ለመለካት የእለቱን ትምህርት ጠቃሚነት በደንብ በማስረዳት ወደ ትምህርቱ እንዲሳቡ የማነቃቃት ግንዛቤ እንደሚሰጡ ። መልስ መስጠትንም በተመለከተ የተለያዩ ይዘቶችን በእለቱ ትምህርት ካስተማሩ በኋላ ተማሪዎቹን ጥያቄ እንደሚጠይቁና ያለፈውን ትምህርት በማስታወስ ወደ እለቱ ትምህርት እንደሚገቡ ታሳቢ በማድረግ በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ እንደሚያቅዱ ስምንቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የገለጹ ሲሆን አራቱ መምህራን ግን የትምህርት እቅድ እንደማያቅዱ መረዳት ተችሏል ። ዋጋ መስጠት፣ ድርጅት እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት በተመለከተ በሰጡት ምላሽ በእነዚህ ሶስት ሀሳቦች ላይ በቂ እውቀት እንደሌላቸውና የትምህርት እቅድ አላማ ላይም እንደማያቅዱ አስራ ሁለቱም መምህራን በሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል።

በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከተው (Harrow.A.J.1972) የትምህርት እቅድ አላማ የይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት ቅፅበታዊ እንቅስቃሴን (Reflex)፣ መሰረታዊ እንቅስቃሴን (Fundamental movement)፣ ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታን (Perceptual abilities)፣ አካላዊ ችሎታን (Physical ablities)፣ ክሂሎታዊ እንቅስቃሴን (skill movement) እና የማይዋዥቅ ግንኙነትን (Nondiscursive communication) መለካታቸውን መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል።

በዚህ መሰረት በይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ለሚካተቱት ለእያንዳንዱ ክሂሎች በቃለ መጠይቁ ከተካተቱት አስራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስምንቱ መምህራን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እንዴት በእለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ላይ እንደሚያሰፍሩ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ እያንዳንዱ የትምህርት ይዘት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር በቀረበው መሰረት በትምህርት እቅዳችን ላይ እንደሚያሰፍሩ ነገር ግን ለእያንዳንዱ ክሂል ትኩረት ሰጥተዉ ሳይሆን ይዘቱ ላይ ተሞርኩዘዉ እንደሆነ ገልጸዉ ምክንያቱንም የቋንቋ ክሂሎችን ለመነጣጠል አስቸጋሪ ስለሆኑ በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።አራቱ መምህራን ግን በትምህርት ቤታቸዉ እለታዊ የትምህርት እንደማያዘጋጁ መረዳት ተችሏል ።

በተደረገዉ ቃለ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለዉ  እለታዊ የትምህርት እቅድ በተገቢዉ ሁኔታ እንደማያዘጋጁ እና ምክንያታቸዉም የእርስ በርስ ግጭት፣የትምህህት ቤቶች በጊዜ አለመከፈት፣በዉሃ ሙላት ምክንያት የተማሪዎች በጊዜ ወደ ትምህርት ቤት አለመምጣት፣በዉጭ አገር ዘመን አቆጣጠር የአዲስ ዓመት እና የገና በዓል ዝግጅትና በዓል አከባበር በሚል ሰበብ የተመሪዎች ከትምህርት ገበታቸዉ መቅረት፣ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸዉ ዝቅተኛ አመለካከት፣ተመሪዎች ዓመቱን ሙሉ ሳይማሩ ነገር ግን ወደሚቀጥዉ ክፍል መዘዋወር፣…እንደሆነ ገለጸዉ  በተገቢዉ ሁኔታ እንዳያዘጋጁ እንቅፋት የሚሆኑባቸዉ በበጀት እጥረት ምክንያት መገልገያ ቁሳቁሶች እጥረት/ወረቀት፣ካረቦን፣ማስመሪያ ፣….አቅርቦት መነስ፣የመምህራን ጥቅማጥቅም/እርከን፣ደረጃ እድገት፣የትምህርት ለዉጥ/ አለመሰራት፣ የደሞዝ በወቅቱ አለመከፈል፣….እድሆነ አክለዉ አብራርተዋል።

መምህራን ያዘጋጁትን እለታዊ የትምህርት እቅድ ወደ ክፍል ይዘዉ እንደማይገቡ በተደረገዉ ቃለ መጠይቅና ምልከታ መረዳት ተችሏል፡፡

በተደረገዉ ቃለ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለዉ የትምህርት ጊዜያት የሚባክኑበት ወቅት እንደሚኖር እና የሚባክኑትም ትምህርት በወቅት አለመጀመር፣በእርስ በርስ ግጭት፣በመምህራን ደመወዝ በወቅት አለመከፈል፣ በዉጩ አገር አዲስ ዓመት ዝግጅት እና በዓል አከባበር ምክኒያት፣ መጨረሻ ነጥብ ይሞላልኛል በሚል ሰበብ የተማሪዎች ወደ ክፍል አለመግባት እንደሆነ ዘርዝረዉ ጊዜዉ በመባከኑ ምክኒያት የሚፈጠረዉን የእቅድ አለመጣጣምም በማካካሻ ክፍለ ጊዜ ለመሸፈን እንደሚሞክሩነገር ግን ተማሪዎቹ ስለማይመጡ ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈኑ እንደሚቀሩ አብራርተዋል፡፡

የትምህርት ጊዜ መባከን ወይም እቅዱ በአግባቡ አለመተግበሩ በተማሪዎች ዉጤት ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረዉ ፡፡ከቃለ መጠይቁ መረዳት ተችሏል፡፡

መምህራን የሚያዘጋጁት እለታዊ እቅድ ከዓመታዊ እና ከምእራፋዊ የትምህርት እቅድ ጋር በመጣጣም በተፈለገዉ ጊዜ እንደማይጠናቀቅ እና የማይጠናቀቅበትም ምክንያት አብዛኛዉን ጊዜ በተለያዩ ምክኒያቶች የትምህርት ጊዜያት ስለሚባክኑ የሚያዘጋጁት እለታዊ የትምህርት እቅድ የይስሙላ እንደሆነ በቃለ መጠይቁ ከተካተቱት አስራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከስምንቱ መረዳት ተችሏል፡፡

የእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን አስመልክቶ በትምህርት ቤቱ ወይም በወረዳዉ የተሰጠ ስልጠና እንደሌለ በተደረገዉ ቃለ መጠይቅ ተረጋግጧል፡፡

### 4.4.1 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ገለፃ እና ማብራሪያ

በእነዚህ ቃለ መጠይቆች ውስጥ አስር ጥያቄዎች ለተነደፈው አላማ ግብ መምቻነት ሲባል መምህራኑ የሰጡትን ምላሽ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ለዚህም ቃለ መጠይቅ ምላሽ እንዲሰጡ የተጠየቁት አስራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ ትንተናውም የመምህራኑን ምላሽና የሙሁራን ሀሳብ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ነው፡፡

የእለታዊ የትምህርት እቅድ ሁል ጊዜ ታዘጋጃላችሁን? ለሚለው ጥያቄ በቃለ መጠይቁ ከተሳተፉት አስራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል ስምንቱ መምህራን የእለታዊ የትምህርት እቅድ እንደሚያዘጋጁ ነገር ግን ሂደቱንና ተጣጥማሹን የጠበቀ እንዳልሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አራቱ መምህራን ግን እንደያውም እቅድ እንደያማዘጋጁ ተናግረዋል፡፡

እንደ Richard (1998, 103) አስተያየት ትምህርታዊ እቅድ አንድ መምህር ስለ ትምህርቱ አስቀድሞ አስቦ ችግሮችን ለመፍታት፣ ትምህርቱን ለማደራጀት፣ መምህሩ የሚከተለውን ካርታ (map) ለማዘጋጀትና ማስተማር ያለበትን ነገር መዝግቦ ለመያዝ እንደ ሚያስፈልግ እና እንደሚታቀድ ገልጸዋል። ይህንን ንድፈ ሀሳብ አብዛኛዎቹ መምህራን ወደ ተግባር መለወጣቸውን ከቃለ መጠይቁ መረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም እቅድ ሳያዘጋጁ የሚያሰተምሩም አልታጡም።

> እኔ በኣማርኛ ትምህርት አልሰለጠንኩም፣ እንዳስተምር የተደረገው አማርኛ በመናገሬ እና የመምህር እጥርት በመኖሩ ነው። የአማርኛ ትምህርት እቅድ እንዴት እንደሚዘጋጅ አለውቅም። በዘጋጅም በየጊዜው ተምህርት ሰለሚቋረጥ በእቅዱ መሰረት ትምህርቱን ማስኬድ አዳጋችነው። (በ18/7/2011 የተደረገ ቃለመጠይቅ)

በእለታዊ የትምህርት እቅድ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይካተታሉ ብለው ያስባሉ? ለሚለው ጥያቄ በቃለ መጠይቁ ከተሳተፉት አስራ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በእለታዊ የትምህርት እቅድ ቅፅ ዉስጥ የትምህርቱ ቤቱ ስም፣ የመምህሩ ስም፣ የትምህርት አይነት፣ ቀን፣ ክፍለ ጊዜ፣ የትምህርቱ ምዕራፍ፣ ርዕስ፣ አላማ፣ ይዘት፣ የተማሪውና የመምህሩ ተግባር፣ የመማር ማስተማር ሂደት፣ መርጃ መሳሪያ፣ ግምገማ ዋና ዋናዎቹ ናቸው በማለት አስራ ሁለቱም ምላሽ ሰጥተዋል።

Richards& Lock hart (1996) እንደሚያስረዱት የትምህርት እቅድ መምህሩ ትምህርቱን በብቃትና በውጤታማነት እንዲያደራጁ በውስጡ የትምህርት አላማ፣ ተማሪዎች የሚተገብራቸውን ተግባራት፣ ለእያንዳንዱ ተግባራት የሚያስፈልገውን ሰዓት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የመተግበሪያ ስልቶች፣ በእያንዳንዱ ተግባራት የቡድን አደረጃጀትን፣ የምዘና ስልትን፣ ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና አማራጮችን አካቶ መያዝ አለበት በማለት ገልፀዋል። ይህንን ንድፈ ሀሳብ መምህራን ወደ ተግባር መለወጣቸውን የቃለ መጠይቁ ውጤት አሳይቷል።

ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከተው (Blooms, 1956) የትምህርት እቅድ አላማ የአእምሮእዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት እውቀትን፣ ትርጉምን፣ ወደ ተግባር መለወጥን፣ ትንተናን፣ ግንባታንና ግምገማን መለካታቸውን መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል።

በዚህ መሰረት በአዕምሮአዊ ምድብ ለሚካተቱት ለእያንዳንዱ ክፍሎች በቃለ መጠይቁ መሰረት መምህራኑ የሰጡትን መልስ ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ ከአዕምሮአዊ ምድብ ክፍል ስር የሚመደበው እውቀትን ስንመለከት የተማሪዎች እውቀትን ለመለካት በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ እንዴት ታቅዷል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ስምንቱ መምህራን የተማሪዎችን እውቀት ለመለካት በምናወጣው የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እናቅዳለን በማለት ምላሽ ሲሰጡ አራቱ ግን እንደማያቅዱ ገልጸዋል፡፡ ሌላው የተማሪዎችን የትርጉም ችሎታ ለመለካት በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ ማቀዳቸውን ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ በይዘቱ ላይ የቃላትና የሐረጋት ፍቾ ከቀረቡ ይህንን መሰረት በማድረግ እናቅዳለን በማለት ስምንቱ መምህራን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አራቱ መምህራን ግን በጭራሽ እንደማያቅዱ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠልም ወደ ተግባር መለወጥን በተመለከተ ተማሪው በዕለቱ የሚማረውን ትምህርት በተለያየ መንገድ ማለትም በቡድን በማደራጀት፣ በማከራከር፣ በማወያየት... ወደ ተግባር እንዲለውጡ በሚያዘው ይዘት መሰረት በማድረግ በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ እናቅዳለን በማለት ስምንቱ መምህራን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሌላው ትንተናን፣ ግንባታንና ግምገማን በተመለከተ የሰጡት ምላሽ ትንተናን በይዘቱ ላይ የሚዘረዘሩ ሀሳቦች ቀርበው ከሆነ በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ ትንተናን እናቅዳለን በማለት ስምንቱ መምህራን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አራቱ መምህራን ግን በትምህርት ቤት ዉስጥ እለታዊ የትምህርት እቅድ ጭራሹንም አናዘጋጅም በማለት መልሳቸዉን አስቀምጠዋል ፡፡ ግንባታንና ግምገምን ግን በፍጹም እንደማያቅዱና ግምገማ ራሱን የቻለ ቦታ በትምህርት እቅድ ውስጥ እንዳለው አስራ ሁለቱም መምህራን ገልጸዋል፡፡ መምህራኑ እንደገለጹት መምህረኑ እቅድ ሲያቅዱ ትኩረት የሚሰጡት ለይዘቱ እንጂ በይዘቱ በኩል ኣላማ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

> እቅድ ስናቅድ ትኩረት የምናደርገው ለይዘቱ ነው፡፡ እኔ በግሌ እቅዶች ሲዘጋጁ ምንምን ስለማሟላታቸው ወይም አላማዎቹ ከብሉምስ ታክሶኖሚ ጋር ሂዱ አይሂዱ አስቤም አላውቅም፡፡ በየሳምቱ አርብ የትምህርት እቅድ አዘጋጅተን ለትምህርት ክፍሉ ሃለፊ እና ለምክትል ርእሰ መምህሩ እናስፈርማለን በልዩልዩ ምክንያት ትምህርቱ

ሳይካሄድ ከቀረ በሚቀጥለው ሳምንትም ይንኑ እቅድ እናስቀጥላለን። (በ 28/7/2011 በኤሊያ ትምህርት ቤት የተደረገ ቃለመጠይቅ)

ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከትነው ስሜታዊ ምድብ እንደ karthwal, Bloom,Masia,(1973) የሚያጠቃልላቸው ነገሮች በስሜታዊነት ( enthusiasms ) የምናይበት ሁኔታ ነው።ለምሳሌ፣ ስሜት፣ እሴቶች (values )፣ አድናቆት፣ ፍላጎትን፣ ምስጋናን፣ መልመድን፣ ተነሳሽነት እና ዝንባሌዎች ያጠቃልላል። የትምህርት እቅድ አላማ የስሜታዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት መቀበልን፣ መመለስን፣ ዋጋ መስጠትን፣ መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል።

በዚህም መሰረት በስሜታዊ ምድብ ለእያንዳንዱ ክፍል በቃለ መጠይቁ አማካኝነት የተሰጠዉ ምላሽ ከዚህ በታች ቀርቧል።

ከስሜታዊ ምድብ ስር የሚመደበው የመጀመሪያው መቀበል ሲሆን ተማሪዎች የምናስተምራቸውን ትምህርት ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ለመለካት የእለቱን ትምህርት ጠቃሚነት በደንብ በማስረዳት ወደ ትምህርቱ እንዲሳቡ የማነቃቃት ግንዛቤ እንደሚሰጡ ተናግረዋል። መልስ መስጠትንም በተመለከተ የተለያዩ ይዘቶችን በእለቱ ትምህርት ካስተማሩ ተማሪዎቹን ጥያቄ እንደሚጠይቁና ያለፈውን ትምህርት በማስታወስ ወደ እለቱ ትምህርት እንደሚገቡ ታሳቢ በማድረግ ስምንቱ መምህራን በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ውስጥ እናቅዳለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ዋጋ መስጠት፣ ድርጅት እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት በተመለከተ በሰጡት ምላሽ በእነዚህ ሰስት ሀሳቦች ላይ በቂ እውቀት እንደሌላቸውና የትምህርት እቅድ አላማ ላይም እንደማያቅዱ አስራ ሁለቱም መምህራን ምላሽ ሰጥተዋል።

ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከተው (Harrow.A.J.1972) የትምህርት እቅድ አላማ የይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት ቅፅበታዊ እንቅስቃሴን (Reflex)፣ መሰረታዊ እንቅስቃሴን (Fundamental movement)፣ ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታን (Perceptual abilities)፣ አካላዊ ችሎታን (Physical ablities)፣ ክሂሎታዊ እንቅስቃሴን (skill movement) እና የማይዋዥቅ ግንኙነትን (Nondiscursive communication) መለካታቸውን መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል።

ይህንን የይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ሀሳብ ከቋንቋ ትምህርት ጋር ስናገናኘው አራቱን የቋንቋ ክሂሎች መለማመድንና ማዳበርን የሚመለከት ይሆናል። በዚህ መሰረት በይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ለሚካተቱት ለእያንዳንዱ ክሂሎች በቃለ መጠይቁ መሰረት መምህራኑ የሰጡትን መልስ ከዚህ በታች ቀርቧል። ስምንቱ መምህራን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እንዴት በእለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ላይ እንደሚያሰፍሩ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ እያንዳንዱ የትምህርት ይዘት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር በቀረበው መሰረት በትምህርት እቅዳችን ላይ እናሰፍራለን። ነገር ግን ለእያንዳንዱ ክሂል ትኩረት ሰጥተን ሳይሆን ይዘቱ ላይ ተሞርኩዘን ነው። ምክንያቱም የቋንቋ ክሂሎችን ለመነጣጠል አስቸጋሪ ስለሆኑ በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

እለታዊ የትምህርት እቅድ በተገቢዉ ሁኔታ የማያዘጋጁ ከሆነ  ለምን?በተገቢዉ ሁኔታ እንዳያዘጋጁ እንቅፋት የሚሁንቦት ነገር ምንድነዉ? ተብለዉ ለተጠየቁት እለታዊ የትምህርት እቅድ በተገቢዉ ሁኔታ እንዳናቅድ በወረዳዉ ትምህርት የሚከፈተዉ በሁለተኛዉ ወር አጋማሽ ወይም በሶስተኛዉ ወር ሲሆን ተማሪዎች በጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ስለማመጡ እለታዊ የትምህርት እቅድ በተገቢዉ እንደማያቅዱ፣ በኢታንግ ልዩ ወረዳ አኙዋ፣ ኑዌር ኦፖ፣ እና ሌሎች ብሄረሰቦች የሚኖሩ ሲሆን በየጊዜዉ በአኙዋ እና በኑዌር ብሄረሰብ ግጭት እንደሚፈጠር፣ ግጭቱ ሲፈጠር ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸዉ እንደሚቀሩ፤የመማር ማስተማሩ ሂደት እንድሚደናቀፍ፣ በዚህ የተነሳ እለታዊ የትምህርት እቅድ በተገቢዉ ሁኔታ እንደማያዘጋጁ፤ ኢታንግ ልዩ ወረዳ በባሮ ወንዝ የተከበበች ስትሆን በዉሃ ሙላት ምክንያት ከወንዙ ወዲያ ማዶ የሚኖሩ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት እንደሚቀሩ፣የኑዌር ተማሪዎች ደግሞ የዉጭ አገር ዘመን አቆጣጠር ስለሚከተሉ ለገና በዓል  እና ላዲስ ዓመት ዝግጅትና በዓል አከባበር በሚል ሰበብ ታህሳስ ወር ወደ ትምህርት ቤት እንደማይመጡ፣ ሌላዉ ደግሞ አብዛኛዉ ተማሪ በመስከረም ወይም በጥምት ወር ተመዝግቦ ዓመቱን በሙሉ ወደ ትምህርት ቤት አይመጣም የሚመጡት ጥቂት ተማሪዎችም በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ወደ ክፍል እንደማይገቡ ከገቡም ወጥተዉ እንደሚሄዱ ነገር ግን በዓመቱ መጨረሻ ላይ እነሱ ባስቀመጡት ዉጤት ሳይሆን 80/ሰማኒያ/ እና ከዚያ በላይ ነጥብ ተሞልቶላቸዉ ወደ ሚቀጥለዉ ተዛዉሮ እንደሚያገኙዋቸዉና ይህ ደግሞ እለታዊ የትምህርት በተገቢዉ ሁኔታ እንዳያቅዱ እንደሚደርጋቸዉ ምላሻቸዉን ሰጥተዋል። እንዲሁም እቅዱን እንዳያዘጋጁ እንቅፋት የሚሆንቦት ነገር ምንድነዉ ለሚለዉ ጥያቄ በበጀት እጥረት

ምክኒያት መገልገያ ቁሳቁሶች/ወረቀት፣ እስክብሪቶ ካርቦን፣ አጋዥ መጻህፍት የመሳሰሉት / አቅርቦት አለመኖር፣የመምህራን ጥቅማጥቅም /የትምህርት ለዉጥ ፣ እርከንና ደረጃ አድገት/ አለመሰራት፣ የደመወዝ በወቅቱ አለመከፈል እንደሆነ አብራርተዋል።

ወደ መማሪያ ክፍል ሲሄዱ ዘወትር እለታዊ የትምህርት እቅድ ይዘዉ ይገባሉ?ተብለዉ ለተጠየቁት አስራ ሁለቱም መምህራን እለታዊ የትምህርት እቅድ ይዘዉ እንደማይገቡ ገልጸዋል።

የትምህርት ጊዜያት የሚባክኑበት ወቅት አለ? በምን ምክኒያት? ጊዜዉ በመባከኑ የሚፈጠረዉን የእቅድ አለመጣጣም እንዴት ያደርጉታል? ለሚለዉ ጥያቄ በቃለ መጠይቁ ከተሳተፉ አስራ ሁለት መምህራን የስምንቱ መምህራን ምላሽ እንደሚከተለዉ ቀርቧል። የትምህርት ጊዜያት የሚባክኑበት ወቅት እንደሚኖር እና የሚባክኑትም ትምህርት በወቅቱ አለመጀመር፣ በእርስ በርስ ግጭት፣በመምህራን ደመወዝ በወቅት አለመከፈል፣በዉጩ አገር አዲስ ዓመት ዝግጅት እና በዓል አከባበር ምክኒያት፣መጨረሻ ነጥብ ይሞላልኛል በሚል ሰበብ የተማሪዎች ወደ ክፍል አለመግባት እንደሆነ ዘርዝረዉ ጊዜዉ በመባከኑ ምክንያት የሚፈጠረዉን የእቅድ አለመጣጣምም በማካካሻ ክፍለ ጊዜ ለመሸፈን እንደሚሞክሩነገር ግን ተማሪዎቹ ስለማይመጡ ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈኑ እንደሚቀሩ አብራርተዋል።

የትምህርት ጊዜ መባከን ወይም እቅዱ በአግባቡ አለመተግበሩ በተማሪዎች ዉጤት ላይ ተጽዕኖ ሊኖረዉ አይችልም?ተብለዉ ለተጠየቁት ተጽዕኖ እንደሚኖረዉ ምላሽ ሰጥተዋል።

የሚያዘጋጁት እለታዊ እቅድ ከዓመታዊ ከምእራፋዊ የትምህርት እቅድ ጋር በመጣጣም በተፈለገዉ ጊዜ ይጠናቀቃል? ለሚለዉ ጥያቄ በቃለ መጠይቁ ከተካተቱት አስራ ሁለቱ መምህራን የስምንቱ ምላሽ እንደሚከተለዉ ተቀምጧል።የሚያዘጋጁት እለታዊ እቅድ ከዓመታዊ እና ከምእራፋዊ የትምህርት እቅድ ጋር በመጣጣም በተፈለገዉ ጊዜ እንደማይጠናቀቅ እና የማይጠናቀቅበትም ምክንያት አብዛኛዉን ጊዜ በተለያዩ ምክኒያቶች የትምህርት ጊዜያት ስለሚባክኑ የሚያዘጋጁት እለታዊ የትምህርት እቅድ የይስሙላ እንደሆነ ገልጸዋል።ይህንን በተመለከተ አንድ መምህር የሰጠው የቃለመጠይቅ ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል።

> ምንም እንኳ በተለያዩ ግዚያት ትምህርት ስለምቋረጥ በርካት ክፍለግዚያት በመባከናቸው የሴሚስተሩ ትምህርት እና ያስተማርነው ባይጣጣምም፣ ሴሚስተሩ ሊያልቅ ስል በመደበኛው ክፍለ ጊዜም ይሁን በማካካሻ ጊዜ አጠዳድፍን ትምህረቱን በመጨረስ ፈተና እንሰጣለን። ብዙ

ተማሪ ፈተናውን ስለማይሰራው ለሁሉም ተማሪ ማርክ በመጨመር እንዲያልፉ እእደርጋለን፡፡(በ04/8/2011 የተደረገ ቃለመጠይቅ)

የእቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን አስመልክቶ በትምህርት ቤቱ ወይም በወረዳዉ የተሰጠ ስልጠና አለ?ለሚለዉ ጥያቄ በቃለመጠይቁ የተካተቱት አስራሁለቱም መምህራን ምንም አይነት ስልጠና እንዳልተሰጠ ገልጸዋል፡፡

## 4.4.2 ከምክትል ርዕሳነ መምህራን እና ከክፍለ ትምህርቱ ተጠሪዎች በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ገለጻና ማብራሪያ

የትምህርት እቅድ ሲዘጋጅም ሆነ ሲተገበር ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ሲኖሩ በቀጥታ የሚመለከታቸዉ መምህሩ፣የክፍለ ትምህርቱ ተጠሪ እና የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ምክትል ርዕሰ መምህር ናቸዉ፡፡ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከፍተኛ ድርሻ ያለዉ በመሆኑ አጠቃላይ የትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ሂደት ዉጤታማ ይሆን ዘንድ የትምህርት ዕቅዱን ተግባራዊነት የመከታተልና የማስፈጸም፣ ለትምህርት መሻሻል የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች (department heads) እና ለመምህራኑ የሞያ እገዛና ምክሮችን በመለገስ የትምህርቱ ሥራ በታለመለት ጊዜና ዕቅድ እንዲተገበር የመቆጣጠርና የመገምገም ሥራ ያከናዉናል፡፡ ስለሆነም ርዕሰ መምህሩ በተጓደሉና ዉሳኔ በሚያስፈልጋቸዉ የእቅድ ጉዳዮች ላይ ከትምህርት ክፍሉ ተጠሪዎች ጋር በመሆን ዉሳኔ በመስጠት ዕቅዱን እንዲተገበር ተጠሪዎችን መገምገምና መከታተል አለበት (Spooner, F. 2007) ፡፡ የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች (department heads) የመምህራኑ የየዕለቱ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ በመሆናቸዉ ጥራት ያለዉን የመማር ማስተማር ሂደትን ለማስቀጠል ሙሉ አቅማቸዉን በመጠቀም ክፍል ዉስጥ ምልከታን ጨምሮ ለመምህራኑ በየዕለቱ የዉሎዉን ግብረ መልስ እየሰጡ መሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተጠሪዎቹ በአሰራር የሥራ ልምዳቸዉ እና ክህሎታቸዉ ከመምህራኑ በመጠኑም ቢሆን የተሻሉ ናቸዉ ተብሎ ስለሚታሰብ በየዕለቱ የዕቅዱን ዓላማና ይዘት እየገመገሙ መምህራኑን የመደገፍ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ዕለታዊዉ

የትምህርት ዕቅዱ እንዲተገበር የትምህርት ክፍሉ ተጠሪዎች የሚከተሉትን የሥራ ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል (Purgason, K. B. 1991) ፣

1. በመማር ማስተማር ሂደቱ ያካበቱትን ልምድ በተግባር ማሳየት አለባቸዉ።
2. በክፍል ዉስጥ እያስተማሩ ማሳየትን ጨምሮ ለመምህራኑ ሞዴል ሆነዉ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፤
3. ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር በመሆን መምህራኑ እዉቀታቸዉን ለማዳበር የእርስ በርስ የልምድ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ ማስተባበር።
4. ምክንያታዊ የሆኑ ግብረ መልሶችን በመስጠት ከትምህርት ክፍሉ መምህራን ጋር ያለፈዉን ጉድለት የማረምና ስለቀጣዮቹ ቀናት የትምህርት ዕቅድ ለዉጤታማነታቸዉ እንዴት መፈጸምና ማስፈጸም እንዳለባቸዉ መወያየት የመሳሰሉት እንደሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል።

በቃለ መጠይቁ የተካተቱት በጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን እና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተጠሪዎችም ለቀረበላቸዉ ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

መምህራን የትምህርት እቅድ ማዘጋጀታቸዉን እንዴት ትከታተላላችሁ? ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ ቼክ ሊስት /ማረጋገጫ ነጥብ/ በማዘጋጀት እያንዳንዱ መምህር የዕለታዊ እቅድ ማዘጃ ቅጽ ሐሙስ ወስዶ አዘጋጅቶ አርብ ማስገባቱን እንከታተላለን በማለት በቃለ መጠይቁ አራት ምክትል ርዕሳነ መምህራን እና ሦሥት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች ምላሽ ሰጥተዋል። ይህን በተመለከተ የአንዱ ትምህርት ቤት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪ ምላሽ ሲሰጥ በሚከተለው መልኩ ገልጾታል፣

> የሳምነንታዊ ትምህርት አቅድ በውስጡ የሳምንቱንም ክፍለ ግዚያት የያዘ ተዘገጅቶ በየሳምንቱ ይሰጣል። ይህን እንጂ ወረቀቱም እቅድን ሰፋ አድርጎ ለመስራት የሚያስችል አይደለም። ትምህርት በየጊዘው በልዩ ልዩ ችግሮች ምክንያቶች

ስለሚቋረጥ ተግባራዊነቱንም ተከታትለን አናይም። ብዙ ጊዜ ፍርማ ማስቀመጥ እና መስራቱን በመዘገብ ላይ ምልክተ አደርገለሁ እንጂ ይዘትና ቅርጹን በስርኣት አይቼ አላውቅም።( በ05/8/2011 የተደረገ ቃለመጠይቅ መኮድ)

መምህራን ያዘጋጁትን የትምህርት እቅድ በትክክል መተግበራቸዉን እንዴት ታረጋግጣላችሁ? ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ መምህራኑ ለማስተማር በሚሄዱበት ወቅት ወደ ክፍል በመግባት አቅዱ በትክክል መተግበሩን እንደሚፈትሹ በቃለ መጠይቁ የተካተቱት አራት ምክትል ርዕሳነ መምህራን እና ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ገልጸዋል።

ለትምህርት እቅድ ዝግጅት የሚሆን በቂ ግበዓት አለ? ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ በቃለ መጠይቁ የተካተቱት የአምስቱ ትምህርት ቤቶች አራት ምክትል ርእሳነ መምህራን እና ሶስት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች ለትምህርት እቅድ ዝግጅት የሚሆን በቂ ግበዓት እንደሌለ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከትምህርት እቅድ አንጻር የሚገጥሟችሁ ችግሮች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸዉ? ተብሎ ለቀረበላቸዉ የሚገጥሟቸዉ ችግሮች እንዳሉና ችግሮቹም የግበዓት አለመኖር፣ መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት አለመመደብ፣ በተለያዩ ምክንያቶች/ በእርስ በርስ ግጭት፣በዉሃ ሙላት፣..../ የተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸዉ መቅረት፣ በደሞዝ መዘግየት ምክንያት የመምህራን በስራ ገበታቸዉ አለመገኘት አንደሆነ በቃለ መጠይቁ ከተሳተፉት ስድስት ምክትል ርዕሳነ መምህራንና አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል አራት ምክትል ርዕሳነ መምህራን እና አራት የክፍለ ትምህርቱ ተጠሪዎች ምላሻቸዉን በተመሳሳይ መልኩ ገልጸዋል።

የትምህርት ጊዜ መባከን ወይም አለመተግበር በተማሪዎች ዉጤት ላይ ተጽዕኖ ሊኖረዉ አይችልም? ለሚለዉ ጥያቄ በቃለ መጠይቁ ከተካተቱት ስድስት ምክትል ርዕሳነ መምራንና አራት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች መካከል አራት ምክትል

ርዕሳነ መምህራን እና አራት የክፍለ ትምህርቱ ተጠሪዎች የትምህርት ጊዜ መባከን ወይም አለመተግበር በተማሪዎች ዉጤት ላይ ተጥዕኖ እንደሚኖረዉ ገልጸዋል።

የትምህርት እቅድን ጠቀሜታ እንዲገልጹ ለተጠየቁት የትምህርት እቅድ ጠቀሜታ ብዙ እንደሆነ ገልጸዉ  የትምህርት እቅድ የታቀደዉ ዓላማ ግቡን እንዲመታ የሚያስችሉ ድርጊቶችን ለመወሰን፣ መርጃ መሳሪያዎችን ለመምረጥ፣ እያንዳንዱ ድርጊት የሚፈጀዉን ጊዜ ለማወቅ፣ተማሪዎችን በቡድን ለማደራጀት፣ አንድን የዓላማ ድርጊት ከሚቀጥለዉ የዓላማ ድርጊት ለመቆራኘት፣መምህሩ ከሚያስተምረዉ የትምህርት ይዘት ጋር ያለዉን የእዉቀት ተመጣጣኝነት እራሱን ለመገምገም ይረዳዋል፣ለመምህሩ በራስ የመተማመን ባህልን ለማዳበር ያግዘዋል፣ ለትምህርት የተሰጠ ጊዜ እንዳይባክን ይረዳል፣ መምህሩ የሌላዉን ክፍለ ጊዜ ሳይሻማ የራሱን ክፍለ ጊዜ እንዲጠቀም ይረዳዋል፣ ወዘተ በማለት በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ ስድስት ምክትል ርዕሳነ መምህራንና የአማርኛ ቋንቋ  ትምህርት ተጠሪዎች አብራርተዋል።

የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን አስመልክቶ በትምህርት ቤቱ ወይም በወረዳዉ የተሰጠ ስልጠና አለ? ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ በቃለ መጠይቁ የተካተቱት ስድስት ምክትል ርዕሳነ መምህራን እና አራት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተጠሪዎች የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን አስመልክቶ በትምህርት ቤቱም ሆነ በወረዳዉ ምንም  የተሰጠ ስልጠና እንደሌለ ገልጸዋል።

የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን በምን መልኩ መከወን ይቻላል? ተብለዉ ለተጠየቁት ምቹ በሆነ የአቀራረብ ዓይነትና በተመጠነ የአቀራረብ ፍጥነት ላይ ትኩረት በመስጠት፣ ክፍሉን ተወዳጅና ሳቢ በማድረግ፣ አቀራረብንም በመቀያየር (ከፈጣን ዝግ ወዳለ እንቅስቃሴ) በመቀየር መከወን እንደሚቻል በቃለ መጠይቁ የተካተቱት ስድስት ምክትል ርዕሳነ መምህራንና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተጠሪዎች አብራርተዉ ገልጸዋል።

ለባዝየል እና አከዶ ምክትል ርዕሳነ መምህራን በተካሄደዉ ቃለ መጠይቅ በየዓመቱ የአዲስ መምህራን ምደባ የነባር መምህራን ዝዉዉር በየትምህርት ቤቱ በሚደረገዉ

ስርጭት መምህራን የሚመደቡት ክፍተት ባለዉ የትምህርት ዓይነት ሳይሆን ለመዳቢዉ በሚመች መልኩ እንደሆነና በተደጋጋሚ የአማርኛ ቋንቋ መምህር እንዲመድቡላቸዉ ቢያመለክቱም ሊመድቡላቸዉ እንዳልቻሉና ሌላ አማራጭ ስሌላቸዉ በሌላ ትምህርት መስክ መምህራን እንዲሸፈን ማድረጋቸዉን ገልጸዉ እነዚህን መምህራን አስገድደዉ እለታዊም ሆነ ዓመታዊ የትምህርት እቅድ ማሰራት እንዳልቻሉም አክለዉ አብራርተዋል።

## 4.5 ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

የክፍል ውስጥ ምልከታ ከቃለ መጠይቅ እና ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ ለማጠንከር እና በክፍል ውስጥ የሚደረገውን የዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን ለማረጋገጥ ሲባል በስራ ላይ ውሏል። ይህንንም ለማከናወን ሲባል አጥኚዋ በእያንዳነዱ ትምህርት ቤት አራት ኣራት ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ በመገኘት ምልከታ አካሂዳለች። በድምሩ ሃያ አራት ጊዜ አስራ አምስት ጥያቄዎችን የያዘ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በባለ ሁለት ድርድር (አዎ/ አይደለም) የጥያቄ አቀራረብ ስልት በመጠቀም ምልከታ አካሂዳለች። ጥያቄዎቹ በሶስት ክፍል የተከፈሉ እና የአማርኛ ቋንቋ ዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን ለመፈተሽ የተዘጋጁ ናቸው።

በመጨረሻም በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ውጤት እንደሚከተለው በተዘጋጀው ቼክ ሊስት በመታገዝ እንደየምድባቸው በመግለጽ ተተንትኗል። ለክፍል ምልከታ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በሰንጠረዥ ማስቀመጥ የተፈለገበት ምክንያት በተለያዩ ሶስት ምድቦች የተከፈሉትን የመከታተያ ጥያቄዎች በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችል ለማድረግ ነው። ምድቦቹም የዕቅድ አዘገጃጀትን አስመልክተው የተዘጋጁ የዕቅድ አተገባበርን አስመልክተው የተዘጋጁ እና የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በተመለከተ የተዘጋጁ ጥያቄዎች በማለት በሶስት ዋና ዋና ምድቦች ተከፋፍለው የቀረቡ ናቸው።

በነዚህ ምድቦች የቀረቡት ጥያቄዎችም ጥናቱ በተከናወነባቸው ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያዘጋጁትን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር ምን እንደሚመስል ለማሳየት ያግዛል ተብሎ የታመነበት ስለሆነ የቀረበ ነው።

የዕቅድ አዘገጃጀትን አስመልክቶ በአንድ ተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የተመደቡት ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. መምህሩ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ?

2. መምህሩ ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው ይገባሉ?

3. መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕቅድ አላማውን ከግብ ያደረሰ ነው?

4. ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት አለው?

5. መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት አለው?

ምልከታዉ እንደሚያመለክተው መምህሩ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ? ለሚለው ጥያቄ በአጠቃላይ ከተደረገው ሃያ አራት የክፍል ምልከታ ውስጥ አስራ ስድስቱ አዎ የሚል ሲሆን ስምንቱ አይደለም የሚል ምላሽ የያዘ ነው። ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው የሚጠቀሙ ቢሆኑም ስምንት ያህል ጊዜ ግን መምህራን ያለእቅድ ክፍል እንደሚገቡ ታውቋል፡ ስለዚህ ያለዝግጅት የሚገቡ መምህራን ጥቂት እንዳልሆኑ ለመገመት የሚያስችል ነው።

መምህሩ ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው ይገባሉ?ለሚለው ጥያቄ ከተደረገው የክፍል ምልከታ ውስጥ አስራ ሁለቱ አዎን የሚል ሲሆን አስራ ሁለቱ ደግሞ መምህሩ ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው የማይገቡ መሆኑን ተረጋግጧል። ይህ ደግሞ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ዕቅዱን ከማዘጋጀት በዘለለ በክፍል ትግበራ ወቅት ወደ ክፍል ይዘው በመግባት የማይገለገሉበት መሆኑን የሚያሳይ ነዉ።

መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕቅድ አላማውን ከግብ ያደረሰ ነው? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ከተደረገው የክፍል ምልከታ ውስጥ ሶስቱ አዎ የሚል ሲሆን የሃያ አንዱ ምልከታ እንደሚያመለክተው ደግሞ መምህራኑ የሚያዘጋጁት ዕቅድ አላማውን ከግብ ያደረሰ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ ማለት መምህራን ባቀዱት እቅድ መሰረት የማይተገብሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከተደረገው ምልከታም መረዳት የተቻለው መምህራኑ በትምህርት እቅድ ላይ በአላማ ነድፈው በዕቅዳቸው ላይ ካሰፈሩት ሃሳብ ውጪ በሌላ ክፍለ ጊዜ አላማ ተነድፎለት ሌላ ርዕስ

ሊሆን የሚችል ርዕስ በተደራቢነት ሲተገብሩ ለማየት ተችሏል። ይህ ደግሞ ምናለባት መምህራኑ ያቀዱትን ዕቅድ በተሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ለማጠናቀቅ ከመሻት በዘለለ ሊኖረው የሚችል ጥቅም ይኖራል ብሎ መናገር አስቸጋሪ ይመስላል።
ከክፍል ምልከታው ሁለቱ መምህራኑ ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት ያለው መሆኑን ሲያመለክት ሃያ ሁለቱ ደግሞ መምህራኑ ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በክፍል ውስጥ መምህራን የሚያዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ ዕቅዱን ለመተግበር የሚፈልግ ሌላ አካል በቀላሉ ተረድቶ ወደ ተግባር ሊያሸጋግረው የማይችል መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል።

መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት አለው? ለሚለው የክፍል ምልከታ ጥያቄ ሁለቱ አዎ የሚል ምላሽ ያስገኘ ሲሆን ሃያ ሁለቱ ደግሞ መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ ማለት መምህራኑ አቅደው እየተገበሩ ያለው ዕቅድ ከአመታዊ የትምህርት ዕቅድ ቀድሞ እየተተገረ መሆኑን አሊያም ከአመታዊ ዕቀዱ ወደኋላ ዘግይተው እየተገበሩ መሆኑን የሚያሳ መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ነው። ይሁንና በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታም ሆነ በተከናወነው የሰነድ ፍተሻ መምህራኑ እየተገበሩ ያሉት የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ወደ ኃላ የቀሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ለዚህም በምክንያትነት የሚነሳው ከላይ እንደተጠቀሰው ለትምህርቱ የተሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ከትምህርቱ ይዘት ጋር የማይመጣጠን መሆኑ ይመስላል።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አብዛኛውን ጊዜ መምህራኑ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው ያለመጠቀም፤ቢያዘጋጁም ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው ያለመግባት፤መምህራኑ የሚያዘጋጁት ዕቅድ በሚፈለገው መልኩ አላማውን ከግብ ያደረሰ አለመሆኑ፤ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት የሚጎለው መሆኑን እና መምህራኑ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት የሌለውና በተፈለገው ወቅት መጠናቀቅ የማይችል መሆኑን የሚያሳ ነው።

Elizzabeth (1982፡12) ስለ ትምህርት ዕቅድ ጠቀሜታ ሲያስረዱ ‹‹አጠቃላይ የትምህርት አካሄድ በእቅድ ላይ የተመሰረት በመሆኑ እቅድ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ይኖረዋል፡፡›› ይላሉ፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ Dorothy (1985፡48) ስለዚህ እቅድ ሲናገሩ‹‹የትምህርት እቅድ ስኬታማ ለሆነ የትምህርት ሂደት እንደ መሳሪያ ወይም መርጃ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለጥሩ የማስተማር ሂደት አስፈላጊና እንደመርህም ይጠቅማል›› ይላሉ፡፡ ይህ ማለት የመማር ማስተማርን ሂደት ያለ ዕቅድ ስኬታማ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ በመሆኑም የትምህርትን ሂደት ከግብ ለማድረስ ዕቅድ ወሳኝና ዋነኛ የመምህሩ ተግባር መሆኑን ማወቅና መተግበር ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

የዕቅድ አተገባበርን አስመልክቶ በአንድ ምድብ ውስጥ ተመድበው ምልከታ የተደረገባቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. መምህሩ ባዘጋጁት ዕቅድ መሰረት ይተገብራሉ?
2. መምህሩ የትምህርት ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ ጥረት ያደርጋሉ?
3. ዕቅዳቸውን ባቀዱት ሰአት በአግባቡ ይተገብራሉ/ያጠናቅቃሉ?
4. መምህሩ ለትምህርት ማጠናከሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ይጠቀማሉ?
5. መምህሩ የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ ይከልሳሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በአንድ ምድብ ስር በማድረግ ምልከታ ተከናውኖበታል፡፡

ከላይ መምህሩ ባዘጋጁት ዕቅድ መሰረት ይተገብራሉ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ከክፍል ምልከታው ውስጥ ሁለቱ አዎ የሚል ሲሆን ሃያ ሁለቱ ደግሞ አይደለም የሚል ነው፡፡ ማለትም ያዘጋጁት እቅድ ከሚያሰተምሩት ጉዳይ ጋር አይሄድም፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ባዘጋጁት የትምህርት እቅድ መሰረት መተግበር የማይችሉ መሆኑን ነው፡፡ ከተደረገው የክፍል ምልከታ ውስጥ አራቱ መምህሩ የትምህርት ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ ጥረት ያደርጋሉ? ለሚለው ጥያቄ አራቱ አዎ ያደርጋሉ የሚል ምላሽ ያስገኙ ሲሆን ሃያው አያደርጉም የሚል ምላሽ ነው ያስገኙት፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው

መምህራኑ የትምህርቱ ዕቅድ ይሰካ ዘንድ የተቻላቸውን ጥረት ማድረግ የሚችሉ መሆኑን የሚያሳይ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡ በመቀጠልም መምህራን ዕቅዳቸውን ባቀዱት ሰአት በአግባቡ ይተገብራሉ/ያጠናቅቃሉ? ለሚለው ጥያቄ ሁለቱ አዎ ይተገብራሉ የሚል ምላሽ ያስገኘ ሲሆን ሃያ ሁለቱ አይደለም አይተገብሩም ወይም አያጠናቅቁም የሚል ምላሽ አስገኝቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው መምህራን ባቀዱት ሰአት ዕቅዳቸውን ወደ ተግባር እንዳይለውጡት እንቅፋት የሚሆንባቸው ነገር እንዳለ አመላካች ነው፡፡ በቀጣይነት በክፍል ምልከታው የተስተዋለውና ለመከታተያ ከተዘጋጀው ጥያቄ ማግኘት የተቻለው ምላሽ መምህሩ ለትምህርት ማጠናከሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ይጠቀማሉ? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም ወይም ሃያአራቱም ምልከታ ምንም አይነት የመርጃ መሳሪያ መምህራኑ እንደማይጠቀሙ በእቅዳቸውም ላይ እንዳላካተቱ ለማየት ተችሏል፡፡ የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም  ደግሞ መምህራን ያቀዱትን ዕቅድ ወደ ተግባር ለማሸጋገር ወሳኝ መሆኑን ተመራማሪዎች እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህን የትምህርት መረጃ በተመለከተ Sells (1981፡268) በመማር ማስተማር ሂደት ስለማስተማሪያ ቁሳቁሶች አስፈላጊነት ሲገልፁ ለትምህርት መስጫነት የተለያዩ ዓይነት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በትምህርት ሂደት ላይ መሠረታዊ ምርምርን ይፈጥራሉ፡፡ ሀሳቡን ይሰበስባሉ፡፡ ፍላጎትን ይቀሰቅሳሉ፣ መረዳትን ያጠናክራሉ፣ ዝምድናን ያፀናሉ፣ ትዝታን ይፈጥራሉ፣ ሀሳብን ያነሳሳሉ በተጨማሪም የምንማረውን ትምህርት በማጠናከር ጊዜንና ሀይልን ይቆጥባሉ ይላሉ፡፡

የቋንቋ መምህራን በትምህርት ዕቅዳቸው ላይ ጥሩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማስፈራቸው ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በተገቢው ጊዜና ቦታ የመጠቀምና የተነደፈውን የመማር ማስተማር ዓላማ ግብ ማስገኘት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ መምህራን በተገቢው መንገድ መቼ እንዴትና ምን ወይም የትኛውን ቁሳቁስ ለየትኛው ትምህርት ተገቢ ነው የሚለውን ማወቅ አለባቸው፡፡ Sells (1981፡263) ትክክለኛ የሆነ የማስተማሪያ ቁሳቁስ በትክክለኛው ጊዜና ሁኔታ መጠቀም ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ የምንረዳው መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪዎችን በአግባቡ ቢጠቀሙ ዕቅዳቸውን በሚፈለገው መልኩ ለማከናወን የሚያስችላቸው መሆኑን ነው፡፡

የዕቅድ አተገባበርን አስመልክቶ ከክፍል ምልከታ ምልከታ የተገኘው ሌላው የትግበራ ጥያቄ ደግሞ የሚከተለው ነው። መምህሩ የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ ይከልሳሉ? የሚል ሲሆን የአራት መምህራን ተግባር በአዎንታዊነት የታየ ሲሆን የሃያ ስድስቱ መምህራን ትግበራ ደግሞ አሉታዊ እንደነበር ለመረዳት ተችሏል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ለመከለስ ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑን አመላካች ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ባላቸው ጊዜ በመጠቀም የዕለቱን ትምህርት ለመሸፋን ከማሰብና ያላቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆን ያሳደረባቸው ተጽዕኖ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል።

በአጠቃላይ ከላይ ያለው ሀሳብ እንደሚያመለክተው የመምህራን የዕቅድ አተገባበር ምን እንደሚመስሉ የሚያሳይ ነዉ። የተዘጋጁት የመከታተያ ጥያቄዎችም መምህራን ባዘጋጁት ዕቅድ መሰረት መተግበር አለመተግበራቸውን፣ መምህራን የትምህርት ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ ጥረት ማድረግ አለማድረጋቸውን፣ መምህራን ዕቅዳቸውን ባቀዱት ሰአት በአግባቡ መተግበር አለመተግበራቸውን /ማጠናቀቅ አለማጠናቀቃቸውን መምህራን የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት ያለው መሆኑን እና ተዛማጅነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም መምህራን ለትምህርት ማጠናከሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም አለመጠቀማቸውን እና መምህራን የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ የዕለቱን ትምህርት መከለስ አለመከለሳቸውን ለማረጋገጥ የተዘጋጁ የምልከታ መከታተያ ጥያቄዎች ናቸው።

በመሆኑም ከላይ የተገለጸው ማብራሪያ እንደሚያሳየን የመምህራኑ የዕቅድ አተገባበር ከአዎንታዊ ጎኑ ይልቅ አሉታዊ ጎኑ የሚያመዝን ሆኖ የተገኘ መሆኑን ነው። ከዚህ የምንረዳው ጥናቱ በተከናወነባቸው ትምህርት ቤቶች ተዘጋጅተው የሚተገበሩት የትምህርት ዕቅዶች በተፈለገው መንገድ ስራ ላይ አለመዋላቸውን የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው። በመሆኑም የትምህርት ዕቅዱ በአግባቡ ካልተተገበረ በአመቱ የትምህርት ወቅት መጠናቀቅ የነበረበት የትምህርት ሽፋን ሳይሸፈን ይቀራል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ለትምህርቱ የተሰጠው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ክፍተት ያለበት መሆኑን ያሳያል።

የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን አስመልክቶ በሌላው ተመሳሳይ ምድብ የቀረቡት የመከታተያ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ ነው?
2. ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁዎች ናቸው?
3. መምህሩ ተማሪዎቹን ጥያቄ ይጠይቃሉ?ተማሪዎቹ እንዲጠይቁስ ያበረታታሉ?
4. በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት ተማሪዎች በፍላጎት ይሳተፋሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

ከላይ በመጀመሪያ ለቀረበው "የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ ነው?" ለሚለው ጥያቄ ከክፍል ምልከታ ከተገኘው መረጃ ሁለቱ አዎ የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ ነው የሚል ምላሽ ያስገኘ ሲሆን ሃያ ሁለቱ ደግሞ የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ አለመሆኑን አመልክቷል። ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁዎች ናቸው? ለሚለው ጥያቄ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በሁለት ምልከታ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር በመጠኑ ዝግጁዎች መሆናቸውን ሲያመለክት ሃያ ሁለቱ ምልከታ ደግሞ ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁዎች አለመሆናቸውን የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ የሚያሳየው የተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ዝግጁ አለመሆን መምህራኑ አዘጋጅተው በሚተገብሩት ዕቅድ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድርባቸው መሆኑን ነው። ይህ ማለት የተማሪዎች ለትምህርቱ ተነሳሽነት ማጣት መምህራን ዕቅዳቸውን በተፈለገው ጊዜና ሰአት እንዳያጠናቅቁ እንቅፋት ከመሆኑም ባሻገር በተማሪዎች ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

በሌላ መልኩ መምህራኑ ተማሪዎቹን ጥያቄ ይጠይቃሉ? ተማሪዎቹ እንዲጠይቁስ ያበረታታሉ? ለሚለው ጥያቄ በተደረገው ምልከታ ለማየት የተቻለው ስምንቱ አዎ ተማሪዎችን ያረታታሉ የሚለውን ሲያመለክት፤ ተማሪዎቹንም ይጠይቃሉ የሚል ምላሽ ያስገኘ ሲሆን አስራ ስድስት የሚሆነው ደግሞ አይደለም ወይም አያበረታቱም ተማሪዎቹንም አይጠይቁም የሚል ምላሽ ያስገኘ ሆኗል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎቹን ጥያቄ በመጠየቅና እንዲጠይቁ የማይበረታቱ ከሆነ የተማሪዎቹ ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑን አመላካች ነው። የተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው ተሳትፎ ደግሞ አነስተኛ መሆኑ መምህራን አዘጋጅተው በሚተገብሩት ዕቅድ

ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ የማይቀር መሆኑ የታመነ ነው። ከዚህ ምልከታም የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ይሄንኑ መሆኑን መረዳት ተችሏል።ይህን በተመለከተ Dorothy (1985፡32) "ብቁ መምህራን ያለማቋረጥ ያስተማሯቸውን ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰሩ ባዘጋጁት መሥፈርት ይመዝናሉ። መምህሩም ራሱን ይመዝናል። ይኼውም የተማሪዎችን ፍላጎት መጠበቅ አለመጠበቁን የተጠቀሙባቸው የትምህርት ማጠናከሪያዎች ተገቢ መሆናቸውን በተማሪዎቹ መካከል ባለው ልዩነት ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠና በራሱና በተማሪዎቹ መካከል የነበረውን መስተጋብር በቂ መሆን አለመሆኑን ራሱን ይጠይቃል"ይላሉ።

ከዚህ ባሻገር በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት ተማሪዎች በፍላጎት መሳተፍ አለመሳተፋቸውን ለመረዳት በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ የሚጠቁመን የሚከተለውን ነው። ከተከናወነው ምልከታ ውስጥም አራቱ አዎ በፍላጎት ይሳተፋሉ የሚል ሲሆን የተቀረው ሃያዉ ደግሞ በፍላጎት አይሳተፉም የሚል ምላሽ አስገኝቷል። ከዚህ የምንረዳው ከላይ በሌላዎቹ ምልከታዎች እንዳየነው የተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር በፍላጎት አለመሳተፍ መምህራን በሚተገብሩት ዕቅድ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ መኖሩን አመላካች ነው።

ባጠቃለይ በተጠኚ ተምህርት ቤቶች የተደረገው ምልከታ እንደሚያመለክተው የእቅድ ዝግጅት እና አተገባበሩ ገሚፈለገው በታች ነው። እቅዶች የሚፈለገውን ቅርጽ አና ይዘት ጠብቀው አልተዘጋጁም አራት ያክል ትምህርት ቤቶች እቅድ ከናካቴው የላቸውም። እቅድ አዘገጅተው ይዘው ያልገቡ አሉ። እቅዱ እንደቋንቋትምህርት አሳታስፊ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ አልነበረም። ይህ ሁኔታ የማማር ማስተማሩን ሂደት በአግባቡ ለመከውን አያስችልም። ተማሪዎችን በቋንቋው ብቁ የሆኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ካለማስቻሉም በላይ በውጤታቸው ላይ ጉለህ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። በተግባር የሚታየውም ይሄው እውነታ ነው።

## 4.6. የውጤት ትርጎማና ማብራሪያ (Discussion)

### 4.6.1 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከአዕምሮአዊ ምድብ ክፍሎች አንፃር

ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከተው (Bloom,1956) የትምህርት እቅድ አላማ የአእምሮአዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት እውቀትን፣ ትርጉምን፣ ወደ ተግባር መለወጥን፣ ትንተናን፣ ግንባታንና ግምገማን መለካታቸውን መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል። በመሆኑም በ2011 ዓ.ም ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ያለውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ከአእምሮአዊ ምድብ ማለትም ከእውቀት፣ ከትርጉም፣ ወደ ተግባር ከመለወጥ፣ ከትንታኔ፣ ከግንባታና ከግምገማ አንጻር እንዴት ተቀርጾዋል የሚለውን ለመረዳት የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት በ2011 ዓ.ም ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ያሉት የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ላይ የሰነድ ፍተሻ ምርመራ ተካሂዷል።

ከአእምሮአዊ ምድብ ስር የሚጠቃለሉት ዋና ዋናዎቹ ምድቦች ስድስት እንደሆኑ (Bloom 1956) በምዕራፍ ሁለት ስር ለማሳየት ተሞክሯል። ከነዚህም መካከል በእቅዱ ውስጥ እውቀት የመጀመሪያው ተጠቃሽ ነው። እውቀት ማለት ቀደም ብሎ የተማሩትን ማስታወስን የሚይዘው ክፍል ነው። ይህም አንዳንድ ነገር ከዝርዝር እውነታ ተነስቶ አጠቃላይ ቃለ ነቢብን ለማስታወስና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ስራ ላይ መዋልን እንደሚያጠቃልልና በአእምሮአዊ ክፍል ውስጥ ዝቅተኛውን መደብ የሚያመለክት መሆኑ ተገልጿል። በዚህ መሰረት ከተመረጡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ቅጽ ውስጥ 90(60%) አላማዎች ከአዕምሮአዊ ምድብ ስር ከሚጠቃለለው እውቀትን የሚገልጹ መሆናቸው ከሰነድ ምርመራው የተገኘው መረጃ አረጋግጧል።

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ስለ ቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ይናገራሉ።
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የነፃና ጥገኛ ምዕላድን ምንነት ይገልፃሉ።

ከእውቀት በተጨማሪም ከአእምሮአዊ ምድብ ዝቅተኛ ክፍል ስር የሚጠቃለለው ሌላኛው ትርጉም ነው። ትርጉም ስንል አንድን ነገር ተረድቶ የመያዝና ለዚያ ነገር አስፈላጊውን የመግለጫ ትርጓሜ ወይም ተለዋጭ ትርጓሜ መስጠት መቻልን እንደሚያመለክት ተገልጿል። በመሆኑም በናሙና ከተመረጡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ቅጽ ውስጥ 5(3.33%) አላማዎች ትርጉምን የሚገልጹ መሆኑን ከሰነድ ፍተሻው ከተገኘው መረጃ ተረጋግጧል።

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ከግሶች ሌሎች ግሶችን በመመስረት የምሳሌያዊ ንግግሮችን ፍች ይገልጻሉ፡፡
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ፍች ይዘረዝራሉ፡፡

ሌላው ከአዕምሮዊ ምድብ ዝቅተኛ ደረጃ ስር የሚመደበው በሰስተኛነት ላይ የሚገኘው ወደ ተግባር መለወጥ ነው፡፡ ወደ ተግባር መለወጥ ማለት ቀደም ሲል ያወቁትን፣ የተማሩትን ወደ አዲስና ተጨባጭ ሁኔታ መለወጥ መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል፡፡ በመሆኑም በመረጃ ምንጭነት ከቀረቡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ዝግጅት ቅጽ ውስጥ 45 (30%) አላማዎች ወደ ተግባር መለወጥን የሚገልጹ መሆኑን ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ ,አረጋግጧል፡፡

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የውይይት መመሪያን ተጠቅመው ይወያያሉ፡፡
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ከግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን በመስራት የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው ይፅፋሉ፡፡

ከአዕምሮአዊ ምድብ ውስጥ ከከፍተኛ ደረጃ ስር የሚመደቡት ትንተና፣ ግንባታና ግምገማ መሆናቸውን በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ትንተና ማለት አንድን ነገር ወደ መሰረታዊ ክፍሎች የመበተን ችሎታ ያመለክታል፡፡በዚህም መሰረት በመረጃ ምንጭነት ከቀረቡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ቅጽ ውስጥ 10(6.66%) አላማዎች ትንተናን የሚያመለክቱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ያልተጻፈውን ስነ ጹሑፍ ስነቃልን በየዘርፋቸው ያስቀምጣሉ፡፡
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የልቦለድ አለባውያን ይተነትናሉ፡፡

ከአዕምሮአዊ ምድብ በከፍተኛ ደረጃ ስር ከሚጠቃለሉት ውስጥ ግንባታና ግምገማ መሆናቸውን በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል፡፡

ግንባታ ማለት ልዩ ልዩ ክፍሎችን በአንድ ላይ በመሰብሰብ አንድ አዲስ ነገርን መፍጠር ነው፡፡ ግንባታ ንግግር ማዘጋጀትን፣ጥናት ማካሄድንና የመሰሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ ይህ የምደባ ክፍል የመፍጠር ችሎታን ሊያስጨብጡ የሚችሉ አላማዎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ግምገማ ደግሞ

የአንድን ነገር ዋጋ የመመጠንና የመገምገም ችሎታን ይይዛል። ለምሳሌ የአረፍ ተነገርን፣ የግጥምን፣ የአንድ ጥናታዊ ጽሁፍን፣ የቅርጽ የመሳሰሉትን ደረጃ መገምገምን ያጠቃልላል። ይህም ግምገማ በአንድ በተወሰነ የመገምገሚያ ነጥብ ላይ መመስረት አለበት። የመገምገሚያው ነጥቦች በሚገመገመው ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ወይንም የሚገመገመው ጉዳይ በሌላ በኩል ከሆኑ ነጥቦች የሚወዳደር መሆን አለበት።

እነዚህ ከላይ የተገለጹት ሁለቱ የአዕምሮአዊ ምድብ ክፍሎች በናሙና ከተመረጡ 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማዎች ውስጥ ግንባታ እና ግምገማ ምንም ያልተገለፁ ወይም 0% መሆኑን ከሰነድ ፍተሻው ለማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ ስድስቱን የአዕምሮአዊ ምድብ ከከፍተኛ ደረጃ እና ከዝቅተኛ ደረጃ አንጻር ከናሙና ከቀረቡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ውስጥ 138(92%) አላማዎች ዝቅተኛውን የአዕምሮአዊ ምድብን (እውቀት፣ ትርጉምና ወደ ተግባር መለወጥ) የሚያሳይ ሲሆን ከፍተኛው የአዕምሮአዊ ምድብን ትርጉም ብቻውን 12(8%) አላማዎች በውስጡ የያዘ መሆኑን ያሳያል።

ከዚህ የምንረዳው በአእምሮአዊ ምድብ ከተቀረጹት አላማዎች ውስጥ ከከፍተኛ ደረጃ ይልቅ ዝቅተኛ ደረጃውን መያዛቸውን ከሰነድ ፍተሻ መረጃው ተረጋግጧል።

### 4.6.2 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች አንጻር

ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከተው (Harrow.A.J.1972) የትምህርት እቅድ አላማ የይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት ቅፅበታዊ እንቅስቃሴን (Reflex)፣ መሰረታዊ እንቅስቃሴን (Fundamental movement)፣ ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታን (Perceptual abilities)፣ አካላዊ ችሎታን (Physical ablities)፣ ክሂሎታዊ እንቅስቃሴን (skill movement) ና የማይዋዥቅ ግንኙነትን (Nondiscursive communication) መለካታቸውን መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል። ይህንን የይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ሀሳብ ከቋንቋ ትምህርት ጋር ስናገናኘው አራቱን የቋንቋ ክሂሎች መለማመድንና ማዳበርን የሚመለከት ይሆናል። በመሆኑም በ2011 ዓ.ም ከጥቅምት 1 እስከ

ሚያዚያ 30 ያለውን የአማርኛ ቋንቋ ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ማለትም ከማንበብ፣ ከፅህፈት፣ ከማዳመጥና ከመናገር አንጻር እንዴት ተቀርጸዋል የሚለውን ለመረዳት የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት በ2011 ዓ.ም ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ያሉት የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ላይ የሰነድ ፍተሻ ምርመራ ተካሂዷል።

ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ስር ከሚጠቃለሉት ስድስት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉ Harrow.A.J.(1972) በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል። የእያንዳንዳቸውም ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው የውጤት ትንተና ከዚህ በታች ቀርቧል። ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ስር ከሚካተቱት መካከል የመጀመሪያው ማዳመጥ ነው። ማዳመጥ ድምጾችን ለመለየት፣ መልእክትን ለመረዳት፣ መረጃን ለመቀበል፣ ተናጋሪዎች ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ለማገዝ፣ መልዕክትን ለመገምገም፣ ራስን ለማዝናናትና ንግግርን ለማድነቅ እነዚህን ሀሳቦች አላማ በማድረግ የሚተገበር የክሂል አይነት ነው በማለት (በድሉ 1996፣46) ገልጿል። ይህንንም ሀሳብ ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች ጋር ስናገናኘው ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታን፣ አካላዊ ችሎታንና ክህሎታዊ እንቅስቃሴን በውስጡ ይይዛል።

በዚህ መሰረት በናሙና ከተመረጡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ቅጽ ውስጥ 20(13፣33%) አላማዎች ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ስር ከሚጠቃልለው ውስጥ ማዳመጥን የሚገልጹ መሆናቸው ከሰነድ ምርመራው ተረጋግጧል።

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ከሚያዳምጡት ጽሑፍ በምክንያትና በውጤት የተገለጸ ሀሳቦችን በማስታወሻ ይይዛሉ።
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የሚነበብላቸውን ጽሑፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።

ሌላው ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ስር ከሚካተቱት መካከል ሁለተኛው መናገር ነው። ንግግር በተናጋሪውና በአድማጮ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት ነው።
ማቀበያ ክሂል (productive skill) የሆነው የንግግር ክሂል ይዳብር ዘንድ መቀበያ (receptive skill) የሆነው የማዳመጥ ክሂል መዳበር አለበት። የሁለቱ ክሂሎች መዳበር

በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በአብዛኛው የቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ተግባራት በተለይ አንድ የቋንቋ ክሂል ላይ ማተኮር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተለይ በንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚካሄድ የሁለትዮሽ ቃላዊ ተግባቦት መሆኑን ልብ ማለት ያሻል በማለት (በድሉ 1996፤57) ገልጿል፡፡ ይህንንም ሀሳብ ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች ጋር ስናገናኘው ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታን፣ አካላዊ ችሎታንና ክህሎታዊ እንቅስቃሴን በውስጡ ይይዛል፡፡ በዚህ መሰረት በናሙና ከተመረጡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ዝግጅት ቅጾች ውስጥ 35 (23.33%) አላማዎች ከይበልጥ ክሂሎች ምድብ ስር ከሚጠቃልለው ውስጥ ንግግርን የሚገልጹ መሆናቸው ከሰነድ ምርመራው ተረጋግጧል፡፡

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርቡላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ፡፡
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የተውኔት አለባውያንን ምንነት በሚመለከት ይወያያሉ፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ሐረጋትን በራሳቸው አባባል ያብራራሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ስር የሚካተተው ማንበብ ነው፡፡ ማንበብ ማለት አንድ የቀረበን ፅሑፍ ወይም ነገር ትክክለኛ ድምጾቹንና ድምጸቱን ጠብቆ ማንበብ መቻልን ይመለከታል፡፡ ተማሪዎች ያነበቡትን ጽሁፍ አስመልክቶ ማብራሪያ እንዲሰጡ ቢጠየቁ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍ ይላል፡፡ያነበቡትን ቅንጫቢ ፍሬ ሀሳብ ለምን በዚያ መንገድ እንደተረዱ፣ ፍሬ ሀሳቡ ይህ ነው ብለው ለማጠቃለል ያበቋቸው መረጃዎች ምን እንደሆኑ ምክንያቶቻቸውን እንዲዘረዝሩ ቢደረግ የዘነጓቸውን ጠቃሚ ዝርዝር መረጃዎች ያስታውሳሉ፡፡ ዝርዝር ጉዳዮችን ማስታወስ ደግሞ ማን፣ መቼ፣ እንዴት፣ የት ለምን ከዋናው ሀሳብ /ጭብጥ ጋር እንደሚገናኝ ለማወቅ ይረዳል በማለት (በድሉ 1996፤39-40) ገልጿል፡፡

ይህንንም ሀሳብ ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች ጋር ስናገናኘው ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታን፣ አካላዊች ችሎታን፣ ክህሎታዊ እንቅስቃሴንና የማይዋዥቅ ግንኙነትን በውስጡ ይይዛል፡፡ በመሆኑም ከቀረበው 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ናሙና ውስጥ 45 (30) አላማዎች ማንበብን የሚያመለክቱ መሆናቸውንም ከሰነድ ፍተሻ ተረጋግጧል፡፡

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የስንኞችንና የሐረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ ያብራራሉ።
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የተውኔቱን ዋና ዋና ሀሳቦች በድርጊት ቅደም ተከተል ይገልጻሉ።

በመጨረሻም ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ስር የሚካተተው ፅህፈት ነው። ጥሩ የመጻፍ ችሎታ ተማሪዎች ጥሩ የማሰብ ብልሀት (thinking strategies) እንዲያዳብሩ ያደርጋል። መላመምታትን፣ መጠየቅን፣ ግምት መስጠትን፣ መላምት ማረጋገጥ እና የተደረሰበትን ውጤት መገምገምን እንዲማሩ ያደርጋል (Block and Mangieri,1995; Applebee,Langer and Mullis,1988)። አዘወትሮ የሚጽፍ ተማሪ የሚጽፈውን ይዘት እየከለሰ ይመረምራል፤ ያደራጃል። ከቃላት ጋር ስለሚጫወት የተለያዩ ፍቺዎቻቸውን ያውቃል፤ የአገላለጽ ስልቱን ያዳብራል፤ የራሱን ሀሳብ ማደራጀት ይማራል። ከዚህ በተጨማሪ ጽሁፋቸው በሌላው መነበቡ ለራሳቸው ያላቸውን ግምት ከፍ ያደርጋል፤ ለሌላው አስፈላጊ እንደሆኑ አድርገው ይገምታሉ በማለት (በድሉ1996፣52) ገልጿል።

ይህንንም ሀሳብ ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች ጋር ስናገናኘው ነገሮችን የማገናዘብ ችሎታን፣ አካላዊ ችሎታን፣ ክህሎታዊ እንቅስቃሴንና የማይዋዥቅ ግንኙነትን በውስጡ ይይዛል። በመሆኑም ከቀረበው 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ናሙና ውስጥ 50(33.33%) አላማዎች መጻፍን የሚያመለክቱ መሆናቸውንም ከሰነድ ፍተሻ ተረጋግጧል።

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ስርዐተ ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይጽፋሉ።
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው የተዘረዘሩ ዐ.ነገሮችን ያያይዛሉ።

### 4.6.3 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ከስሜታዊ ምድብ ክፍሎች አንጻር

ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው ስሜታዊ ምድብ እንደ karthwal ,Bloom,Masia, (1973) የሚያጠቃልለው ነገሮች በስሜታዊነት (enthusiasms) የምናይበት ሁኔታ ነው። ለምሳሌ፣ ስሜት፣ እሴቶች (values )፣ አድናቆትን፣ ፍላጎትን፣ ምስጋናን፣ መልመድን፣ ተነሳሽነት እና ዝንባሌዎች ያጠቃልላል። የትምህርት እቅድ አላማ የስሜታዊ ምድብ ተገቢነትን ለመለካት መቀበልን፣ መመለስን፣ ዋጋ መስጠትን፣ ድርጅትንና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠትን መለካታቸውን መታሰብ እንዳለበት ያስገነዝባል። በመሆኑም በ2011 ዓ.ም ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ያለውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ከስሜታዊ ምድብ ማለትም ከመቀበል፣ ከመመለስ፣ ዋጋ ከመስጠት፣ ከድርጅትና ረቂቅ የሆነ ዋጋ ከመስጠት አንጻር እንዴት ተቀርጸዋል የሚለውን ለመረዳት የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት በ2011 ዓ.ም ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ያሉት የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ላይ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል።

ከስሜታዊ ምድብ ስር ከሚጠቃለሉት አምስት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉ Kathwal, Bloom, Masia,(1973) በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል። ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው የእያንዳንዳቸዉ የዉጤት ትንተና ከዚህ በታች ቀርቧል። ከስሜታዊ ምድብ ስር ከሚመደቡት መካከል የመጀመሪያው መቀበል (Receiving) ነው። መቀበል ከዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ሲሆን የሚያመለክተውም የአንድን ተማሪ አንድን ክስተት ወይም ማነቃቂያ ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ነው። ከዚህ በተጨማሪ መቀበል የአንድ ነገር የመኖር ግንዛቤ ሲያውቅ ለዚያ ነገር የራሱን ፍላጎት ሲያሳይ ነገሩን ለመቀበል ዝግጁ ሆኗል ማለት ነው። በዚህ መሰረት በናሙና ከተመረጡት 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ቅጽ ውስጥ 130 (72.2%) አላማዎች ከስሜታዊ ምድብ ስር ከሚጠቃለለው ውስጥ መቀበልን የሚገልጹ መሆናቸው ከሰነድ ምርመራው ተረጋግጧል።

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የማስታወሻ አያያዝ ስልትን ይናገራሉ።
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የምክንያት እና የውጤትን ጥምረት አውቀው ይጠቀሙበታል ተብሎ ይጠበቃል።

ሌላው የስሜታዊ ምድብ ዝቅተኛ ደረጃ ስር የሚመደበው መመለስ (Responding) ነው። መመለስ የሚያመለክተው ተማሪው በክፍል ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ነው። ይህም የሚያመለክተው ተማሪው የአንድን ክስተት ወይም ማነቃቂያ መቀበሉን ብቻ ሳይሆን ስለ ክስተቱ የራሱ የሆነ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን ነው። ተማሪው ለአንድ ነገር መልስ ለመስጠት ዝግጁ ሲሆን/ የቤት ስራ መስራት፣/ በፈቃደኝነት ለመመለስ ቢፈልግ (ከታዘዘው በላይ ሲሰራ፣/ በነገሩ መሰረት ደስተኛ ሲሆን/ ለደስታ መስራት/ በስሜታዊ ምድብ ውስጥ ከፍ ወዳለ ደረጃ መሸጋገሩን የሚያመለክት መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል።

በዚህም መሰረት ከቀረበው150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ዘግጅት ቅጽ ናሙና ውስጥ 130 (72.2%) አላማዎች መመለስን የሚገልጹ መሆኑንም ከሰነድፍተሻው ተረጋግጧል።

አስረጂ፡-

-ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የድርጊት ቅደም ተከተልን መሰረት አድርገው ሀሳባቸውን ያንጸባርቃሉ።

-ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ።

ሌላው ከስሜታዊ ምድብ ስር በሶስተኛነት የሚመደበው ዋጋ መስጠት (Valuing) ነው። ዋጋ መስጠት አንድ ተማሪ ለሚማረው ትምህርት ስለጠቃሚነቱ፣ ስለ እውቀት ሰጪነቱ የራሱ የሆነ ዋጋ ሲሰጠው የበለጠ የመማርና የማወቅ ፍላጎቱ መቀስቀስ ማለት ነው። የዋጋ መስጠቱ ሁኔታ በደረጃ ይለያል። በቀላል (ማለትም በጋራ መስራትን በጋራ የስራ ችሎታ ማሻሻልን) ወደ ከባድ (ማለትም በጋራ ለመስራት ኃላፊነት መቀበልንና) የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። በመሆኑም ከቀረበው 150 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ ናሙና ውስጥ 35(19.4%) አላማዎች ዋጋ መስጠትን የሚያመለክቱ መሆናቸውንም ከሰነድ ፍተሻ ተረጋግጧል።

አስረጂ፡-

- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያብራራሉ።
- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርብላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ።

- ከዚህ ትምህርት በኋላ የክርክር መመሪያን ተከትለው ክርክር ያካሂዳሉ።

ከስሜታዊ ምድብ ስር በአራተኛና በአምስተኛ ምድብ የሚገኙ ትድርጅት (Organization) እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት (Characterization by value complex) መሆናቸው በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልጿል።

ድርጅት የሚያጠቃልለው የተለያዩ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች በማዛመድ እና በውስጣቸው ሊገኝ የሚችለውን ቅራኔ በመፍታት አንድ ጽኑ የሆነ ዋጋ መስጠትን ወይም ማበጀትን ነው። ይህም እንደማወዳደር፣ ማዛመድና መገንበት ያሉት ዋጋ በመስጠት ላይ ማተኮር ነው። የዚህም ውጤት ለጽንሰ ሃሳቡ ዋጋ መስጠትን የእያንዳንዱን ግለ ሰብ ኃላፊነት ማወቅን ወይም የአንድን ስርዐት ማደራጀት የሙያ ትምህርት በማዋቀር ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገት ማምጣትንና የሕዝብን ፍላጎት መሟላትን ያመለክታል። በዚህ ምደባ አማካኝነት የአንድን ሰው ሕይወት፣ የኑሮ ፍልስፍና መያዝ እስከ መቻል ድረስ ይደርሳል።

ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት ማለት ተማሪው እዚህ ደረጃ በሚደርስበት ጊዜ ኑሮውን ለመምራት የሚያስችል ልምድ ያገኛል። ስለሆነም የተማሪው ጠባይ ግልጽ፣ የማይለዋወጥና ሊተነበይ የሚችል ይሆናል። በዚህ የስሜታዊ ምድባ ሰፋ ያለ ስራ የሚያከናውንበት ቢሆንም ዋናው ትኩረት የሚደረገው የግለሰቡን ግላዊ ልምድ እማዳበሩ ላይ ይሆናል።

እነዚህ ከላይ የተገለጹት ሁለቱ የስሜታዊ ምድብ ክፍሎች በናሙናነት ከተመረጡት 10 የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማዎች ውስጥ ምንም ያልታቀዱ ሲሆን በመቶኛ ሲሰላም 0% መሆኑን ከሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል።

## ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት

በዚህ ክፍል የሚቀርበው የጥናቱ ዋና ዋና ሀሳብ እና ግኝት ማጠቃለያና  የትምህርትን እቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር ቃለነቢቦች/ንድፈ ሀሳቦች መሠረት በማድረግ በአጥኚዋ የሚሰነዘር የይሁታ አስተያየት ነው።

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትእና አተገባበርን በጋምቤላ ክልል በጋምቤላ ከተማ እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ ተተኳሪነት መፈተሽ ነው።በመጀመሪያ የእለታዊ የትምህርት እቅዶቹ በእቅድ አወጣጥ/ዝግጅት ወቅት መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች/ዝርዝር ጉዳዮች ከቅርጽ እና ከይዘት አኳያ ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በእያንዳንዳቸው የእለታወዊ ትምህርት እቅዶች ላይ የሰነድ ፍተሸው ተከናወነ። የሰነድ ፍተሻው ስከነወን የእለታዊ ትምህርት እቅድን ከኒግሀም (2009) የትምህርት እቅድ እርከኖችች (Lesson Plan Phases) በስምንት እርከኖች/ ደረጃዎች/ በመመደብ እንደሚከተለው ባቀረበው መሰረት ነው።

እርከን አንድ፤ መግቢያ (Introduction) ፤
እርከን ሁለት፤መደላድል/ መሰረት (Foundation)
እርከን ሶስት፤ አዕምሮን ማነቃቃት (Brain Activation)
እርከን አራት፤ የአዲስ እውቀት / የእለታዊ መረጃ አካላት (Body of New Information)
እርከን አምስት፤ ግልጽ ማድረግ (Clarification)

እርከን ስድስት፤ ማለማመድ እና መከለስ (Practice and Review)
እርከን ሰባት የተናጥል (ግላዊ ልምምድ) (Independent Practice)
እርከን ስምንት፤ መደምደሚያ (Closure)

የትምህርት እቅድ በአብዛኛው እና በመሰረታዊነት እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ከሞላ ጎደል በማካተት መቅረብ እንዳለበት እነ ከኒግሀም/ Cunnigham/ (2009) ፣ ኬንዝ ብያሬ (2010)/ Kenneth Beare/ (2018) በተሸሻለ መልኩ በመዘርዘር አስቀምጠውታል። አንድ መምህር የቱንም ያህል ልምድ እና እውቀት ቢኖረውም ለሚያስተምረው ጉዳይ በስርአቱ የተደራጀ እቅድ ሊኖረው ይገባል በማለት በአጽንኦት ያስገነዝባሉ፡
በዚህ መሰረት እለታዊ የትምህርት እቅድ ዝግጅቶች ተፈትሸው በትክክለኛው መስፈርት ሲመዘኑ ሁሉም በሚያስብል መልኩ በቅርጽም ይሁን በይዘት የትምህርት እቅድ አዘገጃጀት መስፈርቱን በትክክል አያሟሉም። እይንዳንዳቸው ለስሙላ የቀረበ ውስን ነጥቦችን ብቻ የያዙ እቅዶች ናቸው።

በመቀጠል የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አላማ አዘገጃጀት ከብሉምስ ታክሶኖሚ የትምህርት ስፍረቶች አንጻር ሰፈተሸ የትምህርት እቅዱ አላማ አዘገጃጀት በተመለከተ መምህራን የተለያየ አሰራር እንዳላቸው ችግሩ ይታያል። ጥናቱ በዋናነት አላማ አድረጎ የተነሳው ከብሉምስ ታስሶኖሚ (Bloom's taxonomy) አንጻር በአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት እና አተገባበር መፈተሽ ሲሆን በስሩ ቀጣዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል።

1. የዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ባግባቡና በስረዓቱ ተዘጋጅተዉ ይተገበራሉ?
2. የዕለታዊ የትምህርት እቅዶቹ በየደረጃዉ ካለዉ /የዓመት እና የምዕራፍ/ ተጣጥመዉ ይሄዳሉ?
3. ዕለታዊ እቅዶቹን ለማዘጋጀት ወይም ለመተግበር እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸዉ?
4. በዕለታዊ የትምህርት እቅዱ ዉስጥ የሚገለጸዉ የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ ከብሉምስ ታክሶኖሚ አንጻር የሚሄድ ነዉ?

ለጥያቄዎቹ መልስ ለመፈለግ ለጥናቱ በተጠኚነት የተወሰዱት በጋምበላ ክልል በጋምቤላ ከተማ ጋምቤላ ሁለተኛ ትምህርት ቤት እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። ተጠኚዎቹ ከጥቅምት 1 እስከ መያዚያ 30/2011 ዓ.ም ያሉትን የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ በብሉምስ ታክሶኖሚ ቃለ ነቢቦችን ፍተሻ በማድረግ መረጃ ተሰብስቦ ተተንትኗል።

ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት በናሙናነት ከተሰበሰቡት 150 የዕለታዊ እቅድ ውስጥ ከአዕምሮአዊ ምድብ ክፍሎች እውቀት 90 (60%)፣ መረዳት 5(3.33%)፣ ወደ ተግባር መለወጥ 45 (30%)ና ትንተና 10(6.66%) በአላማ ውስጥ የታቀዱ ሲሆን ግንባታና ግምገማ ያለ መታቀዳቸውን ትንተናው አመልክቷል።

ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት በናሙናነት ከተሰበሰቡት 150 የዕለታዊ እቅድ ውስጥ ከስሜታዊ ምድብ ክፍሎች መቀበል 65 (43.33%)፣ መመለስ 55 (36.66%)ና ዋጋ መስጠት 30 (20%) በአላማ ውስጥ የታቀደ ሲሆን ድርጀትና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠት ያለመታቀዳቸውን ትንተናው አመልክቷል።

ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት በናሙናነት ከተሰበሰቡት 150 የዕለታዊ እቅድ ውስጥ ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ክፍሎች ማዳመጥ 20(13.33%)፣ መናገር 35 (23.33%)፣ ማንበብ 45 (30%) እና መጻፍ 50 (33.33%) የታቀደ መሆኑን ትንተናው አመልክቷል። ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤትም ከአዕምሮአዊ ምድብ ክፍሎች ውስጥ እውቀት፣ መረዳት፣ ወደ ተግባር መለወጥና ትንተናን በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ላይ ማቀዳቸውን ግንባታና ግምገማን አለማቀዳቸውን ገልጸዋል። በሌላ በኩል ከስሜታዊ ምድብ ውስጥ መቀበልንና መመለስን በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ላይ ማቀዳቸውን ነገር ግን ዋጋ መስጠትን፣ ድርጅትንና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠትን አለማቀዳቸውን ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪም ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ ውስጥ ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን በዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማ ላይ ማቀዳቸውን ገልጸዋል።

ከመምህራን፤ ከአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች እና ከምክትል ረእሳነ ምምህራን ጋር ከተደረገው ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በተለይ በኢታንግ ወረዳ የትምህርት ክፈለጊዜያት በተለያዩ ምክንያት ስለሚባክን፤የእቅድ ማዘጋጃ ቁሳቁስም ባአግባቡ ስለማይሟላ የትምህርት እቅድ በአግባቡ እንደማይዘጋጅ እና እንደማይተገበር ተመልክቷል። በተለይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እቅድ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በሙያው የሰለጠነ ባለሙያ ባለመኖሩ እቅድ እንደማይዘጋጅ ጸመልክቷል።

የእቅድ በኣግባቡ አለመዘጋጀት እና በተግባር ላይ አለመዋል ከሌሎች ችግሮች ጋር በመደማመር የሚጠበቀውን የቋንቋ ክህሎት ማስገኘት ካለማስቻሉም በለይ በብሄራዊ ድረጃ ለሚሰጠው የኣማርኛ ቋንቋ የተማረዎች ውጤት ማነስ የራሱ የሆነ አሉታዊ ውጤት ሊኖረው ይችላል።

## 5.2 አስተያየት

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የእለታዊ የትምህርት እቅዶቹ በእቅድ አወጣጥ/ዝግጅት ወቅት መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች/ዝርዝር ጉዳዮች ከቅርጽ እና ከይዘት አኳያ ማሟላተቸውን ለማረጋገጥ በእያንዳንዳቸው የእለታወዊ ትምህርት እቅዶች  በተገቢው መንገድ መዘጋጀትና መተግበር አለመቻለቸው ታዉቋል። የብሉምስ ታክሰኖሚ ቃለነቢብን መሰረት በማድረግ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ ትምህርት እቅድ አላማ አዘገጃጀት ወደ ተሻለ የጥራት ደረጃ ለማሳደግ የማስተማር መማር ሂደት በተሻለ ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግና የትምህረቱንም ውጤታማነት ለማጎልበት የታዩ ችግሮች ማሻሻል የሚቻልባቸውን ነጥቦች በተመለከተ አጥኚዋ ከዚህ በታች የሚከተሉትን አስተያየት ሰንዝራለች።

- የእለታዊ የትምህርት እቅዶቹ በእቅድ አወጣጥ/ዝግጅት ወቅት በእየእረከኑ መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች/ዝርዝር ጉዳዮች ከቅርጽ እና ከይዘት አኳያ አሟልተው ቢዘጋጁ እና በተግባር ቢተረጎሙ፣
- መምህራን የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማዎችን ሲያዘጋጁ የአዕምሮአዊ ምድብ (Cognitive domain) ክፍሎችን ውስጥ ግምባታን እና ግምገማን ትኩረት በመስጠት ቢያቅዱ፣

- መምህራን የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማዎች ከስሜታዊ ምድብ (Affective domain) ክፍሎችን ውስጥ ድርጅት እና ረቂቅ የሆነ ዋጋ መስጠትን ትኩረት በመስጠት ቢያዘጋጁ፣
- ለመምህራን የዕለታዊ የትምህርት እቅድ አላማዎች አዘገጃጀት ላይ ማለትም ከአእምሮአዊ ምድብ፣ ከስሜታዊ ምድብና ከይበልጥ ክሂሎታዊ ምድብ (Psychomoter domain) አንጻር ማዘጋጀት እንዳለባቸው፣ የተለያዩ ስልጠናዎችን ቢሰጣቸው የሚሉትን ሀሳቦች ሰንዝራለች።መምህራን በሚያዘጋጁአቸው የትምህርት ዕቅድ ውስጥ የሚነድፏቸው የትምህርት ዓላማና ይዘቶች ውስንና በአንድ ክፍለ ጊዜ መጠናቀቅ የሚችል ሆኖ ቢዘጋጅ፤
- መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት የትምህርትን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚያስችልና ተማሪን በንቃት ሊያሳትፍ የሚችል ተለዋዋጭ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴን ለመጠቀም የዕቅድ አዘገጃጀታቸውን ተለዋዋጭ ቢያደርጉ፤
- የአማርኛ ቋንቋን ዕቅድ አዘገጃጀትን እና አተገባበርን በተመለከተ ባለድርሻ አካላት አስፈላጊ የሆነ ስልጠና በየጊዜው እያዘጋጁ ለመምህራን ቢሰጡ፤
- ተማሪዎቹ ለቋንቋው ያላቸው ግንዛቤና የአማርኛ ቋንቋን ትኩረት እንዳያደርጉበት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው አካላት አልፎ አልፎ መኖራቸው ተገቢ ባለመሆኑ በሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገድ በማመቻት ስላማዊ የሆነ የትምህርት ድባብ ቢፈጠር፤
- መምህራን ትምህርቱን የሚያቅዱባቸው የዕቅድ ቅጾች በሁሉም ትምህርት ቤቶች ማለት ይቻላል ተመሳሳይ አይደሉም፤ ይህ መሆኑ ደግሞ የዕቅዱን አዘገጃጀትና አተገባበር ሁኔታ የተለያየ አድርጎታል። ስለዚህ መምህራን የሚያዘጋጁት የዕቅድ ቅጾች መስፈርቱን የሚያሟላ ተመሳሳይና ወጥ ሆኖ እንዲዘጋጅ ቢደረግ፤
- የዚህ ጥናት አቅራቢ የተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ማጣት፤ የውጤታቸው ዝቅተኛ መሆን ተጨማሪ ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ሌላ ሠፊ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ  መሆኑን ታምናለች።

**ዋቢ መፃህፍት**

መስታወት ከልክሌ። (2009) ።የአማርኛ ቋንቋ የዕለታዊ ትምህርት እቅድ አላማአዘገጃጀት ከብሉም የትምህርት አላማ አመዳደብ አንፃር፣ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን ባሉ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፤በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት። የመመረቂያ ጽሁፍ፣ጅማ ዩኒቨርሲቲ ያልታተመ

ሙሉቀን ታምሩ። (1992) ። በአ/አ ከተማ የሚገኙ የአራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችየ1991 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሳምንታዊ/ ዕለታዊ የትምህርት ቅጽ ብቃት ፍተሻ። ኮተቤ መምህራን ት/ ኮሌጅ (ያልታተመ)።

ማረው አለሙ። (1998) ። ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ። ባህርዳር፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ።

በድሉ ዋቅጅራ። (1996) ። በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር። አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ።

ነቢዩ ሐረገወይን። (2008) ። የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እለታዊ እቅድ አዘገጃጀትና አ**ተገ**ባበር በጢሮ አፈታ ወረዳ እና በኦሞናዳ ወረዳ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ የመመረቂያ ጽሁፍ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ።

ኮኮቤ መኮንን። (2002) ።የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በወምበራ ወረዳ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች።ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

ያለው እንዳወቀ። (2009) ። መሰረታዊ የምርምር መርሆዎችና አተገባበር።አዲስ አበባ፤አልፋ አሳታሚዎች ድርጅት።

ዮሴፍ ደመቀ። (1989) ። የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች አነዳደፍና ይዘቶች አደረጃጀት ብቃት ትንተና፤ አማርኛን በማስተማር ማስተር ድግሪ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ) ።

Amininik, S, (2000). A survey of the implementation of lesson plan in Bushehr University of Medical Sciences.*Presented in the 4th nationa medical education conference in Bushehr.*

*Beare Keenth. (2018).* Standard Lesson Plan Format Guide for ESL Teachers online sourse.

Bloom, B.S.(Ed). (1956). Taxonomy of Educational Objectives: Handbook Cognitive Domain (New York: Mc kay).

Borko, H, & Niles, J.A. (1987).Descriptions of teacher planning: Ideas for teachers and researchers, In.V. Richardson. Kochler(Ed), Educator'

Handbook: A research perspective (pp.167-187).New York Longman.

Cunnigham Gini (2009). The New Teacher's Campanion; Practical Wisdom for Succeeding in the Classrom. ASCD.org

Dorothy, R. (1985). Teaching Elementary Language. Canada. Dr. Bob kizli http//www.adprima.com/mistaks.htm

Elizzabeth, P. (1982). Effective Teaching apractical Guide to Improv Teaching. New York, Longman.

Escope, (2012) English Language Proficiency Standards and the 5E Model oInstruction, Region XIII Education Service Center, Austin, IXRetrieve

Farrell, T. S. C. (2002) Lesson Planning in Methodology in Language Teaching An Anthology of Current Practice, Jack C. Richards (Editor), Will A. Renandya (Editor) New York: Cambridge University Press

Fink, Dl. (2005).http;//ida edtl. Org/wp.content /up.loads/2014/11/ide Paper 42.pdf

Gwang chol chang (2006) Strategic Planning in Education, Paris

Hargreaves, D.H. (1972). Interpersonal relation and education. London Routledge and KaganPaul.

Harmer, J. (1991). The practice of English Language Teaching. (Ne edition). New York, Longman publishing.

Harrow.A.J.(1972).A taxonomy of the psychomotor domain: A guide for developing behavioural objectives; New York: David Mckay.

Houston, D. & Beech, M. (2002). Designing Lessons for the Diverse Classrooa Handbook for Teachers. *Florida Department of Education.*

Jensen. (2001)How do elementary school teacher plan? The nature ofthe planning process and influences onit. The Elementary schoo journal 81(1), 4-23.

Julie Ann Van Sickle (2011). LESSON STUDY'S IMPACTS ON TEACHER PERCEPTION OFEFFICACY IN TEACHING Master's paper, Humboldt State University

Naimie, Z.et al. (2012). Have You Heard About The New Fashion? (Tailorin Your Lesson Plan Based on Learners Preferences) Procedia *Social and Behavioral Sciences* 46 (2012) 5840 – 5844. Retrieve From: www.science direct.com.

Richards, J, C, &C. Lock hart.(1996). Reflective Teaching in second Language Class rooms. Cambridge University press

Richards, J. C. (1998) what is the use of lesson plans? In J. Richards (Ed.Beyond Training, 103- 121, New York: Cambridge University

PressSpooner, F. (2007) Effects of Training in Universal Design for Learning o Lesson Plan Development, Remedial and Special Education, 28 108-116

Spratt, M., Pulverness, A., & Williams, M. (2005). *The TKT course*. Cambridge Cambridge University Press.

Purgason, K. B. (1991) Planning lessons and units. In Celce-Murcia (Ed.)Teaching English as a Second or Foreign Language (2nd ed.),41431, Boston, MA: Heinle & Heinle.

Taylor,P.H. ( 1970). How teachers plan their courses.Sloph,England National Foundation for Educational Research in England and Wales.

Tyler, R.W. (1949).Basic Principles of curriculum and Instruction.( Chicago Unveristy of Chicago press).

Volkan Cicek and Hidayet Tok (2009), Effective Use of Lesson Plans to Enhance Education in U.S. and Turkish Kindergarten thru 12th Grade Public School System: A Comparative Study, InternationalJournal of Teaching and Education Vol. II (No. 2)

Wei, Meile.(2006). The importance of lesson planning. Retrieved fro http://zxb.xmycxx.com/jiaoxue/ShowArticle.asp?ArticleID=824

Yıldırım, A. (2003). Instructional planning in a centralized school systemLessons of a study among primary school teachers iTurkey.*International Review of Education,* 49(5), Pp: 523-543.

Yi, Ming (2012). The daily lesson plan. Retrieved from http://www.060s.com/ oJan 20, 2013.